# የአያያዥ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ጥናት በአራት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መነሻነት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ለድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ጥናት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም. ኤ. ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ

ብርሃኑ አንዱዓለም

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# የአያያዥ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ጥናት በአራት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መነሻነት

በ

ብርሃኑ አንዱዓለም

ሰኔ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአያያዥ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ጥናት በአራት የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መነሻነት

በ

ብርሃኑ አንዱዓለም

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና ............ i

የሰንጠረዥ ማውጫ ............ ii

የአባሪ ማውጫ ............ iv

አጠቃሎ ............ v

ምዕራፍ አንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ............ 1

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ............ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን ............ 2

ምዕራፍ ሁለት ............ 3

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ............ 5

2.1 የዕህሬት ክሂል ምንነት ............ 5

2.2 የዕህሬት ክሂል አስፈላጊነት ............ 5

2.3 በንግግርና በዕህሬት ክሂሎች መካከል ያለ አንድነትና ልዩነት ............ 7

2.4 የዕህሬት ክሂል የትኩረት አቅጣጫዎች ............ 9

2.5 የዕህሬት ክሂልን ማስተማር ............ 11

2.6 የአያያዥ ቃላት ምንነት ............ 13

2.7 የአያያዥ ቃላት ተግባርና ጠቀሜታ ............ 14

2.8 የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ ............ 16

2.9 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ............ 18

ምዕራፍ ሦስት ............ 24

የአጠናን ዘዴ ............ 26

3.1 የጥናቱ ክልል እና የትምህርትቤቶች ናሙና አመራረጥ ............ 26

3.1.1 የክልል ናሙና አመራረጥ ............ 26

3.1.2 የትምህርት ቤቶች አመራረጥ ............ 26

3.1.3 የተማሪዎች አመራረጥ ............ 26

3.1.4 የመምህራን አመራረጥ ............ 27

3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ............ 27

3.2.1 የፅሑፍ መረጃ /ድርሰት/ ............ 27

............ 28

3.2.2 የዕሑፍ መጠይቅ ........ 29
3.2.3 ቃለ መጠይቅ ........ 29
3.3 የመረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል ........ 29
3.3.1 የፅሑፍ መረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል ........ 29
3.3.2 የፅሑፍ መጠይቅ መረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል ........ 29
3.3.3 የቃለ መጠይቅ መረጃ አወሳሰድ ቅድም ተከተል ........ 30
3.4 የፅሑፍ መረጃው የአስተራረም ሂደት ........ 30
3.5 የጥናቱ ዘዴ ........ 30
3.5.1 ዓይነታዊ ዘዴ ........ 30
3.5.2 አሃዛዊ ዘዴ ........ 30
3.6 የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈል፣ አመዳደብ ምርጫ (የአመራረጥ) ሁኔታ ........ 30
ምዕራፍ አራት ........ 37
የመረጃዎች ትንተናና ውጤት ........ 37
4.1 የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት ........ 37
4.1.1 የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት መረጃ ትንተና ........ 38
4.1.2 የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት መረጃ ትንተና ........ 45
4.2 ድርሰት አንድ እና ሁለት ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ተገቢ መሆን አለመሆን አንፃር ........ 50
4.2.1 ምድብ "ሀ" የድርጊት /የጊዜ/ ቅደም ተከተልን የሚያመለክቱ ጊዜ ጠቀስ (Temporal) አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 50
4.2.2. ምድብ "ለ" የፀሐፊው የዕሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሃረጋት ........ 55
4.2.2.1 ክትትሎሽን አመልካች /Sequencing/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 56
4.2.2.2 በድጋሚ መግለፅ /Re-expressing/ ........ 58
4.2.2.3 ነጥሎ ማመልከት (Specifying) ........ 59
4.2.2.4 ለይቶ ማመልከት (Referring) ........ 61
4.2.2.5 በድጋሚ ማንሳት (Resuming) ........ 62
4.2.2.6 ምሳሌ መስጠት (Exemplifying) ........ 64
4.2.2.7 ማጠቃለያ (Summarizing) ........ 65
4.2.2.8 ትኩረት መስጠት (Focusing) ........ 67
4.2.3 ምድብ "ሐ" የፀሀፊውን አተያይ /አመለካከት/ የሚያመላክቱ አያያገሮች ........ 70
4.2.3.1 አካይ (Additive) ........ 71
4.2.3.1.1 ተጨማሪ ማስረጃን መጥቀስ (Aducing further evidence) ........ 71
4.2.3.1.2 የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር (De-emphasizing) ........ 72
4.2.3.2 ልየታ (Adversative) ........ 74

4.2.3.2.1መካድ /ማስተባበል/ (Denying expectation) ........ 75
4.2.3.2.2 ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል (admitting the unexpected) ........ 76
4.2.3.2.3 የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሊከሰት እንደሚችል መንገር (Correcting from expected to un expected) ........ 77
4.2.3.2.4 ማነፃፀር (Contrasting) ........ 78
4.2.3.2.5 የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ (Dismissing) ........ 79
4.2.3.3 ሰበባዊ (Causal) ........ 80
4.2.3.3.1 አጠቃላይ (General) ........ 80
4.2.3.3.2 ምክንያታዊ (Reason) ........ 81
4.2.3.3.3 ውጤት (Result) ........ 82
4.2.3.3.4 ዓላማ (Purpose) ........ 83
4.2.3.3.5 ሁኔታ (Condition) ........ 83
4.3 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና የመምህራን ቃለመጠይቅ ትንተና ........ 86
4.3.1 የፅሁፍ መጠይቅና የቃለ መጠይቅ ትንተና ........ 86
ምዕራፍ አምስት ........ 102
ማጠቃለያና አስተያየት ........ 102
5.1 ማጠቃለያ ........ 102
5.1 አስተያየት ........ 104
ዋቢ ፅሁፎች ........ 106
አባሪዎች ........ 109

## ምስጋና

እዚህ ላደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው፡፡

ይህ ጥናታዊ ስራ ተጀምሮ ፍጻሜ ላይ እንዲደርስ የቅርብ ክትትል፣ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግና በማማከር ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለረዳት ፕሮፌሰር ጌታቸው እንዳላማው ከፍ ያለና የላቀ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የጥናትና ምርምር ስራዬ እንዲሳካ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ያለኝን የአክብሮት ምስጋና እገልፃለሁ፡፡ ለዚህ ጥናት መሳካት በተለያየ መልኩ ድጋ ላደረጋችሁልኝ ውድ ወንድሞቼና ጓደኞቼ ለአቶ ጌታሰጠኝ እንግዳ ለአቶ ተክላይ ትዕዛዙ፣ ለአቶ ተገኝ አህመድ፣ ለአቶ በላይሁን አውላቸው፣ ለአቶ ዳንኤል አባተ፣ ለአቶ ነፃነት ደመቀ፣ ለአቶ መስፍን ደፈረሱና ለአቶ አስናቀ ዋስይሁን ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

የቤተሰብን ኃላፊነት ተሸክመሽ በገንዘብም በሞራልም ከጎኔ ሳትለይ እዚህ ላደረሽኝ ብርታትና ጉልበት ለሆንሽኝ ውዷ ባለቤቴ ለወይዘሮ ለምለም እውነቱ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባሁ፡፡ የአባትነት ፍቅር ተነፍጋችሁ የመጫወት ነፃነት አጥታችሁ ለነበራችሁት ታጋሾቹ ልጆቼ ተማሪ ናትናኤል ብርሃኑና ተማሪ ዮናስ ብርሃኑ በጣም አመሰግናለሁ፤ እወዳችኋለሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ፡፡

በመጨረሻም በከፍተኛ ትዕግስትና ጥንቃቄ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳትል የቀረበላትን የፅሁፍ ስራ ሁሉ በምፈልገው ጊዜና ወቅት በማድረስ በኮምፒውተር ለተየበችልኝና ለአራባችልኝ ለወይዘሪት ሰብለ ተሰማ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1:- የናመና ትምህርት ቤቶች የመማሪያ ምድቦች በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት ........ 27
ሠንጠረዥ 2:- ምድብ “ሀ” የፅሁፍን ሁነት (events) ሲዘገብ የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 31
ሠንጠረዥ 3:- ምድብ “ለ” የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 32
ሠንጠረዥ 4:- ምድብ “ሐ” ፀሀፊው በፅሁፉ ውስጥ ስላስፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ያለውን አተያይ/አመለካከት/ የሚያመለክቱ አያገሮች ........ 33
ሠንጠረዥ 5: የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ውስጥ ተገቢ የሆኑ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ........ 39
ሠንጠረዥ 6:- የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከአያያዥ ቃላትና አመዳደብና አከፋፈል አንፃር ........ 40
ሠንጠረዥ 7:- በግል ትምህርት ቤቶች የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዝርዝር ስርጭት ........ 43
ሠንጠረዥ 8: የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ........ 45
ሠንጠረዥ 9:- የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከተገቢ የአያያዥ ቃላት አመዳደብና አከፋፈል አንፃር ........ 47
ሠንጠረዥ 10:- በመንግስት ት/ቤቶች የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዝርዝር ስርጭት ........ 48
ሠንጠረዥ 11:- ተተኳሪዎች ስለአያያዥ ቃላት ምንነትና አከፋፈል መማር አለመማራቸውን የገለፁበት ምላሽ ........ 86
ሠንጠረዥ 12:- አያያዥ ቃላት በስንት ይከፈላሉ ........ 88
ሠንጠረዥ 13:- የፅሁፍ ሁነት (event) ሲዘጋ የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላትን በተመለከተ ........ 89
ሰንጠረዥ 14:- ፅሁፍን ለማደራጀት የሀሳብ ቅደም ተከተልን ለመጠበቅ የሚያገለግል አያያዥ ቃላትን በተመለከተ ........ 91
ሠንጠረዥ 15:- የፀሀፊውን አተያይ አመለካከት ለማሳዬት የሚረዱ አያያዥ ቃላት ሀረጋት ........ 92
ሠንጠረዥ 16:- ተጨማሪ ሀሳብን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የሚረዱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 93

ሠንጠረዥ 17:- ተቃራኒ ሀሳብን ለመግለፅ የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 94
ሠንጠረዥ 18:- ምክንያትን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የሚጠቅሙ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ........ 96
ሠንጠረዥ 19: ስለ ድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ ተማሪዎችዎ ተምረው ያውቃሉ? ለተማሪዎች የድርሰት እርማት ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀም አኳያ ተሰጧቸው ያውቃል? ........ 97
ማጠቃለያ 1:- የምድብ “ሀ” አያያዥ ቃላት አጠቃቀም ........ 55
ማጠቃለያ 2:- የምድብ “ለ” አያያዥ ቃላት አጠቃቀም ........ 70
ማጠቃለያ 3:- የምድብ “ሐ” አያያዥ ቃላት አጠቃቀም ........ 85

# የአባሪ ማውጫ


አባሪ 1፡ የድርሰት አንድ የአፃፃፍ መመሪያ ............ 109

አባሪ 2፡ የድርሰት ሁለት የአፃፃፍ መመሪያ ............ 110

አባሪ 3፡ የድርሰት እርማት መመሪያ ............ 112

አባሪ 4፡ ለተጠኝ ተማሪዎች የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ ............ 116

አባሪ 5፡ ለመምህራን የቀረበ ቃለ መጠይቅና ዝርዝር መልሶቻቸው ............ 120

አባሪ 6፡ Hallidays and Hassan's Classification of Discourse Markers ............ 130

አባሪ 7፡ Trimbl's Classification of Discourse Maters ............ 131

አባሪ 8፡ Nutall's classification of Discourse Markers ............ 132

አባሪ 9፡ የመምህራን የድርሰት እርማት አማካይ ውጤት ............ 133

አባሪ 10፡ ማረሚያ ቅፅና የተማሪዎች ድርሰት ............ 141

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት የአያያዥ ቃላትና ሐረጋትን አጠቃቀም በተመለከተ በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ስር ባሉ የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተገለገሉባቸውን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ከአጠቃቀም ተገቢነት አኳያ ለመፈተሽ የተደረገ ጥናት ነው፡፡ ከተጠኝዎች ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ድርሰቶችን ፅፈዋል፣ የፅሑፍ መጠይቆችን ሞልተዋል፣ ከአማርኛ ቋንቋ መምህሮቻቸውም የቃለ መጠይቅ መልሶች ተገኝተዋል፡፡ ተጠኝዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ በድምሩ (በአጠቃላይ) 2901 አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ሲጠቀሙ 415ቱ የአጠቃቀም ስህተት/ጉድለት/ ታይቶባቸዋል፡፡ 2486 ያህሉ ደግሞ በአጠቃቀም ተገቢነት የተመዘገቡ ሲሆን ይህንንም ተገቢ አጠቃቀም በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አመዳደብና አከፋፈል ሂደት ተከፋፍሎ ሲታይ፡- በምድብ "ሀ" የፅሁፍ ሁነት (event) ሲዘገብ የጊዜ ቀደም ተከተልን የሚያመለክቱ ጊዜ ጠቀስ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት 450 ያህል፣ በምድብ "ለ" (የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት) የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት 438 ያህል፣ በምድብ "ሐ" (ፀሀፊው በፅሁፍ ውስጥ ስላሰፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች . . . ወዘተ ያለውን አተያይ (አመለካከት) የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ደግሞ 1598 ያህል ሆነዋል፡፡ ከላይ ከቀረቡት የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አመዳደብና አከፋፈል አኳያ ከተጠኝዎች በብዛት የተጠቀሙበት ምድብ "ሐ" ሲሆን የተጠቀሙባቸው አያያገሮች ብዛት 1598(64.28%) ሆኗል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሠረት መምህራንን ከዘመናዊ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት/ዲስኩር አመልካቾች/ አጠቃቀም አመዳደብና አከፋፈል ዘዴዎች ጋር ማስተዋወቅ፣ በማስተማሪያ መፃህፍት ዝግጅትም ሆነ በሰው ኃይል ስልጠና በኩል ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣ በበቂ ሁኔታ አጋዥ መፃህፍትን ማዘጋጀት፣ መምህራን የተማሪዎችን የድርሰት መፃፍ ፍላጎት ለማነሳሳት የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንዲሁም የድርሰት መፃፍ ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣ ተማሪዎች በጽሁፎቻቸው ውስጥ ለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላት አገባብ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ፣ የሚሉት በመፍትሔ ሀሳብነት ተሰንዝረዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ፅሑፍ ሐሳብን፣ እምነትን፣ እውቀትን፣ አዲስ ግኝትን፣ ወዘተ. በፊደሎች ወይም በቋንቋ ምልክቶች አማካይነት ከፀሐፊው ወደ አንባቢው ለማስተላለፍ የሚያስችል ክሂል ነው:: ሃሳብን በፅሕፈት አማካይነት ለሌላው አካል ለማስተላለፍ የቋንቋውን ስርዓት የጠበቁ እርስ በርሳቸው የተያያዙ ቃላትን፣ ሐረጋትን እና ዓረፍተ ነገሮችን ማፍለቅን ይጠይቃል:: እንዲሁም አያያዥ ቃላትን እና ሐረጋትን በተገቢው መንገድ መገልገልን ግድ ይላል::

ፅሑፍ ግጥምጥምነትን (Coherence) ለመጠበቅ አያያዥ ቃላትን እና ሐጋትን በመገልገል ብቻ የሚከናወን ባይሆንም (ምክንያቱም በፅሑፍ ውስጥ የሚገኙ ሐሳቦች እርስ በርስ የተሰናሰሉ ከሆኑ ፅሑፉ ግጥምጥምነት ሊኖረው ስለሚችል ነው) አያያዥ ቃላትና ሐረጋት የአንድን ፅሑፍ የሐሳብ ፍሰት በመጠበቅ እና የፀሐፊውን አተያይ በማመልከት ረገድ ጉልህ ድርሻ እንደሚያበረክቱMccarthy (1991); Haliday and Hassan, (1976) ይገልፃሉ:: White (1980:16) ም ፅሁፍ ዓረፍተ ነገርን ከማፍለቅ በላይ በመሆኑ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ እና ተጠየቃዊ አካሄድን የተከተሉ ዓረፍተ ነገሮችን የመፃፍ ችሎታ እንደሚጠይቅ እና ፅሑፍ የሚፃፍበትን ዓላማም ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ ያስገነዝባሉ:: አማረ (1976:130) በበኩላቸው አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት የተለያዩ ሐሳቦች ግንኙነት እና ውህደት እንዲኖራቸው በዐረፍተ ነገሮችም ሆነ በአንቀፆች መካከል መነጣጠል እንዳይኖር የሚረዱ መሆናቸውን ያስረዳሉ::

ስለሆነም ከፍ ሲል ከቀረቡት ጥቅሶች መረዳት እንደሚቻለው የአንድን ፅሑፍ ውሁድነት ወይም ግጥምጥምነት ለመጠበቅ በቋንቋው ውስጥ ከሚገኙ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት መካከል ተገቢ አያያዥሮችን በተገቢ ቦታቸው መርጦ መጠቀም አስፈላጊ ነው:: ከዚህ አኳያ የፅሁፈት ክሂልን ይበልጥ መለማመድና ማዳበር ወሳኝ ነው:: በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ባስተማረባቸው በርካታ ዓመታት ውስጥ ተማሪዎች ሐሳባቸውን እና ስሜታቸውን በተገቢው መንገድ እንዳያስተላልፉ ከሚያስቸግሯቸው መካከል የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እውቀት ማነስ ሆኖ አግኝቶታል:: ከዚህ አኳያ አፋቸውን በአማርኛ ቋንቋ የፈቱ በመንግሥት እና በግል ትምህርትቤቶች የሚማሩ የአስረ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሚፅፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት ቢጠና ከላይ የተጠቀሰውን ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል በሚል እምነት ይህ ጥናት ሲወጠን ችሏል::

ከዚህ ሌላ ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ በሚፈፅሟቸው ስህተቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው ያጠኑ ተመራማሪዎች ቢኖሩም ተማዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት ላይ ያተኮሩ ባለመኖራቸው ይህንን ጥናት ለማጥናት ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል:: ሆኖም ጌታቸው (1987)፣ በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የሚማሩ ተማሪዎች በፃፏቸው ተራኪ ውህድ አህዶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት (discourse markers) ስርጭት እና ተግባር አጥንተዋል:: ጌታቸው (1987) Halliday and Hassan (1976)ን በመጥቀስ አያያዥ ቃላትን እና ሐረጋትን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል ተመልክተዋል:: ይህ ጥናት ደግሞ በNuttal (1982:96-98) አከፋፈልና አመዳደብ ላይ የተመሠረተ ነው:: አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን በሶስት ዋና ዋና ምድቦችና በሌሎች ንዑስ ክፍሎች ተከፋፍለውና ተለይተው ቀርበዋል:: በዚህ መሠረት ዋና ዋና ምድቦቹ:- 1. አንድ ዕሑፍ ሁነት ሲከወን የተዘገበበትን ቅደም ተከተል የሚያመለክቱ 2. አንድ ፀሐፊ ዕሑፉን የሚያደራጅበትን ስልት የሚያመለክቱ 3 አንድ ፀሐፊ ስለሚፅፈው ጉዳይ ያለውን አተያይ የሚገልፅበትን መንገድ የሚያመለክቱ ናቸው:: ከዚህ አኳያ የዚህ ጥናት አቅራቢ ተጠኝ ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀማቸው ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው::

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመንግስት እና በግል የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት መመርመር ነው:: ስለሆነም በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች ተጠይቀዋል፤ እነዚህም:-

1. ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት ምን ይመስላል?
2. ተጠኚ ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ አያያዥ ቃላትን እና ሐረጋትን ከአላማቸው አኳያ በተገቢ መንገድ ይጠቀሙባቸዋል?
3. በመንግሥት እና በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት የተሻሉት የትኞቹ ናቸው? የሚሉ ናቸው::

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል::

1. ይህ ጥናት በመንግሥት እና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት በሚመለከት መረጃ ስለሚሰጥ ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው አካላት ተጠቃሚ ይሆናሉ::

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ችሎታ ተረድተው እንዴት መረዳት እና መደገፍ እንደሚገባቸው ሐሳብ ይሰጣል፡፡
3. በመንግስት እና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት ልዩነት መረጃ ስለሚሰጥ ልዩነቶቹን ለመቅረፍ የሚቻልበትን መንገድ በተመለከተ ሐሳብ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም በመካከላቸው የአጠቃቀም እና የስርጭት ልዩነት ካለም ልዩነቱ የሚጠብበትን መንገድ ለመሻት ያግዛል፡፡
4. ይህ ጥናት ወደፊት በተመሳሳይ ርእስ ጥናት ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በዋናነት ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በናሙናነት በተመረጡ በመንግስትና በግል የመሰናዶ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተጠኝ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን አጠቃቀም እና ስርጭት መመርመር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ጥናቱ በ2000 ዓ.ም. በዕጣ ናሙና አመራረጥ በተመረጡት ከፍተኛ 23፣ የካቲት 12፣ እናት እና ኮከብ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተጠኝ ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኩራል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈፅሟቸው ሌሎች ስህተቶች /የቋንቋ አጠቃቀም፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ወዘተ./ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት አይሆኑም፡፡ እንዲሁም በድርሰት አፃፃፍ ስልታቸው ላይ ትኩረት አድርጎ አይመረምርም፡፡

### የስያሜ ቃላት አጠቃቀም ግላዊ እና መዳዬ ቃላት

**Discourse markers** /ዲስኩር አመልካቾች/፡- በዚህ ጥናት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /መስተፃምራን/ የሚለውን ስያሜ እንዲይዝ ተደረጓል፡፡

### ሙዳዬ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሁኔታ | Condition |
| ለይቶ ማመልከት | Referring |
| ማነፃፀር | Contrasting |
| ማጠቃለል | Summarizing |
| ምሳሌ መስጠት | Exemplifying |
| ምክንታያዊ | Reason |
| ምጋቤ ምላሽ | Feedback |
| ርዕሰ ጉዳይ | Topic areas |
| ሰዋስው | Grammar |
| ቃላት | Vocabulary |

| | |
|---|---|
| ቃላትን መምረጥ | Choosing vocabulary |
| ቅርፅ | Form |
| ቅደም ተከተል አመልካች | Sequencing |
| ቅጥያዎች | Affixes |
| በዝርዝር መግለፅ | Specifying |
| በድጋሚ መግለፅ | Re-expressing |
| በድጋሚ ማንሳት | Resuming |
| ብዛት | Quantity |
| ብያኔ | Definition |
| ተለዋዋጮች | Variables |
| መካድ /ማስተባበል/ | Denying expectation |
| ተቃራኒ ቃላት | Antinomies |
| ተዛማጅ ምስረታ | Relative structure |
| ተዛማጅ ቃላት | Synonyms |
| ተዛምዷዊ ትርጉም | Meaning relationships |
| ተገቢነት | Appropriateness |
| ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ | Adducing further and evidence |
| ትርጉም | Translation |
| ትኩረት መስጠት | Focusing |
| ንበት | Pronunciation |
| አውድ | Context |
| አጠቃላይ | General |
| ዓላማ | Purpose |
| ውጤት | Result |
| የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ | Dismissing |
| የተነገረውን ሃሳብ መሸርሸር | Deemphasizing |
| የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ሊከሰት እንደሚችል መንገር | Correcting from expected to unexpected |
| ያልተጠበቀ ነገር እንደሚከሰት መቀበል | Admitting the unexpected |
| ድግግሞሽ | Frequency |
| ጥምር ቃል | Compound word |
| ፍላጎት | Need |

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

## 2.1 የፅህፈት ክሂል ምንነት

የሰው ልጅ ሃሳብ ከሚለዋወጥባቸውና ተግባቦትን ከሚፈጥርባቸው መሣሪያዎች ውስጥ አንዱ ፅሁፍ ነው። የፅህፈትን ክሂል ምንነት በተመለከተ የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን ከሰጧቸው ብያኔዎች መካከል የተወሰኑትን እንመልከት:-

የፅህፈት ክሂል የቋንቋ ድምፆችን ከወካይ ምልክቶቻቸው ጋር በማዛመድ የቋንቋውን ስርዓት በመከተል ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር መልዕክትን የምናስተላልፍበት ክሂል ነው (Byren 1988:147)።

Lado (1964:33) ደግሞ ፅሁፍ የቋንቋ ድምፆችን በሚወክሉና በሚነበቡ ምልክቶች የሚቀርብ ሲሆን አንድ ሰው ሀሳቡን ለሌላው ማለትም ቋንቋውን ለሚያውቅና አንብቦ መልዕክቱን ሊረዳ ለሚችል ሰው የሚያስተላልፍበት የቋንቋ ክሂል ነው። ነገር ግን በምልክቶች /በትዕምርቶች/ አማካይነት የሚተላለፍ መልዕክት ሁሉ ፅሁፍ ነው ሊባል እንደማይቻል አክለው ይገልፃሉ።

ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች የምንገነዘበው የፅህፈት ክሂል የቋንቋ ድምፆችን በሚወክሉ ምልክቶች አማካይነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር ቋንቋውን ለሚናገርና ለሚረዳ አንባቢ መልዕክትን የምናስተላለፍበት ጥበብ ነው ሀሳብን በፅሁፍ አማካይነት ለሌላው ለማስተላለፍ ደግሞ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት /ህግ/ የጠበቁ እርስበርሳቸው የሳሰሩ (የተያያዙ) ቃላትን፣ ሀረጎችንና ዓረፍተ ነገሮችን ማፍለቅ ይጠይቃል።

የፅህፈት ክሂል ሀሳብን ወረቀት ላይ ማስፈር ብቻ እንዳልሆነና የራሱ የሆኑ ችሎታዎችን እንደሚጠይቅ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል ተክሉ(1989:5)፣ Allen and Cambel (1982)ን ጠቅሰው ፅሁፍ በወረቀት ላይ ሀሳብን በድምፅ ምልክቶች ቀርፆ ከማስተላለፍ ይልቃል። ፅሁፍ ግልፅ ዓላማ ያለው፣ የተመረጡ ልምዶችን የሚያቅፍ፣ በትምህርት የሚገኙ ዕንስ ሀሳቦችንና ክሂሎችን የሚያካትት ችሎታ ነው። ከፅሁፍ ሰዎች የሚቀስሙት የቋንቋውን ክሂልና በቋንቋው የሚተላለፈውን እውቀት ነው የክሂልና የዕውቀት ትስስር የሚንፀባረቀውም በዚህ መንገድ ነው ይላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ Nunan (1989:30) ይህንኑ ሀሳብ አፅንኦት ሰጥተው ሲገልፁት ፅህፈት ሀሳብን በወረቀት ላይ ማስፈር ብቻ አይደለም:: ከዚያም በላይ ውስብስብ የሆነ የተግባቦት ሂደት ነው:: “ፀሀፊው ሊቆጣጠራቸው የሚገቡ በርካታ ተላውጦዎች (variables) ያሉበት እጅግ ውስብስብ አዕምሮአዊ ተግባር ነው” ይላሉ::

አለም (1995:14) በበኩላቸው የፅህፈትን ክሂል ወስብስብነትና አስቸጋሪነት በሚከተለው መልኩ አቅርበውታል::

> የፅሁፍ ክሂል በቀላሉ የሚጨበጥ ክሂል አይደለም የፅህፈት ክሂል ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው:: በተለይ ደግሞ አስቸጋሪነቱን የሚያጎላው እንደማድመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑ ነው:: በትምህርት ሂደትም ውስብስብና አስቸጋሪ የሚያደርገውም በውስጡ ከሰዋስዋዊ ጉዳዮች በተጨማሪ የግንዛቤን የአስተውሎትንና፣ የማመዛዘንን ችሎታ የመጠየቁ ጉዳይ ነው (1995:14)::

ከፍ ሲል በተለያዩ ምሁራን ከቀረበው ሀሳብ እንደምንረዳው ሀሳብን በፅሁፍ ወረቀት ላይ ማስፈርና አንድ ሊተላለፍ የተፈለገን መልዕክት /የቋንቋ ክሂል/ እውቀት ለአንባቢ በትክክል ለማድረስ ሀሳብን በድምፅ ምልክቶች ብቻ ቀርፆ ወረቀት ላይ ማስፈር እንዳልሆነና ፀሀፊው በርካታ ሊቆጣጠራቸው የሚገቡ ተላውጦዎችን እንዳሉና እነዚህን ውስብስብና አዕምሮአዊ ተግባሮች ለመከወን ከአፃፃፍ ስርዓት ጀምሮ ፀሀፊው ግንዛቤውን አስተውሎቱን የማመዛዘን ብቃቱንና ሰዋስዋዉ እወቀቱን ሁሉ በትምህርት አማካይነት ሊያዳብርና ሊያጎለብት እንደሚገባ ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች በግልፅ እንረዳለን::

በፅህፈት ክሂል አማካይነት የሰው ልጅ የህይወት ገጠመኙን ታሪኩን፣ እወቀቱን . . . ለተከታዩ ትውልድ ያስተላልፋል:: አማረ (1976:10) ፅህፈት በፊደላት አማካይነት ድምፅን ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን በማቀናበር የተለያዩ ሀሳቦችን በወረቀት ላይ ፅፈን የምናቀርብበት ጥበብ ነው:: በተለያዩ የአፃፃፍ ብልሃቶች የተቀነባበሩ ፅሁፎች የሰውን ልጅ የታሪክ ሂደትና የስልጣኔ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር በማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው:: ፅህፈት የሰውን ልጅ ሁለንተናዊ ክንውን በፅሁፍ አማካይነት መዝግቦ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚረዳ ስልት

ነው:: የፅሁፈት ክሂል በባህሪው ውስብስብ አዕምሮአዊ ችሎታን የሚጠይቅ ተግባር ነው:: በመሆኑም ጥንቃቄ የተሞላበት ማሰላሰልን ይጠይቃል ይህንን የክሂሉን የተለዩ ባህሪ Hedge (1988:19) በተመለከተ "ፅሁፈት ሀሳብን በወረቀት ከማስፈር በላይ ውስብስብ ሂደት ነው" ብለዋል::

Widdowson (1983:34-5) ፅሁፈት ተግባቦታዊ ተግባር ነው ስለሆነም የተግባቦትን አጠቃላይ መርህ ይከተላል:: የፀሀፊውንና የአንባቢውን ግንኙነት፣ የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገድ ማለትም የቃላት መረጣ፣ የሀሳብ፣ አደረጃጀት የመልዕክት ግልፅነት . . . ወዘተ. ይመለከታል::

ይህ ተግባቦታዊ ተግባር እንደንግግር ሁሉ ፊት ለፊት /ገፅ ለገፅ/ የሚደረግ ባለመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠይቃል:: ስለዚህም በፀሀፊውና በአንባቢው መካከል ያለው ግንኙነት ችግር እንዳይገጥመው ፀሀፊው አንባቢውን እያሰበ ሀሳቡን የሚያሰፍርበት ከመሆኑም ሌላ ከመልዕክቱ ግልፅነት፣ ቅለትና ክብደት በመነሳት ሀሳቡን ሲያደራጅ፣ ቃላት ሲመርጥ የአንባቢውን ችሎታ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባታል::

ፅሁፈት ግልፅ ብቃት ያለውና ውጤታማ የሆነ የተግባቦታዊ ተግባር ነው (Raimes 1983:6):: ፅሁፈት የአዳዲስ ሀሳቦች ማፍለቂያ መረጃን ወደ እውቀት መለወጫና ግኝቶችን ማሸጋገሪያ መንገድና ብልሃት ነው (Condon and Butter 1997:X)::

የፅሁፈት ክሂል የአዳዲስ ሀሳቦች ማፍለቂያ ከመሆኑም ሌላ የራሱ የሆነ ሂደታዊ ባህርይ ያለው ነው:: ፅሁፈት ሀሳብን ለማዳበር ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ ለማሰብ የሚረዳ አዕምራአዊ ምስል መፍጠርንና ምስሉንም አውጥቶ መፃፍን የሚጠይቅ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል:: በአጠቃላይ ፅሁፈት በምልክቶች የሚወከል ለቋንቋ ስርዓት /ህግ/ የሚገዛ በቦታና በጊዜ የማይገደብ ህያውና አፍላቂ ክሂል በመሆኑ መልዕክትን በማስተላለፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው::

## 2.2 የፅሁፈት ክሂል አስፈላጊነት

የፅሁፈት ክሂል አስፈላጊነት ሰዎችን ከመግባባቱ ወይም የቦታና የጊዜ ውሱንነት ሳይገደብ አገልግሎት መስጠት ከመቻሉ አንፃር ብቻ የሚታይ አይደለም:: White and Arndt (1991) ፅሁፈት ከተግባቦታዊ መሣሪያነቱ ባሻገር የዕውቀት መቅሰሚያ፣ የትምህርት መማሪያ፣ የተለያዩ

ሀሳቦችን ማሰባሰቢያ፣ የዕለት ተዕለት፣ ክስተቶችን መከታተያ . . . የመሳሰሉ ፈርጀ ብዙ አገልግለቶች ያሉት ክሂል ነው::

በተመሳሳይ መልኩ Celce Murcia (1991:241) የፅህፈት ክሂልን አገልግሎትና አስፈላጊነት ሲገልፁ ተማሪዎች በተሻለ መንገድ በቋንቋው ሲገለገሉ እንዲችሉና በተግባቦታዊ ሂደቱም በስፋት እንዲጠቀሙበት የሚያደርግ ክሂል ነው:: አክለውም ሲገልፁ በፅህፈት ክሂል አማካይነት በቋንቋው በብቃት መጠቀምና አቅምን ማጎልበት እንደሚቻል ይጠቁማሉ::

የፅህፈት ክሂል አገልግሎት ከተራ ማግባባት የዘለለ መሆኑን ከፍ ሲል ከቀረቡት ብያኔዎች መገንዘብ እንችላለን:: የፅህፈት ክሂል የዕውቀት መቅሰሚያና የትምህርት መማሪያ ከመሆኑ ባሻገር በቋንቋው በብቃት የመጠቀም አቅምን ለማጎልበት ያግዛል::

Raimes (1983:3) የፅህፈት ክሂልን አስፈላጊነት በተመለከተ ፅህፈት ተማሪዎች በቋንቋ አማካይነት ጥናትና ምርምርን ለማድረግ፤ ሀሳባቸውን አመቺ በሆነ አገላለፅ ለማቅረብ፤ የተለያዩ አዕምሮአዊና አካላዊ ተሳትፎዎችን በማድረግ እንዲማሩ ያበረታታቸዋል::

ከላይ እንደተገለፀው በመማር ሂደት ውስጥ የፅህፈት ክሂል ከፍተኛ ድርሻ አለው:: በማድመጥም ሆነ በማንበብ የተማሩትን ትምህርት ለማጠናከር ፅህፈት አስፈላጊ ነው:: ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት ሂደቶች ሁሉ የተማሩትን መዝግበው ለመያዝና ለመከለስ የፅህፈት ክሂል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው::

Raimes (1983:3) "በፅህፈትና በሀሳብ መካከል ያለው ግንኙነት ፅህፈትን የማንኛውም የቋንቋ ትምህርት ጠቃሚ ጎን እንዲሆን አድርጎታል" ይላሉ::

ከዚሁ አባባል የምንረዳው ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በፅሁፍ የሚግባባው (ሊግባባ የሚችለው) በአዕምሮው ያሰበውን ነገር በፅሁፍ በማስፈር ነው:: በፅሁፍ ከመግባባትና ሀሳብ ለሀሳብ ከመለዋወጥ ባሻገር ፅህፈት የሰዎችን የስነልቡና፣ የሀይማኖት፣ የፍልስፍና የፖለቲካ ዕውቀት፣ በባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶችና ክስተቶች . . . ወዘተ. መዝግቦ ለትውልድ በማቆየት ረገድ አስፈላጊ ነው::

በፅሁፈት ክሂል አስፈላጊነትና አገልግሎት ዙሪያ Raimes: (1983:4), Kelly (1998:ii) የሚከተለውን ሀሳብ ይሰነዝራሉ።

- የአፃፃፍ ስልቶችን ለማለማመድ፣
- የተለያዩ ግኝቶችን ለማሰራጨት፣
- ፈሊጦችን፣ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ለመማር፣
- አዳዲስ ቃላትና ዓረፍተ ነገሮችን ፈትሾ ለማግኘት፣
- ትክክለኛና ተገቢነት ያላቸው ዓረፍተ ነገሮች ለመፃፍ፣
- የቃላት አጠቃቀምንና ምርጫን ለመለማመድ፣
- ተቀባይነት ያለውን ሀሳብ ማፍለቅና ማመንጨትን ለመለማመድ፣
- ቋንቋን ለመማርና በተገቢ መልኩ ለመገልገል፣
- ሀሳብን ስሜትንና ፍላጎትን በፅሁፍ ለመግለፅ . . . ወዘተ. ናቸው።

የፅሁፈትን ክሂል አስፈላጊነት በተመለከተ ከፍ ሲል በዝርዝር ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ፅሁፈት ተገቢ የአፃፃፍ ስልትን፣ ተቀባይነት ያለውን ሀሳብ ማመንጨትና ማፍለቅን፣ የቃላት ምርጫንና አጠቃቀምን፣ አዳዲስ ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን ፈትሾ ማግኘትን . . . ወዘተ ለመማርና በተገቢው ሁኔታ ለመገልገልና ለመጠቀም የፅሁፈት ክሂል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አኳያ ሀሳብን በተገቢው መንገድ በመግለጽ መልዕክትን ለማስተላለፍ የሀሳብ ቅደም ተከተልን ጠብቆ ጽሁፍን ማደራጀት ያስፈልጋል። ለዚህ የሀሳብ ግጥምጥምነት ደግሞ አያያዦችን እንደአስፈላጊነታቸው መጠቀም የግድ ነው።

## 2.3 በንግግርና በፅሁፈት ክሂሎች መካከል ያለ አንድነትና ልዩነት

የፅሁፈት ክሂል ከሌሎች ክሂሎች የሚለይበትና የራሱ የሆነ ባህሪያት አለው። ፅሁፈትና ንግግር ሁለቱም የውጤት ክሂሎች ቢሆኑም አንዳቸው ካንዳቸው የሚለዩበት ባህሪያት አላቸው። የሁለቱን ክሂሎች ልዩነት በተመለከተ Raimes: (1983:4-5), Heaton (1991:3), Byme (1991:3) እና Ur (1996:156-157) የሚከተሉትን ነጥቦች ሰንዝረዋል።

- ፅሁፍ ቋሚ መግባቢያ ሲሆን ንግግር ግን ጊዜያዊ ነው።
- ንግግር ሁለንተናዊ ነው። ፅሁፈትን ግን ካልተማሩት አይገኝም።
- ፅሁፍ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚከተል ሲሆን የንግግር ቋንቋ ግን ኢ-መደበኛ በመሆኑ የዘዬ ልዩነት ይታይበታል።

- ንግግር ለማን እንደሚቀርብ የሚታወቅ ሲሆን በፅሁፈት ጊዜ ግን ፀሀፊው አንባቢውን የግድ ማወቅ አይጠበቅበትም:: ይኸውም ክንውኑ ገጽ ለገጽ ለተወሰኑ ሰዎች የሚቀርብ አይደለምና ነው::
- በንግግር ጊዜ ሀሳቦች ድግግሞሽ የሚበዛባቸው ሲሆን በፅሁፈት ጊዜ የሚቀርቡት ሀሳቦች የተመጠኑና እምቅነት የሚስተዋልባቸወ ናቸው::
- በንግግር ጊዜ የድምፅ ቅምታ፣ ቃና፣ ፍጥነትና የፊት ገፅታን በማቀያየር በሰውነት እንቅስቃሴንና በምልክት የሀሳቡን መልዕክት ለማስረዳት ሲቻል በፅሁፈት ጊዜ የሚተላለፈወን መልዕክት ለማጉላት የተለያዩ ሥርዓተ ነጥቦችንና ምልክቶችን መጠቀም የተለመደ ነው::
- ንግግር ድንገቴነት ሲታይበት፤ ፅሁፈት ግን ጊዜ ተወስዶና ታስቦበት የሚፃፍ ነው:: በንግግር የተላለፈን መልዕክት ለመረዳት የሚወስደው ጊዜ የፅሁፍን መልዕክት አንብቦ ለመረዳት ከሚወስደው ጊዜ አነስተኛ ነው::
- የንግግር ምላሽ የወዲያውነት ባህሪ ሲታይበት የፅሁፍ ምላሽ ግን የሚዘገይ አለያም ምላሽ የማይገኝበት አጋጣሚም ይኖራል::
- ንግግር ቀላል አረፍተ ነገሮችን ሲጠቀም ፅሁፍ ግን ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ይጠቀማል::
- ንግግር በድምፅ ፅሁፍ ደግሞ በሆሄያት ይወከላል::

በፅሁፍ የሚተላለፍ ሀሳብ እንደ ንግግር በቀላሉ የሚከናወን አይደለም:: ፅሁፍ የቋንቋውን ህግ ጠብቆ የተደራጀ የአፃፃፍ ስርዓትን ይከተላል:: በመሆኑም የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን፣ የቃላት መረጣና የዓረፍተ ነገር አስካክን፣ የአንቀፅ አደረጃጀትና አወቃቀርን . . . ወዘተ. ማወቅን ይጠይቃል::

Cook (1989:61) በበኩላቸው በፅሁፈት ጊዜ በፀሀፊውና በአንባቢው መካከል ምንም አይነት የገፅ ለገፅ ግንኙነት ባለመኖሩ ፅሁፈት ከኢ-ተራክቧዊ ዲስኩር ውስጥ እንደሚመደብ ያስረዳሉ::

በፅሁፍ ውስጥ ያሉ ዓረፍተ ነገሮች እርስ በርስ በሚፈጥሩት ዝምድናና ግንኙነት መሠረት አንባቢው ሊተላለፍለት የተፈለገውን መልዕክት በቀላሉ ሊገነዘብና ሊረዳ ይችላል (Brown, 1994:235):: ከዚህ አኳያ በዓረፍተ ነገሮች መካከል ያለወ ዝምድናና ትስስር ለትርጉም አዘል

መልዕክት መፌጠር ወሳኝ ነው:: በመሆኑም ፀሀፊው አንባቢዎቹን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፅንሰ ሀሳቦቹን ያሰፍራል:: በዲስኩሩም ትዕዛዝ፣ ጥያቄ፣ ሂስ፣ ይቅርታ መጠየቅ እና ሌሎችም ሊከናወኑ ይችላሉ::

Kelly እና Deborah (1998:65) በበኩላቸው ፀሀፊው ሀሳቡን የሚያደራጅበት መንገድ በአንባቢው ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር በመጠቆም ሶስት የተለመዱና የተዘወተሩ ሀሳብን የማደራጃ ዘዴዎች መኖራቸውን ይገልፃሉ:: እነርሱም በጊዜ ቅደም ተከተል፣ ከሚገኝበት ቦታ እና ከሚሰጠው ወይም ካለው ጠቀሜታ አኳያ በአንድ አንቀፅ ውስጥ የሚገኙትን ዓረፍተ ነገሮች ማደራጀት እንደሚታይ ያስረዳሉ:: አክለውም አንድ ፅሁፍ ተያያዥነትን እንዲጠበቅ የሚያደርጉት መሸጋገሪያ ቃላት እና የሀሳብ ወይም የዓረፍተ ነገር አደጃጀት መሆናቸውን ይገልፃሉ::

ፀሀፊው ለተደራሲው ወይም ለአንባቢው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ሊያቀርብለት ይገባል:: ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው ሀሳብን በጊዜ ቅደም ተከተል ተያያዥነት ባለው መልኩ የሀሳብ ፍሰቱ ሳይደነቃቀፍ ሲቀርብ መሆኑን ከፍ ሲል ከቀረቡት ብያኔዎች ለመረዳት ይቻላል::

በአጠቃላይ እንደንግግር ክሂል በፅሁፌት ክሂል ጊዜ በፀሀፊውና በአንባቢው መካከል የገፅ ለገፅ ግንኙነት ካለመኖሩም በላይ ፀሀፊዎች ከፅሁፎቻቸው አላማና ግብ አኳያ የአንባቢዎቻቸውን ዳራዊ እውቀትና ችሎታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሥራዎቻቸውን ሊያከናውኑ እንደሚገባ የተለያዩ ምሁራን ያስገነዝባሉ:: በመሆኑም በንግግርም ሆነ በጽህፈት ጊዜ መልዕክትን በግልጽና በማያሻማ መንገድ ማስተላለፍ ይገባል:: ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ ለአድማጩ ወይም ለአንባቢው ማድረስ ሲቻል ነው:: በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ጊዜ ተናጋሪው ወይም ጸሀፊው ለመልዕክቱ በትክክል መድረስ የየበኩላቸውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል::

## 2.4 የፅህፈት ክሂል የትኩረት አቅጣጫዎች

በመርህ ደረጃ የፅህፈት ክሂል ጠቀሜታ ሀሳብን ለመግለፅና ለተደራሲው/ለአንባቢው/ መልዕክትን ለማቀበል ነው:: ስለዚህ ሃሳብ ወይም መልዕክት ለፅህፈት በጣም አስፈላጊ ነው:: በሌላ በኩል አንድ ፀሀፊ ለእጅ ፅህፈቱ፣ ትክክለኛነት ለስርዓተ ነጥብ እንዲሁም ተቀባይነት ላለው ሰዋስውና ጥንቃቄ ለተሞላበት የቃላት መረጣ ትኩረት መስጠት አለበት:: ምክንያቱም ከንግግር በበለጠ

በፅሁፍ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የመደበኛ ቋንቋ አጠቃቀም ይስተዋላልና ጥንቃቄ የተሞላባቸው የአረፍተ ነገሮች ግንባታ፣ ግልፅና የተለያዩ ቃላት አጠቃቀም፣ የገለፃዎች ትክክለኛነት፣ በአጠቃላይ የፅህፈት ዘገምተኛ ሂደት /ጊዜ ተወስዶ የሚከወን/ በራሱ ፀሀፊው ጊዜውንና ትኩረቱን ለመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲሰጥ ያደርገዋል (Ur 1996:163)::

ፅህፈትን ስናስተምር እንቅፋት ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ በይዘትና በቅርፅ መካከል ያለውን ተገቢ ሚዛን መጠበቅ አለመቻል ነው:: በርግጥ የምናስተምርበት ሁኔታ ወይም አውድ ሚዛኑን ለመወሰን ወይም ለመጠበቅ ያገለግላል:: ነገር ግን ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከረው የፅህፈት ክሂል ትምህርት ትኩረት ይዘትም ቅርፅም እንደሆነ ግልፅ ነው:: ከዚህ አኳያ በፅህፈት ትምህርት ወቅት ትኩረት ሰጥተን የምንፅፋቸው ነገሮች የተለያዩ ናቸው::

አስቴር **(1998:13)** Raimes (1983:6)ን ጠቅሰው የፅህፈት ክሂል የትኩረት አቅጣጫዎችን በሚከተለው መልኩ አቅርበውታል::




አስቴር **(1998:13)**

በዕህፈት ክፍለ ትምህርት ወቅት ተማሪዎች የሚማሩት ምንድን ነው? ዕፈትን ስናስተምር ዓረፍተ ነገሮች፣ አንቀፅና ድርሰት ዋንኞቹ ተተኳሪዎች መሆናቸው አይቀርም ዋና ዓላማው ተማሪዎች ሃሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸውን ማዳበር በመሆኑ በዓረፍተ ነገር በአንቀፅና በድርሰት አፃፃፍ ላይ ማተኮራችን የግድ ነው ሆኖም የትምህርቱ ይዘት የሚወሰነው በተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ፣ የክፍል ደረጃ . . . ወዘተ. ነው::

በፅህፈት ጊዜ ትኩረት ሰጥተን ተግባር ላይ ልናወላቸው የሚገቡ ዝርዝር ነጥቦች ከላይ በግልፅ ቀርበዋል:: የፅህፈት ክሂል የትኩረት ነጥቦች ሚዛናዊነትን የጠበቁ ሀሳቦችን በማፍለቅ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት ጠብቆና ቃላትን በዓረፍተ ነገሮች አሳክቶ ሀሳብን የማቅረብ ችሎታን ይጠይቃል:: ፀሀፊው ተደራሲውን/አንባቢውን/ ከግምት በማስገባት የቋንቋውን ስርዓት ጠብቆ ግልፅና ወጥነት በሆነ ሁኔታ መፃፍ አለበት:: ይህም ፀሀፊውን ከአደረጃጀት ከዘይቤ፣ አጠቃቀም፣ ከይዘት፣ ከቅርፅ አጠባበቅ . . . ወዘተ አኳያ አስቦበትና ትኩረት ሰጥቶት እንዲፅፍ ይጠበቅበታል::

## 2.5 የፅህፈት ክሂልን ማስተማር

በድሉ (1996) "ፅህፈት መማርን ይፈጥራል" ይላሉ ተማሪዎች በሚፅፉበት ጊዜ ሀሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለፅ ይፈልጋሉ:: በፅሁፍ የሚያስተላለፉትን መልዕክት ደጋግመው ያስባሉ፤ ይመረምራሉ፤ አግረመንገዳቸውንም ስለድርጊት ቃላት ግንኙነት ይመረምራሉ::

የፅህፈት ክሂል ትምህርትን ለማስተማር ትኩረት የሚሰጣቸው ነጥቦች አሉ:: ክሂሉን ለማስተማር በዋናነት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነጥቦች መኖራቸውን የተለያዩ ምሁራን ይገልፃሉ:: ከተለያዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ስልቶችና የትምህርት አላማዎች አኳያ የፅህፈት ትምህርት የትኩረት ነጥቦችን በተመለከተ Raimes (1983:6) የሚከተለውን ያቀርባሉ:: በፅህፈት ጊዜ የሀሳብ ተግባቦትን ግልፅ፣ ርዕቱና ወጤታማ ለማድረግ ከሚረዱት የፅሁፍ አካላት ውስጥ የሚፃፍበትን በሀሳብ ማፍለቅ፣ በምክንያት ማደራጀት፣ በገጠመኝና በምልከታ የተገኘውን መረጃ በመልክ በመልኩ ማደራጀትና ማዘጋጀት . . . ወዘተ ናቸው::

Heaton (1991:135) በበኩላቸው ፅህፈትን በመማር የተለያዩ ችሎታዎች ሊዳብሩ መቻላቸውን ገልፀው የሚከተሉትን ነጥቦች ይሰነዝራሉ::

- ተገቢ የሆነ የመፃፍ ችሎታ ይዳብራል፣

- የስርዓተ አፃፃፍ ደንቦችን ተገንዝቦ በአገልግሎት ላይ የማዋል ችሎታ፣
- የሀሳብን የማመንጨት፣ የመምረጥና አስፋፍቶ የመፃፍ ችሎታ፣
- መደበኛ ቋንቋን የመጠቀም ችሎታ፣
- የአቀራረብ ሚዛናዊነትና የሁነቶችንና የድርጊቶችን ክትትሎሽና ቅደም ተከተል ለይቶ ለማቅረብ፣
- አንባቢንና አላማን ወስኖ የማቅረብ ችሎታ . . . ወዘተ. የመሳሰለትን ለማግኘት የፅሁፈት ክሂልን መማር ተገቢ እንደሆነ ያብራራሉ::

ፅሁፈትን መማር ሚዛናዊነትን የጠበቁ ሀሳቦችን በማፍለቅ፤ ስዋስዋዊ ስርዓትን በመጠበቅ የድርጊት ቃላትን ለይቶ ሀሳብን በተዋጣ ቅደም ተከተል ለማደራጀትና ለማቀናበር ይረዳል:: ሆኖም ክሂሉ በልምምድ እየደረጀ የሚሄድ በመሆኑ ሰፊ ልምምድ ማድረግን ይጠይቃል::

Celce Murcia (1991) ተማሪዎች ሀሳባቸውን ለመግለፅ ተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም (በቃላት ምርጫ፣ በዓረፍተ ነገር አሰካክ . . . ወዘተ) ተጠቅመው መልዕክት ማስተላለፍ የሚችሉበትን የተግባቦት ስርዓት እንዲፈጥሩ ፅሁፈትን ማስተማር ያስፈልጋል:: የፅሁፈት ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበትና መምህራን ደስ ያላቸውን ርዕስ ለተማሪዎቻቸው በመስጠት ፅሁፈትን ማስተማር እንደሌለባቸው በድሉ (1996) ይገልፃሉ::

ከላይ በተለያዩ ምሁራን እንደገለፀው ተማሪዎች ፅሁፈትን በትኩረትና በንቃት እንዲሁም በሙሉ ስሜት እንዲማሩት የተማሪዎች ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ አለበት:: በዚህ ረገድ የፅሁፈት ትምህርት የተወሰነ ክፍለ ጊዜ ትምህርት ብቻ ባመሆኑ ተማሪው በፍላጎትና በስሜት ሊያከናውነው እንዲችል ከርዕስ አመራረጥ ጀምሮ ባለው ትርፍ ጊዜ ሁሉ ተጠቅሞ እንዲፅፍና እንዲለማመድ እድል መስጠት ተገቢ ነው::

## 2.6 የአያያዥ ቃላት ምንነት

አያያዦች /ዲስኩር አመልካቶች/ ቀለል ባለ አገላለፅ ቃላትን ከቃላት፣ ሀረግን ከሀረግ፣ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር፣ አንቀፅን ከአንቀፅ የሚያያይዙ ተብለው የሚታወቁ ቢሆንም ተግባራቸው ግን ከዚያ ያለፈ ነው:: እነዚህ አመልካቶች ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው በወሁድ አሀዱ ውስጥ ባካተታቸው ዓረፍተ ነገሮች አማካይነት ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት እንዲያስተላልፍ ከመርዳታቸውም ሌላ ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው በሚያከናውነው ዲስኩር ውስጥ ምን እያከናወነ እንዳለ የሚያሳዩም ናቸው:: ለምሳሌ ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ለማነፃፀር፣ ምሳሌ

ለመስጠት፣ ለማወዳደር፣ ለማብራራት፣ ለመለየት . . . ወዘተ. እንደፈለገ ያመለክታሉ (Nunan 1993)::

አንድ ንግግር ወይም ፅሁፍ ተፈላጊውን መልዕክት ማስተላለፍ ይችል ዘንድ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ወይም መስተፃምራን አስፈላጊዎች ናቸው:: እነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በዲስኩር ውስጥ የተለያዩ ወሰኖችን /እርከኖችን/ በማበጀት ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ሊያስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት አጉልተውና ግልፅ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው (Crew, 1990:322)::

አያያገሮች በዲስኩር ውስጥ ቁልፍ ጉዳዮች ሲሆኑ ተናጋሪው ወይም ፀሀፊው ንግግሩን ወይም ፅሁፉን በተገቢው መልኩ እንዲያስተላለፍ የሚረዱ መሳሪያዎች ናቸው:: አያያገሮች በአንድ ውሁድ አሀድ ውስጥ ሀሳብን የማደራጀትና የማዋቀር ስራ ይኑራቸው እንጂ በፅሁፉ ወይም በንግግሩ ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ /ተናጠላዊ/ ፍች ይዘው አይገኙም:: በመሆኑም የአንድን ዲስኩር የተለያዩ ተናጠላዊ ሀሳቦችና ክፍሎችን በማጣመር አንድ ጥምረት ያለው ውሁድ አሀድ እንደሆን ይረዳሉ:: እነዚህ የአንድን ውሁድ አሀድን ተግባር በማሳካት በኩል ከፍተኛ ሚና ያላቸው አካላት በውሁድ አሀዱ ውስጥ ትስስርን ወይም ግንኙነትን ስለሚፈጥሩ አድማጩ ወይም አንባቢው ያለምንም ችግር ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሊገነዘብ ይችላል (Bolitho እና Tomlinson:1980)::

አያያገሮች /ዲስኩር አመልካቶች/ ውሁድ አሀድን የሚያደራጁ ቃላት ወይም አጫጭር ቃላዊ ሀረጋት ናቸው:: የተናጋሪውን ወይም የፀሀፊውን ቀዳሚ ንግግር ወይም የፅሁፍ መልዕክት ከተከታዮ ንግግር ወይም የፅሁፍ መልዕክት ጋር አገናኝተው ወይም አቀናጅተው ማሳዬት ዋና ተግባራቸው ነው:: በመሆኑም በውሁድ አሀዱ ውስጥ በተጠቀሱ የተለያዩ ሀሳቦች መካከል ግንኙነት በመፍጠር /በመመስረት/ ግጥምጥምነትን ይፈጥራሉ (Parrot, 2002:29)::

McCarthy (1991:51) በበኩላቸው በዲስኩር ውስጥ ሲገቡ የራሳቸውን ቃላዊ ትርጉም/ፍች/ ማሳዬትን አላማቸው አድርገው አይገቡም:: ስለዚህ የአያያገሮች ተግባር በዲስኩር ውስጥ ከአንድ ውሁድ አሀድ ስኬት ጋር እንጂ ብቻውን መታዬት ያለባቸውም::

Chapman (1983:86) በተመሳሳይ ሁኔታ ሲገልፁ አመልካቾች በራሳቸው የሚያስተላልፉት የተወሰነ ትርጉም ቢኖራቸውም በዲስኩር ውስጥ ሲገቡ ግን ዋናው ተግባራቸው የውሁድ

አህዱን የተለያዩ ክፍሎች ማያያዝና ማገናኘት ነው። በዚህ መሠረት አያያዦች አድማጭ ወይም አንባቢ ከሚያደምጠው ወይም ከሚያነበው ዲስኩር ትርጉም እንዲያገኝ የሚያግዙ ናቸው። በተጨማሪም በቀዳሚውና በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መካከል ትስስርና ግንኙነት በመፍጠር አንዱ ለሌላው ምክንያት ወይም ውጤት እንደሆነ አድማጩ ወይም አንባቢው እንዲገነዘብ ያደርጋሉ። አያያዥ ቃላትና ሐረጋት በጽሁፍ ወይም በንግግር ውስጥ ሲገቡ ያላቸውን ጠቀሜታ በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ አገላለጽ /አቀራረብ/ ለማሳየት ሞክረዋል። አድማጩ ወይም አንባቢው ከንግግሩም ሆነ ከጽሁፉ መልዕክትን በትክክል እንዲረዳና እንዲገነዘብ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ /እገዛ/ አላቸው። አያያዥ ቃላትና ሐረጋት የጸሀፊውን ወይም የተናጋሪውን ሀሳብ ከጊዜ፣ ከድርጊት ክትትሎሽ፣ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ሀሳብን ለመግለጽ፣ ለማጠቃለል ወዘተ. መርዳታቸውን መገንዘብ እንችላለን።

የአያያዥ ቃላትን /የዲስኩር አመልካቾችን/ ምንነት በተመለከተ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን ብያኔ መሠረት አያያዦች ከራሳቸው ተናጠላዊ ፍች/ትርጉም/ ይልቅ በንግግር ወይም በፅሁፍ ሊተላለፍ የተፈለገውን የውሁድ አህዱን ግጥምጥምነት በማሳካት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። በአንድ ውሁድ አሀድ ውስጥ ያለ ሀሳብ አንድነቱን ጠብቆ መልዕክቱ ለአንባቢው ወይም ለአድማጩ እንዲደርስ አያያዦች ሃሳብን በማደራጀትና በማዋቀር ረገድ ድርሻ እንዳላቸው ከብያኔዎቹ መገንዘብ ይቻላል።

## 2.7 የአያያዥ ቃላት ተግባርና ጠቀሜታ

አያያዥ ቃላት/ዲስኩር አመልካቾች/ ከተለያዩ የንግግር ክፍሎች ውስጥ መገኘታቸውን ቀደም ብለን ጠቅሰናል። የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አይነታቸውም ሆነ ቁጥራቸው ከመብዛቱ የተነሳ ተግባርና ጠቀሜታቸውን በቀላሉ ለመግለፅ አስቸጋሪ እንደሆነ Parrot (2002:29) ይገልፃሉ። እኒሁ ምሁር አያያዦች ካሏቸው በርካታ ተግባራት መካከል የተወሰኑትን ለማሳየት ሞክረዋል።

- ተጠይቃዊ ግንኙነትንና ቅደም ተከተላዊ አካሄድን ያረጋግጣሉ። ይህም ማለት ለመናገር ወይም ለመፃፍ በምንፈልግበት ጊዜ የምናወጣቸውን የተለያዩ ብጥስጣሽ ሀሳቦች አንድ ላይ በማገናኘት በቅደም ተከተል በማስተቀመጥ የፈለግነውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ያስችሉናል።

- ተግባቦትን ለመቆጣጠር ያስችላሉ፡፡ በተግባቦት ሂደት አድማጭ ወይም አንባቢ እና ተናጋሪ ወይም ፀሀፊ አለ፡፡ መልዕክት አስተላለፊው ሀሳቡን በአይነት በአይነት እየከፋፈለ ለማስተላለፍና አድማጩም የተለያዩ ሀሳቦችን ማድመጥ እንዲችልና የሚና ለውጥ ማለትም አድማጭ የነበረው ተናጋሪ፣ ተናጋሪ የነበረው አድማጭ የሚሆንበትን እድል እንዲያገኝ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ናቸው፡፡
- ተናጋሪው (ፀሀፊው) እና አድማጩ (አንባቢው) መቼ መናገር፣ መቼ ማድመጥ፣ መቼ ሀሳቡን መለዋወጥ . . . ወዘተ እንደሚገባቸው የሚያመላክቱ ናቸው፡፡
- ተናጋሪው (ፀሀፊው) በተግባቦታዊ ሂደቱ ወቅት ያለውን ዝንባሌ /ፍላጎት/ መግለፅ ያስችላሉ፡፡ መቆጣቱን፣ ሃሳቡ ያልጣመው መሆኑን፤ ማስተላለፍ የፈለገውን ነገር በአፅንኦት /አስረግጦ/ መንገር መፈለጉን . . . ወዘተ ያሳያሉ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን ዋና ተግባር ሲገልፁ የአንድን ሀሳብ የሂደት እርከንና የተለያዩ ክፍሎች አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዘና የተዛመደ መሆኑን ለአንባቢ በቅድሚ ማመልከት ነው፡፡ እነዚህ ቃላትና ሀረጎች ከፀሀፊው አቋም አንፃር ሲታዩ የተለያዩ የፀሀፊውን የስሜት አገላለፆች ማመላከቻዎች በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ መፈንጠቅ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

McCarthy (1991:69) አያያዦች /ዲስኩር አመልካቾች/ አንድ ውሁድ አሀድ መናገር ያለበትን አውዳዊ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ያደርጋሉ፡፡ እየተናገረ ወይም እየተፃፈ ያለን ሀሳብ ለመቃወም፣ አማራጭ ለማቅረብ፣ ለማጠቃለል . . . ወዘተ ያገለግላሉ በማለት ጠቀሜታቸውን ይገልፃሉ፡፡ የመስኩ ምሁራን በአያያዥ ቃላት ተግባርና ጠቀሜታ ዙሪያ የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ከአያያዦች ብዛት አኳያ ተግባራቸው የበዛ ቢሆንም በውህድ አሀድ ውስጥ በገቡ ጊዜ የሚያስገኙት ፍችና ትርጉም ሌላ የውሁድ አሀዱን የሀሳብ ፍሰት አንድነትና ግጥምጥምነት የሚያስጠብቁ መሆኑ ሁሉም ይስማሙበታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ዳኛቸው (1977:127) በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥም ሆነ ከዓረፍተ ነገር ወደ ዓረፍተ ነገር ለመሸጋገሪያነት የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላት መግባት ያለባቸው ዓረፍተ ነገሮቹ ያለ እነርሱ ተጨማሪነት ዝምድናቸው በግልፅ የማይታይ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ አለዚያ ቃላቱ መደርቻ ከመሆናቸውም አልፎ አንባቢን ያሰለቻሉ ይላሉ፡፡ ይህንኑ በመደገፍ አማረ (1976:130) ሀሳቡን ይጋሩታል፡፡ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋት በቁጥር ብዛት ያላቸው ቢሆንም እንኳን

በዓረፍተ ነገሮችም ሆነ በአንቀፆች መካከል ተገቢውን የቁርኝት ተግባር አጥጋቢ በሆነ መንገድ አሟልተው ሲገኙ ይችሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ መደበኞቹ የሽግግር ቃላትና ሀረጎች ሀሳብን ከአንድ ዓረፍተ ነገር ወደ ሌላው ዓረፍተ ነገር ወይም ከአንድ አንቀፅ ወደ ሌላው አንቀፅ በማሸጋገር ረገድ በቂ የማይሆኑበት ምክንያት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ በብዛት ተደጋግመው በአገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ ከብዛታቸውና ከመደጋገማቸው የተነሳ አንባቢን ያሰለቻሉ። የአንድ ፀሀፊ አይነተኛ ተግባር ደግሞ በዓረፍተ ነገሮች/በአንቀፆች/ መካከል ተገቢ አያያዦችን በመጠቀም የሽግግር ድልድይ እንዲኖር ማድረግ ነው።

ከላይ የአያያዥ ቃላትን ጠቀሜታና ተግባር በሰፊው አይተናል። በመሆኑም አያያዥ ቃላትን ስንጠቀም ተገቢና አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ብቻ እንደሆነ ግልፅ ነው። አያያዦች ያለቦታቸው ሲገቡ መልዕክቱ ለአንባቢው በትክክል እንዳይደርስ እንቅፋት ይሆናሉ።

## 2.8 የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ

የአያያዥ ቃላትን /የዲስኩር አመልካቾችን/ አመዳደብና አከፋፈል በተመለከተ ምሁራንን የሚያስማማ አንድ ወጥ አመዳደብና አከፋፈል ያለ አይመስልም። ይህን ጉዳይ አስመልክተው Parrot (2002:29) ሲገልፁ የአያያዦች /የዲስኩር አመልካቾች/ አይነት መብዛት፣ በአንድ ውሁድ አሀድ ውስጥ ተመሳሳይ የሆኑ አያያዦች ወይም የዲስኩር አመልካቾች በተለያዩ አገልግሎትና ተግባር ላይ መዋል፤ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ አመልካቾችን ካላቸው ብዛትና ልዩነት የተነሳ ዘርዝሮና ለይቶ ለማሳየት አለመቻል እንዲሁም በአከፋፈሉና አመዳደቡ ረገድ በምሁራን ዘንድ አንድ ወጥ አተያይ /አመለካከት/ አለመኖር አስቸጋሪ አድርጎታል። ይህ ወጥ ያልሆነ አከፋፈልና አመዳደብ እንዳለ ሆኖ የመስኩ ምሁራን በተለያዩ መስፈርት አያያዦችን /ዲስኩር አመልካቾችን/ መድበዋቸዋል።

ከነዚህም ውስጥ Halliday and Hasan (1976) አያያዦችን /ዲስኩር/ አመልካቾችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መድበዋቸዋል። እነርሱም

ሀ. **አካይ (Additive)፡-** እነዚህ ክፍሎች የ(እና) ወይም የ(and) ወገን ተብለው የሚመደቡ ናቸው። በዚህ ክፍል ሊካተቱ የሚችሉ አመልካቾች እንደ (እና ከዚህ በተጨማሪ፣ ከዚህ ሌላ፣ እንዲሁም፣ በተጨማሪ፣ በሌላ መልኩ፣ በሌላ በኩል፣ በነገራችን ላይ፣ በሌላ አገላለፅ . . . ወዘተ) የመሳሰሉት ናቸው።

ለ. **ልየታዊ (Adversative)፡-** በዚህ ክፍል የሚታወቁት ዲስኩር አመልካቾች የ"ነገር ግን" የ("But") ወገኖች ተብለው ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ክፍል ከሚካተቱት አመልካቾች መካከል (ይሁን እንጂ፣ ነገር ግን፣ ይህም ቢሆን፣ ቢሆንም፣ በተቃራኒው፣ በየትኛውም ሁኔታ /መንገድ/. . . ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

ሐ. **ሰበባዊ (Causal)፡-** እነዚህ አመልካቾች ደግሞ የስለዚህ "So" ወገን ቡድኖች በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡ (ስለሆነም፣ ስለዚህ፣ በዚህም፣ ለዚህም፣ በዚህ ምክንያት . . . ወዘተ) የመሳሰሉት በዚህ ክፍል ይመደባሉ፡፡ (አባሪ 6 ይመለከቷል)

መ. **ጊዜ ጠቀስ (Temporal)፡-** በዚህ ክፍል የሚመደቡት ደግሞ የ"ከዚህ በኋላ" (after that) ወገኖች በመባል ይታወቃሉ (ከዚህ በኋላ፣ ከዚህ ቀጥሎ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ በኋላ፣ በመጨረሻ፣ ለአንድ ጊዜ . . . ወዘተ) የመሳሰሉት እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ በሚል ሲከፍላቸውና ሲመድቧቸው ከዚሁ አመዳደብና አከፋፈል ጋር በተቀራረበ መልኩ፡፡

Nunan (1993:26-27) ዲስኩር አመልካቾች /መስተፃምራን/ በአራት አብይ ክፍሎች መክፈል እንደሚቻል ይጠቁማሉ፡፡ መስተፃምራን አካይ ልየታዊ ሰበባዊና ጊዜ ጠቀስ በማለት ይከፈላሉ፡፡ ይህም ክፍ ሲል እንደተጠቀሰው ከ Halliday and Hasan (1976) ስራ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

Trimble (1985:52-54) በበኩላቸው የዲስኩር አመልካቾች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ተፈጥሮአዊና ተጠይቃዊ ቅደም ተከተል ያገናዘበ ክፍፍል አድርገዋል፡፡ እንደ Trimble (1985:52-54) አገላለፅ ተዘውታሪ ተፈጥሮአዊ ሂደቶች የሚባሉ የጊዜ፣ የቦታ፣ የምክንያትና ውጤት ቅደም ተከተሎች ሲሆኑ ተጠየቃዊ (Logical patterns) ቅደም ተከተሎች ደግሞ በተናጋሪው ወይም በፀሀፊው ሆን ተብሎ የሚመረጥ ሲሆን ለአድማጩ ወይም ለአንባቢው ሊተላለፍ የተፈለገውን መረጃ ቅንጅት በግልፅ ማመልከት ነው፡፡ ይህ ቅደም ተከተልም የምክንያትና የውጤት፣ የጠቀሜታ፣ የንፅፅርና ውድድር ተጠየቅን በምሳሌ ማስረዳት . . . ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ (ክፍፍሉን በአባሪ 7 ይመለከቷል)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Cook (1989:61) በሀረጎችና በዓረፍተ ነገሮች መካከል የሚገኝ ማንኛውንም ተዛምዶ በግልፅ የማስቀመጥን ስራ የሚሰሩ አካላት አያያዦች እንደሆኑና እነዚህ አያያዦች በነበረ ነገር ላይ ሌላ መረጃ የሚጨምሩ፣ ምሳሌ የሚሰጡ፣ አዲሱን ነገር ከቀደመው ጋር

የሚያነባዕሩ፣ ምክንያትና ውጤትን የሚጠቁሙ ወይም ማጠቃለያ የሚሰጡ ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ዝርዝራቸውን አስፍረዋል።

ከዚህ በላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ የዬበኩላቸውን ክፍፍል አቅርበዋል። ከቀረቡት አከፋፈሎች እንደምንረዳው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በተለያዬ ምድብ ስር ሊካተቱ እንደሚችሉና በአመዳደቡም ሆነ በአከፋፈሉ ረገድ ምሁራን ወጥ የሆነ አከፋፈል እንደሌላቸው አስተውለናል። ይህም ልዩነት ምሁራን እንደተነሱበት የጥናት ትኩረት አቅጣጫ መለያዬት የዲስኩር አመልካቾችን አተናተንና የምድብ አከፋፈል አንድ አለመሆን ጌታቸው (1987፣28) McCarthy (1991:51)ን ጠቅሰው ልዩነቱን አስፍረዋል።

ለዚህ ጥናት ትንተና ይበልጥ አመቺ ሆኖ የተገኘው የNuttal (1982) ስራ ነው። ይህንንም በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን።

የአያያዥ ቃላትን እና ሐረጋትን በዓይነት በዓይነት ለመክፈል የተለያዩ ምሁራን ጥረት ማድረጋቸው ቀደም ሲል ተገልጿዋል። ከዚህ መካከል ጌታቸው (1987፣105)፣ አማረ (1976፣126-127)፣ Halliday and Hasan (1976)፣ Nuttal (1982:96-98) ይገኙባቸዋል። አማረ (1976:126-127) አያያዥ ቃላትን እና ሐረጎችን በርከት ባሉ ክፍሎች ከመክፈላቸው በተጨማሪ አንዱ የሌላውን ቦታ የሚተካበት ሁኔታ ስለመኖሩ ያነሱት ጉዳይ ስለሌለ የአከፋፈሉን አስተማማኝነት ዝቅ ሊያደርገው ችሏል። ቀደም ሲል እንደመለከት ነው Halliday and Hasan (1976) ደግሞ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል በሥራቸው ንኡሳን ክፍሎች እንደሚገኙ ይገልፃሉ። ሆኖም በNuttal (1982) የተካተተውን የዕሁፍ አደረጃጀት (Discourse organization) የሚያመለክተውን ክፍል ካለማካተታቸውም ሌላ አካይ (Addative)፣ ልየታ(Adversative) እና ሰበባዊ (Causal) የተባሉት በፀሐፊው አተያይ (writer's point of view) አመልካቾች ዋና ክፍል ሥር የተመደቡትን ሦስት ንኡሳን ክፍሎች ራሳቸውን አስችለው አበይት ክፍሎች አድርገው ስለሚከፍሏቸው ለNuttal (1982) አከፋፈል ተመራጭነት የቅድሚያ ቦታ ይሰጣሉ። ይህ ማለት ግን ከሚጠናው ጥናት ባህርይ አኳያ የHalliday እና Hasan (1976) የጌታቸው (1987፣105) አከፋፈልና አመዳደብ ተመራጭ አይሆኑም ማለት እንዳለሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

በዚህ መሠረት Nuttal (1982:96-98) አያያዥ ቃላትን እና ሐረጋትን ከአንባቢ እይታ አኳያ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከፈሉ የገለፁ ሲሆን እነዚህም

ሀ. የፅሑፍ ሁነት (events) ሲዘገብ ቅደም ተከተሉን የሚያመለክቱ (ጊዜ ጠቀስ) ቃላት እና ሐረጋት::

ለ. የፀሐፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት::

ሐ. ፀሐፊው በፅሁፉ ስላሰፈረው መረጃ ወይም ሐሳብ ወዘተ. ያለውን አተያይ/አመለካከት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ናቸው:: (በአባሪ 8 ይመለከቷል)

## ሀ. የፅሑፍ ሁኔት (events) ሲዘገብ ቅደም ተከተሉን የሚያመለክቱ አያያዥ ቃለት እና ሐረጋት::

እነዚህ ዓይነት አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት እንደ (መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ በአንድ ጊዜ፣... ) የመሳሰሉት ሲሆኑ "መቼ?" የሚለውን ጥያቄ የሚመልሱ ናቸው:: እነዚህ ዓይነት አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ጊዜውን በ1981፣ ዕለተ ሐሙስ ወዘተ. በማለት ወስነው ሊያቀርቡም ይችላሉ:: አልያም በተለያዩ ጊዜ አመልካች ምዕላዶች፣ ቃላት እና ሐረጋት አማካይነት ሊያመለክቱ ይችላሉ::

## ለ. የፀሐፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልትን የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት

የዚህ ዓይነት አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ለምሳሌ፣ ለማጠቃለል ያህል፤ በአጭሩ እና የመሳሰሉ ሲሆኑ በምድብ ሀ እንደተጠቀሱት ዓይነቶች የዘገባው አካል ሳይሆኑ፣ ፀሐፊው አንባቢው የዐረፍተ ነገሩን አገልግሎት (function) እንዲረዳ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች ሲሆኑ፣ ከፅሑፍ ዘገባው አካል ውጭ የሆኑ ናቸው:: እነዚህ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት በአንድ ምድብ ሥር ይካተቱ እንጂ ካላቸው አገልግሎት አኳያ ግን በተለያዩ ንኡሳን ምድቦች ሊከፈሉ የሚችሉ ናቸው፤ እነዚህም:-

1. ክትትሎሽ አመልካች(Sequencing) - በቅድሚያ፣ ቀጥሎ፣ በአጠቃላይ፤. . .ወዘተ
2. ድጋሚ መግለፅ (Re-expressing) - በሌላ አነጋገር፣ ይህም ማለት፣ . . .ወዘተ
3. በዝርዝር መግለፅ (Specifying) - እነዚህም፣ በስም ለመጥቀስ፣ . . .ወዘተ
4. ለይቶ ማመልከት (Referring) - ይህን በሚመለከት፣ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከረው፣ ከዚህ በተለየ መንገድ . . . ወዘተ

5. ድጋሚ መጥቀስ (resuming) - ቀደም ሲል ወደተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ፣ በድጋሚ ለማስታወስ፣ . . .ወዘተ

6. ምሳሌ መስጠት (exemplifying) - ለምሳሌ፣ ይህንን በይበልጥ ለመግለፅ፣ . . .ወዘተ

7. ማጠቃለል (Summarizing) - ለማጠቃላል፣ በአጭሩ፣ . . .ወዘተ

8. ትኩረት መስጠት (Focusing) - በዚህ ምዕራፍ ለማንሳት የሚሞከረው፣ ቀጥሎ የምንሸጋገረው፣ . . .ወዘተ

እዚህ ላይ ግንዛቤ የሚያስፈልገው ነጥብ ቢኖር የፀሐፊውን የዕሁፍ አደረጃጀት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጎች በምድብ ሀ ከተጠቀሱት አያያገሮች መካከል ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸውን ነው:: ዋናው ጉዳይ የፀሐፊው የፅሑፍ አደረጃጀት ስልትን ለማመልከት ሲባል ግልጋሎት ላይ የዋሉ መሆናቸውን ነው::

ለምሳሌ:- መጀመሪያ ዶሮዋን ገነጣጠለቻት (ምድብ ሀ ምሳሌ)

በመጀመሪያ ደረጃ ያደረገችው ቢኖር (የምድብ ለ ምሳሌ)

## ሐ. ፀሐፊው በፅሑፉ ስላስፈራቸው መረጃዎች ወይም ሐሳቦች ያለውን አተያይ የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት

እነዚህ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት እንደ (በተመሳሳይ፣ ስለሆነም፣ ምንም እንኳ፣ የሆነ ሆኖ፣ ከሆነ) እና የመሳሰሉት ናቸው:: ስለሆነም ፀሐፊው ስለሚፅፈው ጉዳይ ያለውን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት የሚያመለክቱ ናቸው:: እንዲሁም ፀሐፊው በፅሑፍ ያገኛቸው መረጃዎች ያልጠበቃቸው መሆናቸው ወይም በመካከላቸው ዝምድና መኖሩን መመልከቱን (ማስተዋሉን) ሊያንፀባርቅባቸው የሚችልባቸው ናቸው:: ከዚህ አንፃር በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት በሦስት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ:: እነዚህም አካይ፣ ልየታዊ እና ሰበባዊ ናቸው::

## 1. አካይ (additive)

በዚህ ምድብ ሥር የሚካተቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ፀሐፊው ለሚፅፈው ጉዳይ ተጨማሪ መረጃዎች ወይም ሐሳቦች ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ለማመልከት የሚገቡ ናቸው:: ስለሆነም ለዚህ ዓይነት ተግባር ተጠቃሽ የሆነው አያያዥ እንዲሁም (and) የሚል ቢሆንም ለተለያዩ ተግባራት የሚውሉ ተመሳሳይ አያያገሮችም አሉ፤

እነዚህም:-

1. ተጨማሪ ማስረጃን መጥቀስ (Adducing further evidence) - በተጨማሪ፣ ከዚህ ሌላ . . . ወዘተ፣
2. የተነገረውን ሐሳብ ለመሸርሸር (De-emphasizing) - በተመሣሣይ፣ ባጋጣሚ . . . ወዘተ፣

## 2. ልዩታ (Adversative)

በዚህ ምድብ የሚካተቱ አያያዦች ደግሞ ፀሐፊው በሚፅፈው ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ሐሳብ ነው የሚለውን ለማመልከት የሚጠቀምባቸውን ነው:: ስለሆነም የዚህ ምድብ ተጠቃሽ አያያዥ "ግን" ቢሆንም የሁሉንም ስሜት ሊወክል ስለማይችል በተለያዩ ንኡሳን ክፍሎች ሥር የሚካተቱ አያያዦች መኖራቸው ግድ ይላል፤ እነዚህም:-

1. መካድ /ማስተባበል/ (Denying expectation) - ምንም እንኳ፣ ቢሆንም
2. ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል (Admitting the unexpected) - እርግጥ ነው፣ ባጋጣሚ፣ ወዘተ.
3. የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ሊከሰት እንደሚችል መንገር (Correcting from expected to unexpected) - በምትኩ፣ በተቃራኒው . . .ወዘተ
4. ማነፃፀር (Contrasting) በሌላ በኩል፣ በተመሳሳይ መልኩ፣. . . ወዘተ
5. የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ (Dismissing) የሆነ ሆኖ፣ በሁሉም አቅጣጫ፣ በማንኛውም መልኩ፣ . . . ወዘተ

## 3. ሰበባዊ (Causal)

የዚህ አዓይነት አያያዦች የምክንያትን፣ የውጤትን፣ የዓላማን እና የሁኔታን እርስ በርሳዊ ግንኙነት የሚያመለክቱ ናቸው:: ግንኙነታቸውም

ሀ. ፀሐፊው ከማያነሳቸው ጉዳዮች ውጭ ባሉ እውነታዎች ላይ ሊሆን ይችላል::

ለ. ፀሐፊው በሚፅፋቸው ጉዳዮች ላይ በሚነሱት ውስጣዊ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ:- ሀ. ሃይለኛ ድካም ተሰምቷታል:: <u>በዚህ የተነሳ</u> ከክፍሏ መውጣት አልቻለችም::

ለ. ጉዳዩ ከመጠን በላይ የተወሰሰበ ነው:: <u>በዚህ የተነሳ</u> በአሁኑ ሰዓት በጉዳዩ ላይ <u>ከዚህ በላይ</u> መሄድ አንችልም::

ከዚህ አኳያ የፀሐፊ አተያይን (አመለካከትን) ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት በተለያዩ ንኡሳን ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ፤ እነዚህም:-

1. አጠቃላይ (General) - በመሆኑም፣ ስለዚህ፣ በዚህ የተነሳ (Consequently)
2. ምክንያታዊ (Reason) - በዚህ ምክንያት፣ ምክንያቱም
3. ውጤት (Result) - ከተገኘው ውጤት በመነሳት፣ ከዚህ በመነሳት
4. ዓላማ (Purpose) - ይህንን መሠረት በማድረግ፣ ይህንን ለማሳካት፣
5. ሁኔታ(Condition) - በዚህ ሁኔታ፣ ከሆነ፣ አለበለዚያ፣

ከፍ ሲል የቀረበውን የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት (ዲስኩር አመልካቾች) አመዳደብና አከፋፈል ዝርዝር ከNuttal (1982:96-98) ስራ ወደ አማርኛ የተመለሰ ነው:: በዚህም ውስጥ እንደዋና መተንተኛ ተደረጎ መወሰዱን ከፍ ሲል ገልፀናል::

## 2.9 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

አጥኚው ባደረገው የቀደምት ስራዎች ቅኝት ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ቀጥተኛም ሆነ ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎችን ለመዳሰስ ሞክሯል::

ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ብቸኛ ተጠቃሽ ሥራ የጌታቸው እንዳላማው ሲሆን “በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነፅሁፍ ተማሪዎች በተፃፉ ተራኪ ውህድ አሀዶች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች ስርጭትና ተግባር ትንተና” በሚል ርዕስ በ1987 አማርኛ በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርበዋል:: የጥናታቸው አላማ የኮሌጁ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ የዲፕሎማ መርሀ ግብር የሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በፃፏቸው ሁለት ታራኪ ውሁድ አሀዶች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡትን ዲስኩር አመልካቾች ውሁድ አሀዳዊ ስርጭትና ተግባር በመተንተን በመጨረሻ የደረሱበት ነጥብ በተራኪ ውሁድ አሀዶች ውስጥ ተደጋግመው የገቡትን ዲስኩር አመልካቾች ተግባርና ስርጭት በመተንተንና በመፈረጅ በዋናና በንዑሳን ምድቦች ስር አጠቃለው አቅርበዋቸዋል:: ከዚህ በመነሳት ጠቃሚ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል:: በጥናቱ ውስጥ ከፍተኛ ድግግሞሽ ያላቸው ስምንቱ ተተኳሪ ዲስኩር አመልካቾች በጥናቱ ውጤት መሠረት በታዩት የዝምድና አይነቶች ተጠቃለው ቢቀርቡም ለአንዳንዶቹ የዝምድና አይነት የተገኙት መረጃዎች አነስተኛ በመሆናቸው

ተጨማሪ ጥናት ሊደረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል:: በዲስኩር አመልካቾች አገባብ ተግባር፣ እና በጭብጥ መዋቅር መካከል የጠበቀ ግንኙነት ሊኖር እንደሚችል፣ የዲስኩር አመልካቾች ተግባራት ከልማዳዊው ሰዋስው ግላዬና ዝርዝር አስረጅዎች በእጅጉ የተለዩ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል:: ስለሆነም የስርዓተ ትምህርትና የመማሪያ መፃህፌት አዘጋጆች ይህን ተረድተው በጥናት የደገፌ የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት እንደሚገባቸው የጠቆመ ነበር:: ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ከጌታቸው ጋር የሚያመሳስለው ጥናቱ ያተኮረው በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በዲስኩር አመልካቾች/ ላይ በመሆኑ ነው:: ከዚህ በተረፌ ሁለቱ ጥናቶች በመካከላቸው ብዙ ልዩነቶች አሉ:: የጌታቸውእንዳላማው ጥናት ያተኮረው በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የስነፅሁፍ ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው::

ሌላው በተጠኝዎች ተራኪ ውሁድ አሀዶች ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተደጋግመው የገቡትን ስምንት ተተኳሪ ዲስኩር አመልካቾች ውሁድ አሃዳዊ ስርጭትና ተግባር መተንተን ሲሆን የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ዓላማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሀረጋት አጠቃቀምና ስርጭት መመርመር ነው:: በዚህና ከፍ ሲል በቀረቡት ምክንያቶች የተነሳ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ሰፊ ልዩነት አለ::

ሌላው ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ኢ-ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች መኖራቸው እሙን ነው:: ምክንያቱም የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት ስንመረምር ስለፅህፌት ክሂል ማንሳታችን የግድ ነው:: በፅህፌት ክሂል ዙሪያ የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች ከጥናታቸው አላማ አኳያ ተተኳሪዎቻቸውን ድርሰት በማፃፍ የስህተት እርማትና ትንተና ያደረጉ፤ ከፅህፌት ትምህርት አኳያ መማሪያ መፃህፍቱንና መርሀ ትምህርቱን የገመገሙ፤ በፅህፌት ትምህርት አሰጣጥ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል ንፅፅራዊ ጥናት ያደረጉ፤ የፅህፌት ትምህርት አቀራረብን በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የፌተሹ ሁሉ ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ኢ-ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸው:: በመሆኑም አለማዬሁ ፀጋዬ (1986)፣ ማረው አለሙ (1987)፤ ስዩም ከበደ (1988)፣ ተክሌ አስፋው (1989)፣ ሰይድ ይመር (1993) ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው::

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ በአዲስ አበባ አስተዳደር በሚገኙ በተመረጡ የመንግስት እና የግል መሠናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት መመርመር ስለሆነ የሚከተለው የአጠናን ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል::

## 3.1 የጥናቱ ክልል እና የትምህርትቤቶች ናሙና አመራረጥ

### 3.1.1 የክልል ናሙና አመራረጥ

ከጥናቱ አላማ አኳያ በኢላማ (Purposive) እና በአመቺ (Convenient) ናሙና (Sampling) አመራረጥ የአዲስ አበባ መስተዳድር ተመርጧል:: ምክንያቱም ለጥናቱ የሚያስፈልጉ የመንግሥት እና የግል ትምህርትቤቶችን ለመምረጥ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሌሎች የክልል ከተሞች የተሻለ መሆኑን አጥኚው ስላመነበት በኢላማ ናሙና ሊመረጥ ችሏል:: እንዲሁም አጥኚው ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች በቅርብ ለማግኘት እንዲያስችለው በአመቺ ናሙና ተመራጭ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል::

### 3.1.2. የትምህርት ቤቶች አመራረጥ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ አሥር ክፍለ ከተሞች ውስጥ በአላማ ናሙና አመራረጥ ሁለት ክፍለ ከተሞች እና ሁለት የመንግሥት እና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች እንዲመረጥ ተደርጓል:: ይህም የተደረገበት ምክንያት ከጊዜና እና ከበጀት አንፃር በነዚህ ክፍለ ከተሞች እና ትምህርት ቤቶች ላይ መወሰን አስፈላጊ መሆኑን የዚህ ጥናት አቅራቢ ስላመነበት ነው:: በዚህ መሠረት በዕጣ ናሙና አመራረጥ ሁለት የመንግስት እና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን ሁለት ክፍለ ከተሞች መምረጥ አስፈላጊ ነበር:: ሆኖም በዕጣ ናሙና ከተመረጡት የጉለሌ እና የክልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የመንግሥት መሰናዶ ትምህርት ቤት የሌለው በመሆኑ ሌላ ሦስተኛ ክፍለ ከተማ መምረጥ የግድ ሆነ:: በመሆኑም በወጣው ዕጣ መሠረት ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማን በሦስተኛነት በመጨመር ሁለት የመንግስት እና ሁለት የግል ትምህርት ቤቶችን ለመምረጥ ተችሏል:: እነዚህም ከጉለሌ ክፍለ ከተማ “የካቲት 12 ከመንግስት ትምህርት ቤት፤ እናት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ ከግል ትምህርት ቤት” ተመርጠዋል:: ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ “ከፍተኛ 23 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከመንግሥት ትምህርት ቤት ሲመረጥ ከክልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ደግሞ ኮከብ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት” ከግል ተመርጧል::

በአጠቃላይ ከሶስቱ ክፍለ ከተሞች ሁለት የመንግስትና ሁለት የግል መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በድምሩ አራት ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ተካተዋል::

### 3.1.3 የተማሪዎች አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሆኑ የተደረገው በአላማ ናሙና ነው:: ይህም የተደረገበት ምክንያት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በ10ኛ ክፍል ማጠቃለያ ላይ የሚሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ተፈትነው የመሰናዶ ትምህርት የሚከታተሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ለማለፍ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በቂ ውጤት ማግኘት ስለሚጠበቅባቸው ከ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በተሻለ ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥተው ይከታተሉታል በሚል እምነት ነው:: ከዚህም ሌላ በ11ኛ ክፍል መርሐ ትምህርትና በተማሪው መማሪያ መጻህፍ ውስጥ አያያዥ ቃላትና ሐረጋት በይዘት መልክ በመቀረጻቸው ትምህርቱን የሰጧቸዋል በሚል ነው:: ለጥናቱ ከተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 40 ተማሪዎች እንዲሆኑ ተደርጓል:: ለዚህም ምክንያቱ ከተጠቀሰው ቁጥር በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል በሚል እምነት ነው:: በዚህ መሠረት ለጥናቱ ከተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች በነሲብ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (random sampling) በድምሩ 160 ተማሪዎች ተመርጠዋል::

ሠንጠረዥ 1:- የናመና ት/ቤቶች የመማሪያ ምድቦች በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች ብዛት

| | የናሙና ት/ቤት | የመማሪያ ምድቦች | ምናሙና የተመረጡ ምድቦች (25%) | የተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት | በተጠኝነት የተመረጡ ተማሪዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| የመንግስት | ከፍተኛ 23 | 11 | 3 | 600 | 40 |
| | የካቲት 12 | 15 | 4 | 783 | 40 |
| የግል | እናት | 3 | 1 | 136 | 40 |
| | ኮከብ | 2 | 1 | 101 | 40 |
| | ድምር | 31 | 9 | 1620 | 160 |

### 3.1.4 የመምህራን አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአላማ ናሙና አመራረጥ በተጠኝ ተማሪዎቹ መማሪያ ክፍል የሚያስተምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሆኑ ተደርጓል::

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ አጋዥ የሆኑትን መረጃዎች በአግባቡ ለመሰብሰብ በዋናነት የፅሑፍ መረጃ (ተማሪዎቹ የሚፅፉት ድርሰት) ተመርጧል:: በዚሁ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚገኘውን መረጃ ለመደገፍ

ደግሞ በተጠኝ ተማሪዎቹ የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ እና የተጠኝ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምላሽ የሚሰጡበት ቃለ መጠይቅ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

ተጠኝ ተማሪዎቹ የሚያዘጋጁትን ድርሰት በሚመለከት በተለያየ ጊዜ (ሁለት ጊዜ) እንዲፅፉ የተደረገ ሲሆን፣ አንደኛው እያንዳንዱ ተጠኝ ተማሪው በመረጠው ርእስ የሚፅፈው ድርሰት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ለሚፃፍ ድርሰትም፡፡ ከ150-300 ቃላትን ሊጠቀሙ እንደሚችሉ እንዲሆን የፅሑፍ እና የቃል መመሪያ ተሰጥቷል፡፡ የቃላት ብዛቱ ከፍ ማለት አያያገሮችን በብዛት ለመጠቀም ያስችላቸዋል በሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ድርሰት ደግሞ በዚህ ጥናት አቅራቢ እና በሌሎች ሦስት የሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የተመረጡ አማራጭ ርእሶች ቀርበውላቸው በመረጡት ርእስ ላይ የተፃፈ ነው፡፡ በአጠቃላይ ሁለት ጊዜ እንዲፅፉ የተደረገበት ምክንያት ስለ ድርሰት ምንነት እና የአፃፃፍ ስልት ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ ሳይሆን በድርሰቶቻቸው ውስጥ አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን እንዴት ባለሁኔታ ይጠቀሙባቸዋል በአጠቃቀም ረገድ የተሻሉትስ የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በብዛት የጠቀሙባቸው አያያገሮች ከምሁራኑ አመዳደብና አከፋፈል አንፃር በየትኛው ምድብ ስር ይካተታሉ የአጠቃቀም ጉድለት የታየው በምን የተነሳ ነው የሚውን ለመፈተሽ ሁለት ጊዜ ያህል ድርሰቶችን እንዲፅፉ ተደርጓል፡፡

### 3.2.1 የፅሑፍ መረጃ /ድርሰት/

በመጀመሪያ ደረጃ ጥናቱ በተማሪዎች የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም ላይ እንዲመሠረት የተደረገው በኢላማ ናሙና ነው፡፡ ምክንያቱም ለ11ኛ ክፍል በተዘጋጀው መርሃ ትምህርት እና የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም በሚመለከት በመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎቹ ተካትቶ ስለሚገኝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ለተማሪዎቻቸው ትምህርት እንደሚሰጡ አጥኚው በቃኚ ጥናት (survey study) ካገኘው መረጃ ለመረዳት በመቻሉ ነው፡፡

ለጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ እንዲያገለግል የተመረጠው ድርሰት በማፃፍ የአያያዥ ቃላትን አጠቃቀም መመርመር ነው፡፡ ይኸውም ከዚህ በፊት በተማሪዎች ድርሰት ወስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ተጠኝ ተማሪዎቹ ወጣት እንደመሆናቸው በተለያዩ ርዕሶች ድርሰት የመፃፍ ፍላጎት ይኖራቸዋል በሚል አጥኚው እምነት በማሳደሩ ሁለት ጊዜ /በተለያየ ጊዜ/ ሁለት ድርሰቶችን አፅፏል፡፡

### 3.2.2 የፅሑፍ መጠይቅ

የዕሑፍ መጠይቁ ክፍት እና ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ነው:: ይዘቱም Nuttall (1982:96-98) ስለአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ዋና እና ዝርዝር አከፋፈሎች በሚመለከት ያቀረቡትን መሠረት በማድረግ እና ፍሬሐሳቡን ወደ አማርኛ በመመለስ ነው:: የተዘጋጁት ጥያቄዎች በሁለት የሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጥባቸው ከተደረገ በኋላ ለዚህ ጥናት አማካሪ ቀርበው እርማት እና ማስተካከያ ከታከለባቸው በኋላ የፅሁፍ መጠይቆቹ ተግባር ላይ ውለዋል::

### 3.2.3 ቃለ መጠይቅ

ለአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ የቀረበው ቃለመጠይቅ ባብዛኛው ክፍት ጥያቄዎችን ያካተተ ነው:: ይዘቱም እንደ ዕሑፍ መጠይቁ ሁሉ Nuttall (1982:96-98) ስለአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አከፋፈል እና አጠቃቀም በሰጡት ሐሳብ ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ ስለተማሪዎቻቸው የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም እና ችሎታ እንዲሁም ስለሚሰጧቸው ምጋቤ ምላሽ የሚጠይቁ ናቸው:: የተዘጋጀው ቃለ መጠይቅ ቀደም ሲል በተጠቀሱት የድህረ ምረቃ ተማሪዎችና በጥናቱ አማካሪ ማስተካከያና እርማት ታክሎበት ተግባር ላይ ውሏል::

## 3.3 የመረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል

### 3.3.1 የፅሑፍ መረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል

ተጠኝ ተማሪዎቹ ራሳቸው በመረጡት ርእስ ድርሰት እንዲፅፉ ከመጠየቃቸው በፊት ስለጥናቱ ዓላማ ስለድርሰቱ መጠን በቃል እና በፅሑፍ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል:: በሌላ ጊዜ በአማራጭነት ከቀረቡት ርእሶች መካከል አንዱን መርጠው እንዲፅፉ ሲደረግም የአፃፃፍ መመሪያ የያዘ ወረቀት ለእያንዳንዳቸው እንዲደርሳቸው ተደርጓል:: በሚፅፉበት ጊዜም ለአስተራረም እንዲያመች አንዳንድ መስመር እየዘለሉ እንዲፅፉ የፅሑፍ እና የቃል ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል:: ሁለቱንም ድርሰቶች ሲፅፉም በራሳቸው ፍጥነት እንዲጨርሱ ዕድል ለመስጠት ሲባል ሰፋ ያለ ጊዜ /ከ1 ክፍለ ጊዜ በላይ/ ተሰጥቷቸዋል:: ድርሰቱንም እንዲፅፉ የተደረገው በአንድ በተለየ ክፍል በማስቀመጥ ነው:: (አባሪ 1 እና 2 ይመለከቷል)

### 3.3.2 የፅሑፍ መጠይቅ መረጃ አወሳሰድ ቅደም ተከተል

ተጠኝ ተማሪዎቹ የዕሑፍ መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ስለዓላማው እና ስለአሞላል ሂደቱ የተፃፈውን መመሪያ በቅድሚያ እንዲያነቡት ተደርጓል:: ያልገባቸው ነገር ቢኖርም እንዲጠይቁ እድል ተሰጥቷቸዋል:: የዕሑፍ መጠይቁንም የሞሉት በነፍስ ወከፍ ነው:: (አባሪ 4 ይመለከቷል)

### 3.3.3 የቃለ መጠይቅ መረጃ አወሳሰድ ቅድም ተከተል

የተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለቃለ መጠይቁ የሰጡት ምላሽ በግል ሲሆን፣ መረጃውን በዝርዝር ለማስቀረት ሲባልም በመቅረፀ ድምፅ ተቀርጿዋል:: (ዝርዝሩን በአባሪ 5 ይመለከቷል)

## 3.4 የፅሑፍ መረጃው የአስተራረም ሂደት

በተጠኚ ተማሪዎቹ የተፃፈው ድርሰት አንድና ሁለት በአራሚዎች እንዲታረም ሲሰጥ ለአራሚዎች ስለጥናቱ ዓላማ እና ስለአስተራረም ሂደቱ የሚገልፅ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፤ የቃል ማብራሪያም ተደርጎላቸዋል:: እርማቱም Nuttall (1982:96-98) ስለአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አከፋፈል እና አጠቃቀም የሰጡትን ሐሳብ መሠረት ያደረገ ነው:: በድርሰቱ እርማት ላይ የተሳተፉት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ልምድ ያላቸው ሶስት የሁለተኛ ዓመት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ናቸው:: (አባሪ 3ን ይመለከቷል)

## 3.5 የጥናቱ ዘዴ

ለጥናቱ የተመረጠው ዋነኛው ዘዴ ዓይነታዊ ዘዴ (qualitative method) ሲሆን፣ አሃዛዊ ዘዴ (quantitative method) ደግሞ በደጋፊነት ተግባራዊ ሆኗል::

### 3.5.1 ዓይነታዊ ዘዴ

ዓይነታዊ ዘዴ በዋናነት የተመረጠበት ምክንያት በድርሰቶቹ የተገኙት አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አከፋፈል፣ አጠቃቀም እና ስርጭት ለመተንተን አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: እንዲሁም በመንግስት እና በግል የሚማሩ ተጠኚ ተማሪዎች በአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት ያሳያሉ? ወይስ አያሳዩም? የሚለውን ለመመለስም ዓይነታዊ የአተናተን ዘዴ ቦታ ስላለው ነው::

### 3.5.2 አሃዛዊ ዘዴ

አሃዛዊ ዘዴ ከዓይነታዊ የአተናተን ዘዴ በተጨማሪ ያስፈለገበት ምክንያት ደግሞ በተጠኚ ተማሪዎቹ ግልጋሎት ላይ የዋሉ የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት ዓይነት እና ስርጭት በአሃዝ መግለፅ አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: ስለሆነም ከአሃዛዊ የአተናተን ዘዴ መካከል የመቶኛ ስሌት (Percentage) ተግባራዊ ሆኗል::

## 3.6 የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈል፣ አመዳደብ ምርጫ (የአመራረጥ) ሁኔታ

በዚህ ጥናት የተመረጠው የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ የNutal (1982:96-98) ሥራ ነው:: ይህ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ የተመረጠበት ምክንያት

ከሌሎች የመስኩ ምሁራን Haliday and Hassan (1976) የአያያዥ ቃላት አከፋፈልና አመዳደብ በተሻለ ሁኔታ ዘርዝር ብሎ በመቅረቡና ለዚህ ጥናት አሠራርም አመቺ ሆኖ በመገኘቱ ተመራጭ ሆኗል፡፡ በ Nutal (1982:96-98) የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አመዳደብና አከፋፈል መሠረት አያያገሮች በሶስት ዋና ዋና ምድቦች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

ምድብ ሀ፡- የአንድ ዕሁፍ ሁነት (events) ሲዘገብ የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት፡-

ምድብ ለ፡- የፀሀፊውን የዕሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት፡-

ምድብ ሐ፡- ፀሀፊው በፅሁፉ ውስጥ ስላስፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ወዘተ. ያለውን አተያይ/አመለካከት/ የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት፡-

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሶስት ምድቦች መካከል በምድብ “ለ” ና “ሐ” ስር የሚጠቃለሉ ንዑስና የንዑስ ንዑስ ዝርዝር አከፋፈሎች አሉ፡፡ በምድብ “ለ” ስር (8) ንዑስ ክፍሎች በምድብ “ሐ” ስር ደግሞ (3) ንዑስ ክፍሎች ሲኖሩ ከነዚህ ንዑስ ክፍሎች ስር (12) የንዑስ ንዑስ ዝርዝር ክፍፍሎች ተካተዋል፡፡

## የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ

ሠንጠረዥ 2፡- ምድብ “ሀ” የዕሁፍን ሁነት (events) ሲዘገብ የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

| ምድብ ሀ | መግለጫ | ከተማሪዎች ድርሰት የተወሰደ /ዱ/ ምሳሌ/ዎች/ |
|---|---|---|
| ጊዜ ጠቀስ (Temporal) | መቼ ብለን ስንጠይቅ በጥያቄው መልስ ውስጥ የሚገቡ/ባ/ (መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ መጨረሻ፣ ዛሬ፣ አሁን፣ ወዲያውኑ . . . ወዘተ) ጊዜን የሚያመለክት/ቱ/ (ጊዜ ጠቀስ) አመልካቾች የዕሁፉን ሁነት ከጊዜና ከድርጊት ቅደም ተከተል አኳያ ያሳያሉ፡፡ | (ከኮብ 088/01) . . . ምን እንዳሳቃት አልገባውም ጠይም ፊቱ አሸቦ መሰለ ወዲያውኑ ቀጠሮ የሰጠው ባለስልጣን መጣ፡፡<br>(ኮከብ 09/2) . . . አውራ ጎዳና መንገድ ላይ ከሚገኘው ጠጅ ቤት ጠጥቶ ሲጋራ እያጨሰ ወደ ቤት መግባቱ የዕለት ተዕለት ተግባሩ ከሆነ ሰንብቷል . . .<br>(የካቲ 144) . . . ወደ ስራ ቦታ ስሄድ አገኘኋት፡፡ እስቴርን ከዚያ በፊት አይቻት ስለማላውቅ ግርም አለኝና ጠራኋት . . . |

ሠንጠረዥ 3:- ምድብ ለ የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

| | ንዑስ | መገለጫ | ከተማሪዎች ድርሰት የተወሰደ/ዱ/ ምሳሌ/ዎች/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ክትትሎሽ አመልካች (Sequencing) | የነገሮችን ቅደም ተከተል የሚያመላክቱ አያያዦች ለምሳሌ (በቅድሚያ፣ ቀጥሎ፣ በአጠቃላይ፣ በመጨረሻ . . .) የመሳሰሉት ሊካተቱ ይችላሉ:: | . . . በመጀመሪያ ጓደኛዬ ስሟ ሬቲና ትባላለች:: የምትማርበት ትምህርት ቤት ሊሴ ሲሆን በጣም ጎበዝና ታታሪ ልጅ ናት:: |
| 2 | በድጋሚ መግለፅ (Re-expressing) | የበለጠ ግልፅ ለማድረግና ሀሳብን ደግሞ መግለፅ ለምሳሌ (በሌላ አነጋገር፣ ይህም ማለት፣ መቼም . . .) ያሉት አያያዦች ይከታተሉ | (ኮከብ 085) . . . ሁሉንም በአንድ አይን ነው የምታዬው ማለትም ለሁሉም እኩል አመለካከት አላት ... |
| 3 | በዝርዝር መግለፅ (Specifying) | ፀሀፊው ሀሳቡን የተብራራና ግልፅ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው አያገኖች ለምሳሌ (እነዚህም፣ በስም ለመጥቀስ ወዘተ) ይጠቀሳሉ | (ከፍተ 027/02) . . . ትንሽ ሱቅ የበዛባትና አብዛኛው ነዋሪ ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ እና ቤቱቹ እንኳን . . . |
| 4 | ለይቶ ማመልከት (Referring) | ፀሀፊው ለይቶ ለማመልከት የሚፈልገውን ሃሳብ ለማሳዬት የሚጠቀምባቸው አያገኖች አሉ ለምሳሌ (ይህን በሚመለከት፣ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከረው፣ ከዚህ በተለያየ መንገድ ወዘተ.) | (የካ/30) . . . ብዙዎቹ ተማሪዎች የት/ቤቱን ደንብ ትንሽ የሳቱት ይመስላል:: አስተማሪዎቹም ቢሆኑ በደንብ የተሟሉ አይደሉም:: (ከፍተ021/02) ... ለሰው የምትራራና ትዕግስተኛ ናት እኔ በተለይ የምወድላት ውስጣዊ ውበቷ ነው . . . |
| 5 | እንደገና ማንሳት (Resuming) | ፀሀፊው ሀሳቡን በድጋሚ ለማንሳት ሲፈለግ የሚጠቀምባቸው አያገኖች አለ ለምሳሌ (ቀደም ሲል ወደተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ ፣ በድጋሚ ለማስታወስ፣ በነገራችን ላይ . . . ) | ከፍ025/02. . . በጣም ተግባብተናል ማለት በጣም እንዋደዳለን በነገራችን ላይ የጓደኛ ዬን ስም አልነገርኳችሁም አይደል . . . |
| 6 | ምሳሌ መስጠት (Exemplifying) | ፀሐፊው ያነሳውን ሀሳብ በተለያዩ ምሳሌዎች አማካይነት ግልፅ አድርጎ ለማቅረብ | (ከፍ003/01). . . ዝግጅታቸውንም ለማቅረብ ለሚፈልጉ ክፍት ነው ለምሳሌ እንደባለፈው ቢዮንሴ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ለማቅረብ የሚጠቀምባቸው አያያዦች (ለምሳሌ፣ ይህንን በይበልጥ ለመግለፅ ወዘተ) ናቸው | መጥታ እንዳዘጋጀችው ኮንሰርት ለተለያዩ ነገሮች አስተዋፅዖ ያደርጋል:: |
| 7 | ማጠቃለል (Summarizing) | ፀሐፊው ያቀረባቸውን ሀሳቦች ለማጠቃለል ሲፈልግ የሚጠቀምባቸው አያያዦች ለምሳሌ (ለማጠቃለል፣ በአጭሩ፣ በአጠቃላይ . . .) | (ኮከብ 113) . . . አለማስረዳት ተማሪዎችን ያለማሳተፍ በጥቂቱ ብንቋጨው ችግሩን ለመፍታት ምን ማድረግ እንደሚገባ . . . |
| 8 | ትኩረት መስጠት (focusing) | ፀሀፊው በምዕራፍ ውስጥ ትኩረት ሰጥቶ የሚገልፃቸውን ሀሳቦች በነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መንደርደሪያነት መልዕክቱን ሊያቀርብ ይችላል:: ለምሳሌ (በዚህ ምዕራፍ ለማንሳት የሚሞከረው፣ ቀጥሎ የምንሸጋገረው . . .) | (ኮከብ117). . . ስትሄድ የሚንከባለል በርሜር ትመስላለች በነገራችን ላይ ወደ አፍንጫዋ ስመለስ . . .<br>(የካ124/1) . . . ሌላ ነገር ለማድረግ አቅሙ ከድቶታል በተለይ ያቺን ቀን አይረሳትም የሰቀቀንና የጭንቅ ኑሮ የጀመረባትን |

ሠንጠረዥ 4:- ምድብ ሐ ፀሀፊው በፅሁፉ ውስጥ ስላስፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ያለውን አተያይ/አመለካከት/ የሚያመለክቱ አያያዦች

| ንዑስ ምድብ | የንዑስ ንዑስ | መግለጫ | ከተጠኝ ተማሪዎች የተወሰደ/ዱ ምሳሌ/ዎች |
|---|---|---|---|
| አካይ (Additive) | 1. ተጨማሪ ማስረጃ መጥቀስ (Adducing further evidence) | ፀሐፊው ላነሳቸው ሀሳቦች ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለማቅረብ የሚጠቀምባቸው አያያዦች ለምሳሌ (በተጨማሪም፣ ከዚህ ሌላ፣ ከዚህ ባሻገር. . .) | (እና-065) . . . ለሰዎችም ብዙ በጎ ተግባራትን አድርጓል ከዚያም ባሻገር ሳሙኤልን በአንክሮ ለተመለከተው ሰው ቅን፣ ደግ፣ ለስላሳ፣ ቀልብን የሚስብ . . . |
| | 2. የተነገረውን ሃሳብ ለመሸርሸር (De-emphasizing) | ቀድሞ በቀረበው ሃሳብ ላይ የሚታከለውን ተመሳሳይ በሆነ አገላለፅ የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር የምንጠቀምባቸው | (ከፍ002). . . ሀኒ በጣም ታምራለች ባትባልም ግን ትስባለች የፊቷ ልስላሴ . . . (ከፍ027) መንገድ የዕድገት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አያያዦች ለምሳሌ (በተመሳሳይ፣ ባጋጣሚ፣ ወዘተ) | በር መሆኑን አጥቼው አይደለም ቢያንስ መንገድ ሲሰራ ለህዝቡ በማሰብ አማራጭ መንገድ . . . |
| ልየታ (Adversative) | 1. መካድ (ማስተባበል) (Denying expectation) | ፀሀፊው በፅሁፉ ውስጥ ስላሰፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ያለውንና የሚጠብቀውን የመጨረሻ ምኞች የሚገልፅበት ነው ምሳሌ (ምንም እንኳ ቢሆንም. . . ወዘተ) | (ከፍ004) . . . እጅግ በጣም የምወዳትና ምክሯን የምትለግሰኝ አንድ ጓደኛ አለችኝ ስለእርሷ የምገልፀው ነገር መናገር ቃላት ቢያንሰኝም መናገር እፈልጋለሁ:: |
| | 2. ያልተጠበቀ ነገር እንደሚከሰት መቀበል (admitting the unexpected) | ፀሀፊው ያልተጠበቀ ነገር እንደሚከሰት በመቀበል ሀሳቡን/አተያዩን/ ሚያመላክትባቸው አያያዦች መካከል (እርግጥ ነው፣ ባጋጣሚ ወዘተ) ናቸው:: | (እናት 057) . . . እያንዳንዱን ውበት እያጣ መጥቷል:: ቢሆንም ያንን የመሰለ ግርማ ሞገሱን ይጣ . . . |
| | 3. የጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሲከሰት እንደሚችል መንገር (correcting from expected to un expected) | የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሲከሰት እንደሚችል ለመንገር የሚጠቀምባቸው አያያዦች አሉ ከነርሱ ውስጥም ለምሳሌ (በተቃራኒው፣ በምትኩ ወዘተ.) | (እናት 047) . . . ከውጭ ሲያይዋት እንኳን የሰው ይቅር እና የዶሮ የማትመስለው ቤት በውስጧ ያልያዘችው ነገር የለም. . . |
| | 4. ማነፃፀር (contrasting) | በተነሱት ሃሳቦች መካከል በማነፃፀር ሀሳብን ለማቅረብ አያያዦችን ለመጠቀም ይቻላል:: ለምሳሌ (በሌላ በኩል፣ በተመሳሳይ መልኩ ወዘተ) | (ከፍ 014) . . . ሳቂታና ደስተኛ ነች ነገር ግን ሂሩት ስትናደድ ወይም ስትበሳጭ በጣም የምታስፈራራ ያ የቀኝ ዳማ ፊቷ በአንዴ ፍም የሚመስል . . . |
| | 5. የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ (dismissing) | በፅሁፉ ውስጥ ስለሰፈሩት ሀሳቦች ያለውን ወይም የነበረው እንዳልነበረ በማድረግ የሚገልፅበት ነው ለምሳሌ (የሆኖ ሆኖ፣ በማንኛውም | (ኮከብ 115). . . ቤቱ ካየኋቸው አስፈሪ የሆረር ፊልሞች መካከል አንዱ የተሰራበት ነው የሚመስለው እንደረዳሁት ከሆነ ግን ቤቱ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | መልኩ . . .) | በአንድወቅት ጫካውን የሚጠብቁ . . . |
| ሰበባዊ (Causal) | 1. አጠቃላይ (General) | ፀሀፊው አተያዩን /አመለካከቱን/ ሀሳቡን በምክንያትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ለማጠቃለል በተለያዩ አያያዦች ሊጠቀም ይችላል (በዚህ የተነሳ፣ በመሆኑም ስለዚህ . . .ወዘተ) | (ኮከ100) . . . ነጋዴናዎችንና ሽማቾችን የሚያገናኝ ስፍራ እንደመሆኑ መጠን በውስጡ የለያዩ ሽቀጣ ሽቀጦች . . . |
| | 2. ምክንያታዊ (reason) | ፀሀፊው አተያዩን በምክንያታዊ መንገድ ሊያቀርበው ይችላል ይህን ለማመልከት (በዚህ ምክንያት፣ ምክንያቱም ወዘተ) በሚሉት መጠቀም ይቻላል:: | (ኮ087) . . . ቆዳዋ በጣም ከመለስለሱ የተነሳ ለመንካት ያሳሳል:: |
| | 3. ውጤት (result) | ፀሀፊው ከአተያዩ በመነሳት በውጤት መልክ የሚያቀርበውን ሀሳብ (ከተገኘ ው ውጤት በመነሳት፣ ከዚህ በመነሳት . . . ወዘተ.) በሚሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ይጠቀማል):: | (ኮከ081) . . . ካሏት መልካም አመለካከት በላይ ሰውን ሁሉ ታከብራለች ከዚህ የተነሳ ሰፈርተኛው በሙሉ እንዲወዳትና እንዳያከብራት . . . |
| | 4. ዓላማ (Purpose) | ፀሀፊው አተያዩንና አመለካከቱን ለመግለፅ ዓላማዬ ብሎ ያሰውን እና የያዘውን ለመግለፅ ሲፈልግ የሚጠቀምባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ ከነርሱም ውስጥ (ይህንን መሠረት በማድረግ፣ ይህን ለማሳካት ወዘተ.) የሚሉት ሊሆኑ ይችላል | (የካ157) . . . ተማሪዎች በአይን ምልክት መልስ እንደሰጡኝ ማግባባት ጀመርኩ:: በዚህ መሠረት የተወሰኑትን ጥያቄዎች ሰርቼ የተቀሩትን . . . |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | **5. ሁኔታ** (Condition) | ፀሀፊው አንድን ሁኔታ (Condition) ቀድሞ ከተነሳው ሀሳብ /መልዕክት/ በመነሳት የግል አተያዩን /አመለካከቱን የሚያቀርብበት ነው ለምሳሌ (ከሆነ፣ እንዲህ ከሆነ፣ አለበለዚያ . . . ወዘተ) በሚል ሀሳቡን ሊሰነዝር ይችላል፡፡ | (እናት 069) . . . እስካሁን የሚያውቁት ሰዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ለብሶት የሚያውቀው ልብስ አንድ ብቻ ነው . . . |

(**ምንጭ** Nutal 1982:96-98)

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃዎች ትንተናና ውጤት

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዓላማ በአዲስ አበባ በሚገኙ የመንግስትና የግል መሠናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀማቸውን መፈተሽ ነው:: በዚህ መሠረት ጥናቱ ይመልሳቸዋል ተብለው የታቀዱ ዝርዝር ዓላማዎች:-

- ተጠኚ ተማሪዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት ምን ይመስላል?
- ተጠኚ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ከአላማቸው አኳያ በተገቢው መንገድ ይጠቀምባቸዋል?
- በመንግሥትና በግል ትምህርት ቤት ከሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀምና ስርጭት የተሻሉት የትኞቹ ናቸው?

የሚሉ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ከተጠኚዎች የተሰበሰቡ ድርሰቶች፣ የፅሁፍ መጠይቆች ለመምህራን ከቀረቡ ቃለመጠይቆች የተገኙ መረጃዎችን በመተንተን ከላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተሞክሯል:: በመሆኑም በመጀመሪያው ክፍል የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚ ተማሪዎችን የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት በመተንተን በተለያዩ ሰንጠረዦች ተደግፎ በተከታታይ ቀርቧል:: በመቀጠል ተጠኚ ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን ከአላማቸው አኳያ በተገቢው መንገድ ተጠቅማውባቸዋል /ተገልግለውባቸዋል/ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳ ዘንድ ከድርሰቶቻቸው መካከል የተወሰኑ ምሳሌዎች በማንሳት ትንተናው ተካሂዷል:: በመጨረሻም ከተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽና ከክፍል መምህራኑ ቃለመጠይቅ በተገኙ ምላሾች ላይ ትንተና ተካሂዷል::

## 4.1 የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት

ዲስኩር አመልካቾች ሰዋሰዋዊ አላባዎች አይደሉም:: ከተግባራቸው አንፃር በጥቅሉ ሲታዩ የሰዋስው አላባ ሳይሆኑ የትርጓሜ አካላት ናቸው:: ምክንያቱም በአንድ ውሁድ አሀድ ውስጥ የሚተላለፍን መረጃ (ሀሳብ) አንድነትና ዝምድና በይፋ የሚያመለክቱ በመሆናቸው ነው:: ጌታቸው (1987:5) ከዚህ ብያኔ አኳያ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት /የዲስኩር አመልካቾች/ ተግባርና ጠቀሜታ አኳያ በአንድ ውሁድ አሀድ አማካይነት የሚተላለፍን መረጃ አንድነትና ዝምድና በግልፅ የሚያመላክቱ ናቸው:: በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ያሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን /አመልካቾችን/ በአጠቃላይ ተገቢነት ማለትም ካላቸው ተግባር እና የስርጭት ስፋት አንፃር ለማዬት ተሞክሯል::

### 4.1.1 የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የአያያኘ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት መረጃ ትንተና

የግል ትምህርት ቤት (እናት እና ኮከብ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ) ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸው አያያዦች ስርጭት ምን ይመስላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በቅድሚያ ይህ ጥናት የአያያኘ ቃላትና ሀረጋት /የዲስኩር አመልካቾች/ አመዳደብና አከፋፈል መሠረት ያደረገው የNuttal (1982:96-98)ን ስራ ነው። ይህም በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል (ዝርዝሩን በገፅ 31-35 ይመለከታል)።

በዚህ አከፋፈልና አመዳደብ መሠረት ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸውን አያያኘ ቃላትና ሀረጋት ከአጠቃቀም ተገቢነት አኳያ በሶስቱ የድርሰት አራሚዎች መካከል ስምምነት የተደረሰባቸው /ያገኙት/ መረጃዎች በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 5፡ የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም፡፡

| ድርሰት | የግል ትምህርት ቤቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | እናት | | | | | | ኮከብ | | | | | | እናት + ኮከብ | | | | | |
| | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| አንድ | 299 | 83.52 | 59 | 16.48 | 358 | 100 | 262 | 75.07 | 87 | 24.93 | 349 | 100 | 561 | 79.35 | 146 | 20.65 | 707 | 100 |
| ሁለት | 338 | 84.92 | 60 | 15.08 | 398 | 100 | 272 | 83.95 | 52 | 16.05 | 324 | 100 | 610 | 84.49 | 112 | 15.51 | 722 | 100 |
| ድምር | 637 | 84.26 | 119 | 15.74 | 756 | 100 | 534 | 79.35 | 139 | 20.65 | 673 | 100 | 1171 | 81.95 | 258 | 18.05 | 1429 | 100 |

መግለጫ

1. ተገቢ አጠቃቀም
2. ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም
3. ድምር

ከሠንጠረዥ 5 እንደምንገነዘበው የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች በድምሩ አንድ ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ (1429) አያያዥር ቃላትና ሀረጋትን በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ሲገለገሉ ከነዚህ ውስጥ 1171 (81.95%) ያህሉ ተገቢ አጠቃቀም ያላቸው ሲሆን 258 (18.95%) ደግሞ ተገቢ አጠቃቀም የሌላቸው ናቸው:: የእናት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከኮከብ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአያያዥር ቃላት አጠቃቀም ረገድ ተሽሎ መታየቱን ከተገኘው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል:: እናት ከሰባት መቶ አምሳ ስድስት (756) አያያዦች ውስጥ 637 (84.26%)ቱ ተገቢ አጠቃቀም ሲኖራቸው 119 (15.74%) ያህሉ ብቻ ተገቢ አጠቃቀም የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል:: ኮከብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከስድስት መቶ ሳባ ሶስት (673) አያያዥር ቃላት መካከል 534(79.35%)ት ያህሉ ተገቢ አጠቃቀም ሲኖራቸው 139(20.65%) ያህሉ ተገቢ ባልሆነ አጠቃቀም ስር ተመዝግበዋል:: በሁለቱ ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል ያለው ልዩነት ከመረጃው ተረጋግጧል:: የኮከብ ሁለተኛ ደረጃ ተጠኝዎች የተጠቀሙባቸው አያያዦች ስርጭት አነስተኛ ከመሆኑም ሌላ ከአጠቃቀም ተገቢነት አንፃር ተገቢ ባልሆነ አጠቃቀም ስር የተመዘገቡት አያያዦች መረጃው ቁጥር ከፍ ብሎአል:: ይህንንም ከሰንጠረዥ አምስት መረዳት ይቻላል:: /ዝርዝር ምሳሌዎች በ4.2.1. ቀርበዋል/

ከዚህ ቀጥሎ የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ያሳዩትን ተገቢ የሆነ አጠቃቀም ከአያያዥር ቃላት አመዳደብና አከፋፈል አንፃር በየምድቡ ያላቸውን ስርጭት በሚመለከት ትንታኔ ቀርቧል::

በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ተገቢ የሆኑ የአያያዥር ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 6:- የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ከአያያዥር ቃላትና አመዳደብና አከፋፈል አንፃር::

| ድርሰት | የአያያዥር ቃላት አመዳደብና አከፋፈል | የግል ትምህርት ቤቶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እናት ከ/ሁ/ ደረጃ | | ኮከብ ከ/ሁ/ ደረጃ | | እናት + ኮከብ | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ድርሰት አንደና ሁለት | *ምድብ "ሀ" | 99 | 15.54 | 93 | 17.42 | 192 | 16.40 |
| | **ምድብ "ለ" | 127 | 19.94 | 111 | 20.78 | 238 | 20.32 |
| | ***ምድብ "ሐ" | 411 | 64.52 | 330 | 61.80 | 741 | 63.28 |
| | ድምር | 637 | 100 | 534 | 100 | 1171 | 100 |

*ጊዜ ጠቀስ አመልካች
** የጸሀፊው የጽሁፍ አደረጃጀት
*** የጸሀፊው አመለካከት

ሰንጠረዥ 6ን ከመተንተናችን በፊት የየምድቡን ምንነት በተመለከተ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የተገለፀ ቢሆንም እዚህ ላይ ዋና ዋናዎቹን ማስታወሱ ተገቢ ነው:: በመሆኑም በየምድቡቹ

ሊነሱ የሚገባቸውን ነጥቦች ከመጥቀሳችን በፊት ከምድብ “ሀ” በስተቀር ሁለቱ ምድቦች በስራቸው ንዑስ እና የንዑስ ክፍሎች አሏቸው በ“ለ” ምድብ ስምንት (8) ያህል ንዑስ ምድቦች ሲኖሩ ምድብ “ሐ” ደግሞ ሶስቱ (3) ንዑስ ምድቦችና አስራ ሁለት (12) ያህል ንዑሳን ክፍሎች ይዟል ሶስቱ ዋና ዋና ምድቦች በ Nuttal (1982:96-98) አከፋፈል መሠረት:-

ምድብ “ሀ” የአንድ ፅሁፍ ሁኔት (Events) ድርጊት ሲዘገብ የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያመለክቱ /ጊዜ ጠቀስ/ (Temporal) አያያዥ ቃላት /ዲስኩር አመልካቾች/ በዚህ ምድብ ስር ይከታተሉ:: /ዝርዝሩን በ4.2.1. ይመለከቷል/

ምድብ “ለ” የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት:- /ዝርዝር ምሳሌዎችን በ4.2.2. ይመለከቷል/

ምድብ “ሐ” አንድ ፀሐፊ በፅሁፉ ስላስፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ወዘተ. ያለውን አተያይ (Writers view) አመለካከት የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት እንደሆኑ በምዕራፍ ሁለት በስፋት ተገልጿል:: /ዝርዝር ምሳሌዎችን በ4.2.3. ይመለከቷል/

ከሠንጠረዥ 6 መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በየምድቡ ስር ተከፋፍለዋል:: የሁለቱም ትምህርት ቤት ተጠኚዎች በከፍተኛ መጠን የተጠቀሙባቸው አያያዦች በምድብ “ሐ” ስር የሚገኙትን እንደሆነ መረጃው ያሳያል:: ይህ ምድብ ከፍ ሲል በቀረበው ማብራሪያ መሠረት በውስጡ ሶስት ንዑስ ምድቦችን አስራ ሁለት ንዑሳን ክፍሎች እንዳሉት ተወስቷል:: “አንድ ፀሀፊ በፅሁፉ ውስጥ ስላሰፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች . . . ወዘተ ያለውን አተያይ/አመለካከት/ ለመግለፅ የሚያስችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት የሚገኙት በዚህ ምድብ ስር ነው:: ምድቡ አካይ (additive)፣ ልየታ (Adversative) እና ሰበባዊ (Causal) የተሰኙ ንዑስ ምድቦች ሲኖሩት በስራቸው አሰራ ሁለት ያህል ንዑሳን ክፍሎች አላቸው::: ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ ስንመለከት ሁለቱም ትምህርት ቤቶች በድምሩ 741(63.28%) ያህሉን የተቀጠሙት በዚህ ምድብ ስር ካሉት አያያዥ ቃላት ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የተገለገሉባቸው አያያዦች ደግሞ ምድብ “ለ” ማለትም የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመላክቱ አያያዦችን ነው:: በአጠቃላይ ከተገለገሉባቸው አያያዦች መጠን (20.32%) ያህሉን በምድብ “ለ” ስር ከሚገኙ አያያዦች ውስጥ መገልገላቸው መረጃው ይጠቁማል:: ምድብ “ሀ” በዝቅተኛ መጠን ከተጠቀመባቸው ምድቦች የመጀመሪያው መሆኑን ከቀረበው ሰንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል:: ይኸውም ተጠኚዎች በጠቅላላው ከተገለገሉባቸው የአያያዥ ቃላት መጠን (16.40%) ያህሉን ብቻ እንደተገለገሉባቸው ከመረጃው መገንዘብ ተችሏል::

ሁለቱን ትምህርት ቤቶች ከቀረበው መረጃ አንፃር ለየብቻ ብንመለከታቸው በሶስቱም (በሁሉም) የአከፋፈል ምድቦች ከፍተኛ አጠቃቀም ያሳየው እናት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። ይህንንም በሰንጠረዥ 6 ውስጥ በግልፅ ተመልክተነዋል።

ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ 7 ውስጥ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ዲስኩር አመልካቾች/ በዋና ዋና ምድቦችና ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍለዋል። የእያንዳንዳቸውም ዝርዝር ስርጭት ለማዬት ያመች ዘንድ በየድርሰቶቹ ተለያይተው ቀርበዋል።

## በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ያሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በዋና ዋና ምድቦችና ንዑሳን ክፍሎች

### ሠንጠረዥ 7:- በግል ትምህርት ቤቶች የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዝርዝር ስርጭት::

| የት/ቤት ይዘት | ድርሰት | የአያያዥ ቃላት ምድቦች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | ተገቢ አጠቃቀም ያላቸው አያያዦች | | ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ያላቸው አያያዦች | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ "ሀ" | ምድብ "ለ" | | | | | | | | ምድብ "ሐ" | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | የፀሀፊው የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት | | | | | | | | አካይ | | ልየታ | | | | | ሰበባዊ | | | | | | | | | | |
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| የግል | ድርሰት አንድ | 103 | 41 | 25 | 12 | 10 | 0 | 4 | 35 | 4 | 173 | 14 | 20 | 6 | 4 | 20 | 2 | 56 | 18 | 9 | 0 | 5 | 561 | 79.35 | 146 | 20.65 | 707 | 100 |
| | ድርሰት ሁለት | 89 | 36 | 12 | 10 | 20 | 0 | 6 | 22 | 1 | 223 | 12 | 4 | 1 | 3 | 46 | 2 | 90 | 28 | 7 | 0 | 1 | 610 | 8349 | 112 | 15.51 | 722 | 100 |
| | ድምር | 192 | 77 | 37 | 22 | 30 | 0 | 10 | 57 | 5 | 396 | 26 | 24 | 7 | 7 | 63 | 4 | 146 | 46 | 10 | 0 | 6 | 1171 | 81.95 | 258 | 10.08 | 1429 | 100 |

መፍቻ- ምድብ ሀ- የጽሁፍ ሁነት /ጊዜጠቀስ/ አመልካች

ምድብ ለ- የጸሀፊው የጽሁፍ አደረጃጀት

1. ክትትሎሽ አመልካች
2. በድጋሜ መግለጽ
3. በዝርዝር መግለጽ
4. ለይቶ ማመልከት
5. እንደገና ማንሳት
6. ምሳሌ መስጠት
7. ማጠቃለል
8. ትኩረት መስጠት

ምድብ ሐ- የጸሀፊው አመለካከት

አካይ 1. ተጨማሪ ማስረጃ መጥቀስ
2. የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር

ልየታ 1. መካድ ማስተባበል
2. ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል
3. የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሊከሰት እንደሚችል መንገር
4. ማነጻጸር
5. የነበረውን እንዳልነበር ማድረግ

ሰበባዊ 1. አጠቃላይ
2. ምክንያታዊ
3. ውጤት
4. ዓላማ
5. ሁኔታ

ከሠንጠረዥ 7 መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው አያያዥ ቃላቱ ተከፋፍለው የቀረቡባቸው ዝርዝር ንዑሳን ክፍሎችም ሆኑ ዋና ዋና ምድቦች ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸውን የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አይነትና ምድብ ያመላክታሉ:: በከፍተኛ መጠን የተቀጠሙባቸውን ምድቦች እንደምድብ ከማዬታችን በፊት በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ካሉት ንዑስ ምድቦችና ንዑሳን ዝርዝር ክፍሎች ውስጥ በየራሱ በየምድቡ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የስርጭት መጠንና በጣም ዝቅተኛውን ለማዬት እንሞክር በተናጠል በየድርሰቶቹም ሆነ በጋራ በሁለቱም ድርሰት ከፍተኛ መጠን ያለው በምድብ "ሐ" ውስጥ በንዑስ ምድብ /ክፍል/ "አካይ" ውስጥ የሚገኘው የንዑስ ንዑስ ክፍል አንድ (1) "ተጨማሪ ማስረጃ መጥቀስ" (Adducing further evidence) የተሰኘውን ንዑስ ክፍል በድርሰት አንድና ሁለት በጠቅላላው ሶስት መቶ ዘጠና ስድስት (396) ጊዜ ያህል ተጠቅመውበታል ወይም ተገልግለውበታል:: በዚህ የንዑስ ንዑስ ክፍል ውስጥ ከተጠቀሱት አያያዦች መካከል /በተጨማሪ፣ ከዚህ ሌላ፣ ከዚህ ባሻገር . . ./ የመሳሰሉት ይገኙ ብታል::

በምድብ "ለ" ንዑስ ክፍል ቁጥር አምስት (5) "በድጋሚ ማንሳት" (Resuming) እና በምድብ "ሐ" የንዑስ ንዑስ ክፍል ቁጥር አራት (4) "ዓላማ" (Purpose) የሚሉት ንዑስና የንዑስ ንዑስ ክፍሉች በድርሰት አንድም ሆነ ሁለት ውስጥ ከተሰበሰበው የተማሪዎች ድርሰት ምንም ማስረጃ እንዳልተገኘላቸው ከሁሉም አራሚዎች የተገኘው መረጃ ይጠቁማል:: /አባሪ ስምንትን ይመለከቷል/::

በሰንጠረዥ 7 መረጃ መሰረት ተጠኝዎች አያያዦችን በእኩል ደረጃ ሶስቱን ዋና ዋና ምድቦች አልተጠቀሙባቸውም ይህንንም ከመረጃው ማረጋገጥ ችለናል:: አያያዦችን የምንገለገልባቸውና የምንጠቀምባቸው አስፈላጊ ሆነው ሲገኙና ያለእርሱ ተጨማሪነት ዓረፍተ ነገሮቹ ዝምድናቸው በግልፅ የማይታይ ሲሆን ብቻ ነው አለዚያ ቃላቱ መደረቻ ከመሆናቸውም አልፎ አንባቢን ያሰለቻሉ ዳኛቸው (1977፣127) ከዚህ አኳያ ልንገነዘበው ይገባል ይላሉ ተጠኝዎች ይህን ተገንዝበው ከአላማቸው አኳያ ተገልለውባቸዋል ለማለት ግን አንደፍርም:: ምክንያቱም የአጠቀቀም ተገቢነት የሌላቸው አያያዦችን ቀደም ሲል ተመልክተናል::

### 4.1.2 የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና ስርጭት መረጃ ትንተና

ሠንጠረዥ 8: የመንግስት ት/ቤት ተማሪዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም

| ድርሰት | የመንግስት ትምህርት ቤቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የካቲት 12 | | | | | | ከፍተኛ 23 | | | | | | የካቲት 12 + ከፍተኛ 23 | | | | | |
| | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ድርሰት አንድ | 312 | 91.23 | 30 | 8.77 | 342 | 100 | 334 | 86.30 | 53 | 13.70 | 387 | 100 | 646 | 88.61 | 83 | 11.39 | 729 | 100 |
| ድርሰት ሁለት | 377 | 95.93 | 16 | 4.07 | 393 | 100 | 292 | 85.43 | 58 | 16.57 | 350 | 100 | 669 | 90.04 | 74 | 9.96 | 742 | 100 |
| ድርሰት አንድና ሁለት | 689 | 93.74 | 46 | 6.26 | 735 | 100 | 626 | 84.94 | 111 | 15.06 | 737 | 100 | 1315 | 89.33 | 157 | 10.67 | 1472 | 100 |

**መግለጫ**

1. ተገቢ አጠቃቀም
2. ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም
3. ድምር

የመንግስት ትምህርት ቤት (የካቲት 12 እና ከፍተኛ 23 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ) ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸው አያያዞች ስርጭት ከፍ ሲል ከቀረበው ሰንጠረዥ 8 እንደምንመለከተው ተጠኝዎች በድምሩ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሁለት (1472) አመልካቾችን ተጠቅመዋል:: ከዚህ አጠቃላይ ድምር ወስጥ 1315 (89.33%) ያህሉን በድርሰቶቻቸው ውስጥ በተገቢ ሁኔታ አያያዦችን ሲጠቀሙባቸው የቀሩት 157(10.67%)ቱ ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም እንዳላቸው ከመረጃው ተረጋግጧል:: ይህ ውጤት በድርሰት አንድና ሁለት ሁሉቱም የመንግስት ትምህርት ቤቶች በጋራ ያስመዘገቡት ነው:: ሆኖም እያንዳንዱ ት/ቤት በተናጠል ለማዬት ስንሞክር ከአጠቃቀም ተገቢነት አንፃር የተሻለ አጠቃቀም ያለው የካቲት 12 ትምህርት ቤት ነው:: ይህን ውጤት ያስመዘገበው በድርሰት ሁለት ውስጥ ሲሆን፤ የካቲት በድርሰት አንድና ሁለት በድምሩ 689(93.74%) ያህል ተገቢ አጠቃቀም ሲያሳይ ከፍተኛ 23 ደግሞ በድርሰት አንድና ሁለት በጠቅላላው 626(84.94%) ያህል ተገቢ የሆነ አጠቃቀም ሲያሳይ 111(15.06%) ያህሉ የአጠቃቀም ስህተት እንደታየባቸው መረጃው ያመለክታል:: ከፍ ሲል በሰንጠረዥ 5 የቀረበውን የግል ት/ቤት ተጠኝዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና በሰንጠረዥ 8 የቀረበውን የመንግስት ት/ቤት ተጠኝዎች አጠቃቀም ስንመለከት በተገቢ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ረገድ ጎልተው የታዩት የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ናቸው:: ይኸውም የመንግስት ት/ቤት ተጠኝዎች (1315) ያህል አያያዦችን በተገቢ ሁኔታ ሲጠቀሙባቸው የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች (1171) ያህል አያያዦችን በትክክል ተጠቅመውባቸዋል:: በሁለቱም ተጠኝዎች ዘንድ የተመዘገቡትን ተገቢያልሆኑ አጠቃቀሞች ስንመለከት ደግሞ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች (157) ያህል የአጠቃቀም ጉድለት ሲታይባቸው የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች (258) ያህል አያያዦችን በተገቢው ሁኔታ ሳይጠቀሙባቸው ቀርተዋል:: ይህም በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለው የአያያዥ ቃላት አጠቀቀም ልዩነት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳና እንድንመረምር ያደርገናል::

ከላይ በሰንጠረዥ 5 እና 8 የተመለከትነው ተገቢና ተገቢ ያልሆነ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ልዩነት የተሰላው ተጠኝዎች ከተጠቀሙባቸው አጠቃላይ የአያያዥ ቃላት ድምር ነው::

ከዚህ ቀጥሎ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ያሳዩት አጠቃቀም ከአያያዥ ቃላት አከፋፈልና አመዳደብ አንፃር በየምድቦቹ ስር ያላቸው ስርጭት በሠንጠረዥ 9 እንደሚከተለው ቀርቧል::

በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ተገቢ የሆነ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም:-

ሠንጠረዥ 9:- የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከተገቢ የአያያዥ ቃላት አመዳደብና አከፋፈል አንፃር::

| ድርሰት | የአያያዥ ቃላት አመዳደብና አከፋፈል | የመንግስት ትምህርት ቤቶች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የካቲት 12 ከ/ሁ/ ደረጃ | | ከፍተኛ 23 ከ/ሁ/ ደረጃ | | የካቲት 12 + ከፍተኛ 23 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ድርሰት አንደና ሁለት | ምድብ “ሀ” | 134 | 19.45 | 124 | 19.81 | 258 | 19.62 |
| | ምድብ “ለ” | 93 | 13.50 | 107 | 17.09 | 200 | 15.21 |
| | ምድብ “ሐ” | 462 | 67.05 | 395 | 63.10 | 857 | 65.17 |
| | ድምር | 689 | 100 | 626 | 100 | 1315 | 100 |

በሠንጠረዥ 9 ውስጥ የቀረበውን መረጃ ስንተነትን በየምድቦቹ ስር ከተጠኚዎች አጠቃቀም አኳያ የተለያየ መጠን ያላቸው ቁጥሮች ሰፍረዋል:: በመሆኑም የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች በጋራ ያስመዘገቧቸውንና በተናጠል የተጠቀሙባቸውን በማዬት የምድቦቹን ተናጠላዊ ውጤት እንመለከታለን የሁለቱ ትምህርት ቤት ተጠኚዎች በጋራ አንድ ሺህ ሶስት መቶ አስራአምስት (1315) አያያዥ ቃላትን በተገቢ ሁኔታ እንደተቀጠሙባቸው መረጃው ያመላክታል:: ከዚህ አጠቃላይ ውጤት ውስጥ የካቲት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (689) ያህል አያያገሮችን ሲቀጠም ከፍተኛ 23 ትምህርት ቤት ደግሞ (626) ያህል አያያገሮችን ተጠቅሟል:: ከአያያዥ ቃላት አመዳደብና አከፋፈል አኳያ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተጠኚዎች ዘንድ በስፋት ጥቅም ላይ የዋለው ምድብ “ሐ” ሲሆን የየካቲት ተጠኚዎች (462) ያህል የምድቡን አያያገሮች ሲጠቀሙ የከፍተኛ ሃያ ሶስት ተጠኚዎች ደግሞ ከዚሁ ከምድብ “ሐ” (395) ያህል አያያገሮችን በተገቢ አጠቃቀም በድርሰቶቻቸው ውስጥ መገልገላቸውን መርጃው ያሳያል:: እዚህ ላይ በሁለተኛ ደረጃ ማለትም (ከአጠቃቀም ብዛት) አኳያ ምድብ “ሀ” ተከታይ ሲሆን የካቲት (134) ያህል ከፍተኛ 23 (124) ያህል አያያገሮችን ተጠቅመዋል:: በሁለቱ ምድቦች ማለትም በምድብ “ሀ” እና “ሐ” የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም የካቲት 12 ከፍተኛ 23 ብልጫ ሲያሳይ በምድብ “ለ” አጠቃቀም በኩል ከፍተኛ ሃያ ሶስት የሻለ አጠቃቀም አሳይቷል:: በሰንጠረዥ 9 ውስጥ ያሉትን የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ በዝርዝርና በስፋት ለማየት ያመቸን ዘንድ ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ እንመልከት::

በሠንጠረዥ 10 ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ዲስኩር አመልካቾች/ በዋና ዋና ምድቦችና ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል:: የእያንዳንዱን ንዑስ ክፍል ዝርዝር ለማየት ይቻል ዘንድ በየምድቦቹ ባሉት ክፍልፋዮች (መገኛ ቁጥሮች) ስር ሰፍሯል::

# በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ ያሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በዋና ዋና ምድቦችና ንዑሳን ክፍሎች

## ሠንጠረዥ 10:- በመንግስት ት/ቤቶች የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዝርዝር ስርጭት

| የት/በት ይዘት | ድርሰት | የአያያዥ ቃላት ምድቦች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | ተገቢ አጠቃቀም ያላቸው አያያዦች | | ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም ያላቸው አያያዦች | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ "ሀ" | ምድብ "ለ" | | | | | | | | ምድብ "ሐ" | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | የፀሀፊው የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት | | | | | | | | አካይ | | ልየታ | | | | | ሰበባዊ | | | | | | | | | | |
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| የመንግሥት | ድርሰት አንድ | 138 | 35 | 19 | 13 | 10 | 11 | 9 | 10 | 0 | 196 | 22 | 25 | 7 | 11 | 23 | 7 | 55 | 39 | 7 | 5 | 4 | 64.6 | 88.61 | 83 | 11.39 | 729 | 100 |
| | ድርሰት ሁለት | 120 | 36 | 14 | 9 | 13 | 4 | 4 | 12 | 2 | 223 | 8 | 6 | 1 | 4 | 64 | 0 | 90 | 45 | 12 | 1 | 1 | 669 | 90.04 | 74 | 9.96 | 743 | 100 |
| | ድምር | 258 | 71 | 33 | 22 | 23 | 15 | 13 | 22 | 2 | 419 | 30 | 31 | 8 | 15 | 87 | 7 | 145 | 84 | 19 | 6 | 5 | 1315 | 88.33 | 157 | 10.67 | 1472 | 100 |

መፍቻ- ምድብ ሀ- የጽሁፍ ሁነት /ጊዜጠቀስ/ አመልካች

ምድብ ለ- የጸሀፊው የጽሁፍ አደረጃጀት

9. ክትትሎሽ አመልካች
10. በድጋሚ መግለጽ
11. በዝርዝር መግለጽ
12. ለይቶ ማመልከት
13. እንደገና ማንሳት
14. ምሳሌ መስጠት
15. ማጠቃለል
16. ትኩረት መስጠት

ምድብ ሐ- የጸሀፊው አመለካከት

አካይ1. ተጨማሪ ማስረጃ መጥቀስ
2. የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር

ልየታ1. መካድ ማስተባበል
2. ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል
3. የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሊከሰት እንደሚችል መንገር
4. ማነጻጸር
5. የነበረውን እንዳልነበር ማድረግ

ሰበባዊ 1. አጠቃላይ
2. ምክንያታዊ
3. ውጤት
4. ዓላማ
5. ሁኔታ

ከሠንጠረዥ "10" መረጃ እንደምንገነዘበው በየምድቦቹ ስር ባሉ ንዑስና የንዑስ ንዑስ ክፍሎች ተጠኝ ተማሪዎች በምን ያህል መጠን እንደተገለገሉባቸው መረጃው በግልፅ ያሳያል:: በምድብ "ሐ" ንዑስ ክፍል "አካይ" የንዑስ ንዑስ ክፍል አንድ (1) "ተጨማሪ ማስረጃን መጥቀስ" (Adducing further evidence) ስንመለከት በድርሰት አንድና ሁለት በድምሩ አራት መቶ አስራ ዘጠኝ (419) ያህሉን ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ ተጠቅመውባቸዋል:: ዝቅተኛ አጠቃቀም ከታዩባቸው ንዑሳን ክፍሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን በምድብ "ለ" ስር ያለውን ንዑስ ክፍል ስምንት (8) ደግሞ ከሁለቱ ድርሰቶች አጠቃላይ የተገኘው ሁለት (2) ብቻ ነው ይህም በአንዱ ድርሰት ማለትም በድርሰት ሁለት ሥር የሠፈረ ወይም የተገኘ ነው በምድብ "ለ" የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመላክቱ ዲስኩር አመልካቾች ብዛት በሰንጠረዡ እንደሚታዬውም ሆነ በምዕራፍ 3 ውስጥ በምሳሌና በመግለጫ ተደግፈው እንደቀረቡት በምድብ "ለ" ንዑስ ክፍል ስምንት (8) "ትኩረት መስጠት"ን (Focusing) የሚያመለክቱ አያያዦች ያሉበት በመሆኑ ፀሀፊው ትኩረት ሰጥቶ ሊገልፃቸው የፈለጋቸውን ሀሳቦች በነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መንደርደሪያነት መልዕክቱን ያቀርባል:: በዚህ ንዑስ ምድብ /ክፍል/ የምንጠቀምባቸው ዲስኩር አመልካቾች ለምሳሌ /በዚህ ምዕራፍ ለማንሳት የሚሞከረው፣ ቀጥሎ የምንሸጋገረው . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው::

በሰንጠረዥ "10" ከተመለከተው መረጃ አንፃር ተማሪዎች ይህን ንዑስ ክፍል በተገቢው ሁኔታ እንዳልተጠቀሙበት መረጃው በግልፅ ያሳያል:: እዚህ ላይ በዚህ ንዑስ ክፍል የተመደቡ አያያዦችን በፅሁፋቸው ውስጥ አለመገልገላቸው ፀሀፊው ለአንባቢው የሚያስተላልፈውን መልዕክት ትኩረት ሰጥቶ እንዲያነበው የሚያስችሉ መሆናቸውን ለይተው ባለማወቃቸው /ባለመማራቸው/ ወይም በፅሁፍ ወቅት እነዚህን አያያዦች መጠቀም አስፈላጊ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል:: በተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ አለመገኘታቸው ከተሰበሰበው መረጃ ተረጋግጧል:: ከምድብ "ሐ" ንዑስ ክፍሎች አንዱ የሆነው ሰበባዊ ስንመለከት ከዚህ ንዑስ ምድብ ስር ካሉት ንዑሳን ክፍሎች ወስጥ ተጠኝዎች በብዛት የተጠቀሙባት የንዑስ ንዑስ ክፍል አንድን (1) ነው:: እርሱም "አጠቃላይ" (General) በሚል ተለይቶ የሚታወቀው ሲሆን ከዚህ ክፍል ተጠኝዎች (145) ያህል አያያዦችን በድርሰቶቻቸው ውስጥ በተገቢ ሁኔታ እንደተጠቀሙባቸው ከአራሚዎች የተገኘው መረጃ ይጠቁማል:: በዚህ ክፍል ውስጥ የሚጠቃለሉት አያያዥ ቃላት /ዲስኩር አመልካቾች/ ፀሀፊው አተያዩን /አመለካከቱን/ ሀሳቡን በምክንያትና ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ለማጠቃለል የሚጠቀምባቸው አያያዦች ናቸው:: እነርሱም /በዚህ የተነሳ፣ በመሆኑም ፣ ስለዚህ . . .ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ከተጠኝዎች አጠቃቀም አንፃር ይህን የንዑስ ንዑስ ክፍል በርከት ባለ ሁኔታ ተገልግለውባቸዋል:: ከአጠቃቀም ጉድለት አኳያም ሲታይ አጠቃቀማቸው ላይ ችግር ጉልቶ አለመታየቱን ከመረጃዎች መረዳት ይቻላል::

ከዚህ በታች የቀረበው ንዑስ ክፍል በተማሪዎች ድርሰት ላይ በመመርኮዝ የአያያዥ ቃላትን አመዳደብና አከፋፈል ከንዑስና ንዑሳን ክፍሎች አንፃር የተለያዩ ምሳሌዎችን በማንሳት ሶስቱ ዋና ዋና ምድቦችና በስራቸው የሚገኙትን ሃያ ያህል ንዑስና የንዑስ ንዑስ ክፍፍሎች ለመተንተን ይሞከራል፡፡

## 4.2 ድርሰት አንድ እና ሁለት ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ተገቢ መሆን አለመሆን አንፃር

በድርሰት አንድና ሁለት ውስጥ በጥቅሉ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ አንድ (2901) ያህል አያያዦች /ዲስኩር አመልካቾች/ ተመዝግበዋል፡፡ ከነዚህ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ውስጥ አራት መቶ አስራ አምስት (415) ያህሉ የአጠቃቀም ጉድለት እደታየባቸው ከሰንጠረዥ "5" እና "8" ተረድተናል፡፡ አያያዥ ቃላቱ በተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ እንዴትና በምን ሁኔታ እንደገቡ ከአመዳደብና አከፋፈላቸው አንፃር እንዲሁም ተጠኝዎች አያያዥ ቃላትና ሀረጋቱን ከአላማቸው አኳያ በተገቢ መንገድ መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማዬት ተሞክሯል፡፡

በዚህ የትንተና ክፍል ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸውን አያያዥ ቃላት ተገቢነት፣ ከተነሱበት አላማ አኳያ የአያያዦቹን አገባብና ባህሪ በማየት በተለያዩ ምድቦች በመክፈልና በመመደብ ትንተና ተካሂዷል፡፡ ይህ ትንተና መሠረት ያደረገው በሶስት ዋና ዋና የምሁራኑ አከፋፈል ላይ እንደሆነ ቀደም ሲል ምዕራፍ ሦስት ተገልጿል፡፡

### 4.2.1 ምድብ "ሀ" የድርጊት /የጊዜ/ ቅደም ተከተልን የሚያመለክቱ ጊዜ ጠቋሚ (Temporal) አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

እንደመስኩ ምሁራን አገላለፅ ጊዜ ጠቋሚ አመልካቾች "መቼ?" በሚል ጥያቄ ሲቀርብ መልስ ሆነው የሚቀርቡ /የሚመመጡ/ ናቸው ይላሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት አያያዦች ደግሞ በምድብ "ሀ" ስር ይካተታሉ፡፡ የጊዜን ዝምድና አስመልክተው ጌታቸው (1987፣57) በሁለት የውህድ አሃድ ዓረፍተ ነገሮች መካከል እንዲኖር የተፈለገው ወይም ያለው ዝምድና የጊዜንና የሁነትን ተለጣጥቆ /Sequence/ ሲያመለክት የሚታየው ዝምድና ነው ይላሉ፡፡ በቅድሚያ የተጠኝዎችን ተገቢ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም የሚያሳዩ ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

ምሳሌ (1) . . . ይህ ሰውዬ ከጊዜ በኋላ አዕምሮው ተነክቶ በየዕለቱ ወደ መጠጥ ቤት እየሄደ ሁልጊዜ ይሰክር ነበር . . . (የካ142/5)

ምሳሌ (2) . . . ምላሽ ባለማግኘቴ ወሬውን መስማት ቀጠልኩ፡፡ አሁንም ስለልጅቷ ቁንጅና ማውራታቸውን አላቋረጡም . . . (ከፍ 009/1)

ምሳሌ (3) . . . አይናቸው ከአንድ ቆንጆ ላይ ያርፋል፡፡ ወዲያው ጊዜ ሳያጠፉ አብረዋት. . . (ኮከብ 111/2)

ከምሳሌ (1) እንደምንረዳው "ከጊዜ በኋላ" "በየዕለቱ" የሚሉት ስንመለከት በምድብ ሀ ውስጥ "መቼ?" ብለን ጥያቄ ስናነሳ መልስ ሆነው የሚገቡት ጊዜ ጠቀስ አመልካቾች ናቸው፡፡ በምሳሌ (1) ውስጥ የተጠቀሰው ባለታሪክ ያከናውናቸው የነበሩትን ድርጊቶች ከጊዜ አንፃር በማመልከት ረገድ ምሳሌ ውስጥ የገቡት አያያዦች መልዕክቱን ግልፅ አድርገውታል፡፡

በምሳሌ (2) እና (3) ስር የቀረቡትን ምሳሌዎች ሰንመለከት ደግሞ በምሳሌ (2) ሥር "አሁንም" የሚል ጊዜ አመልካች እና በምሳሌ (3) ደግሞ "ወዲያውኑ" የሚል ጊዜን የሚያመለክት አያያዥ አለ፡፡ በሁለቱ ምሳሌዎች ውስጥ ያሉት ጊዜ ጠቀስ አመልካቾች ስንመለከት በምሳሌ (2) "አሁንም" ማውራታቸውን አላቋረጡም ድርጊቱ ቀጣይ መሆኑን ያስረዳናል፡፡ ምሳሌ (3) ውስጥ የተጠቀሰው "ወዲያው" የሚለው ደግሞ ምንም ጊዜ ሳይወስድ በፍጥነት የሚል ሀሳብን ያስተላልፋል፡፡ በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሱት ጊዜ ጠቀስ አያያዦች የድርጊት ክንውንን ከጊዜ አንፃር በግልፅ ያሳያሉ፡፡

ምሳሌ (4) . . . ከእንጨት የተሰራው ጠረጴዛ ላይ በአንድ ወቅት ጥሩ ምሳ ወይም እራት የተበላባቸው እቃዎች ሳይነሱ እዛው . . . (ኮከብ 115/2)

ምሳሌ (5) . . . ሁሉም ነገር ተጠናቀቀ ለመጀመሪያ ጊዜ ላም አለብኩ፡፡ . . . (ኮከብ 087/2)

ምሳሌ (6) . . . የሚያማምሩት አለንጋ ጣቶቿ አንዳንዴ እጄን ሲነኩት በረዶ የደፉብኝ ይመስላል . . . (እናት 049/1)

ምሳሌ 4፣ 5፣ 6 በየተራ ለመመልከት እንሞክራለን በምሳሌ (4) ውስጥ የገባው ጊዜ ጠቅሶ አያያዥ "በአንድ ወቅት" የሚል ነው በውል ተለይቶ በዚህ ጊዜ የማይባል ነገር ግን በሆነ ጊዜና ሰዓት የተከወነን ድርጊት አስመልክቶ ባለፈ ነገር ላይ የተዘገበ ነው፡፡ ጊዜው ተለይቶ አይታወቅ እንጅ በአንድ አጋጣሚ ወይም ክስተት ስለተደረገው ነገር ለማውሳት የተሞከረው በጊዜ አመልካቹ ሀረግ ነው፡፡

ምሳሌ (5) በዚህ ምሳሌ ውስጥ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚል ከዛበፊት ያልተደረገ ወይም ያልተከወነ ነገርን በዚያ ጊዜ፣ በዚያ ሰዓት እንጂ ቀድሞ/በፊት/ ያልተደረገ መሆኑንና የድርጊቱ

የተግባሩ/የግብሩ/ የመነሻ ዕለት /ሰዓት/ መሆኑን ባጭሩ አዲስ ክንውን/ መሆኑን/ ከዚያ ቀድሞ ያልተደረገ መሆኑን ለማስገንዘብ የገባ የጊዜ አመልካች ነው::

በምሳሌ (6) ውስጥ የገባው አያያዥ "አንዳንዴ" የሚል ሲሆን አልፎ አልፎ ወይም ዘወትር ያልሆነ መሆኑን የሚገልፅ ጊዜ ጠቀስ አያያዥ ነው:: አንዳንዴ ወይም አልፎ አልፎ የሚሆነውን /የሚደርሰውን/ ነገር የሚገልፅ ስለመሆኑ "የሚያማምሩት አለንጋ ጣቶቿ" እጁን ሲነኩት የሚሆነውን ሁኔታ ወይም የሚከናወነውና የማፈፀመው ክስተት "አንዳንዴ" መሆኑን በግልፅ ያሳያል:: በተጨማሪም ይህ ድርጊት እያሰለሰ የሚመጣ መሆኑን እንድንገነዘብ ያደረገን ጊዜ ጠቀስ አያያዥ ነው::

**ምሳሌ (7)**:- . . . ከሌሊቱ 12 ሰዓት <u>ገና</u> ፀሀይ ስታፈነጥቅ ደጃፋቸውን ከፍተው ዳዊታቸውን በጉያቸው ሸጉጠው . . . (የካቲ158/2)

**ምሳሌ (8)**:- . . . አብዛኛው ወጣት <u>በአሁኑ ሰዓት</u> የአውሮፓን እግር ኳስ ያያል በተለይ በአለፉት 5 አመታት በአውሮፓ የሚካሄዱትን የተለያዩ እግር ኳስ. . . (እናት 052/2)

**ምሳሌ (9)**:- . . . ስልጣኔ <u>በቅርብ</u> እየገባ ቢሆንም በእነሱ አካባቢ <u>አሁንም ቢሆን</u> አንዳንዴ ጠለፋና . . . (የካቲ 145/2)

**ምሳሌ (10)**:- . . . ወደ ስራቦታ ስትሄድ አገኘኋት:: አስቴርን <u>ከዚያ በፊት</u> አይቻት ስለማላውቅ ግርም አለኝና ጠራኋት . . . (የካቲ 144/2)

ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች በገቡበት ቅደም ተከተል መሠረት ለማዬት እንሞክር:-

በምሳሌ (7) ውስጥ "ከሌሊቱ" እና "ገና" የሚሉት ጊዜ አመልካቾች ናቸው:: በነዚህ ጊዜ ጠቀስ አመልካቾች የሚተላለፈው መልዕክት ከሌሊቱ በዚህ ጊዜ የሚልና ፀሀይ ስትፈነጥቅ ገና/ብቅ ስትል የሚል ከጊዜ ጋር ቁርኝት ያለውን ክንውን በግልፅ ያሳያል::

በምሳሌ (8) ደግሞ "በአሁኑ ሰዓት" የሚል ጊዜ አመልካች ይገኛል:: አብዛኛው ወጣት በዚህ ሰዓት እና ጊዜ እያደረገ ያለውን የሚገልፀው ጊዜ አመልካች አያያዥ እንዲሆን እንረዳለን::

በምሳሌ (9) በዚህ ምሳሌ ውስጥ ያሉት ጊዜ ጠቀስ አያያዦች "በቅርብ" "አሁንም ቢሆን " እና "አንዳንዴ" የሚሉት ናቸው:: የቀረበው ምሳሌ ስልጣኔ መቼ እንደገባ በመግለፅ በእነሱ አካባቢ ግን ዛሬም ቢሆን አልፎ አልፎ ጠለፋ እንዳለ ይገልፃል:: የስልጣኔው አገባብ ረጅም ጊዜ እንዳላስቆጠረና ከገባ በኋላም እስከዚህ ሰአት/ጊዜ/ ድረስ ጠለፋው እንዳልቆመና አልፎ አልፎ እንደሚከሰት ይገልፃል ይህን ሁኔታ የተገነዘብነው "በቅርብ፣ አሁንምና አንዳንዴ" ከሚሉት ጊዜ ጠቀስ አያያዦች ነው::

ምሳሌ (10) . . . በዚህ ምሳሌ ደግሞ “ከዚያ በፊት” የሚል ጊዜ ጠቀስ አያያዥ አለ:: ይህ “ከዚያ በፊት” የሚለው አያያዥ አስቴርን አይቷት እንደማያውቅ ለመግለፅ ከዚያ ቀደም /ቀድሞ/ ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ አገኘኋት ወይም አየኋት የሚል ሀሳብ ያለው ነው:: አለማዬቱንም ሆነ አለማግኘቱን ለመግለፅ የተጠቀመበትን ጊዜ ጠቀስ አያያዥ “መቼ?” ብለን ስንጠይቅ መልስ ሆኖ እናገኘዋለን::

አራቱን ምሳሌዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ከጊዜ ቅርበት፣ ርቀት፣ ገና መሆን ወይም ወዲያውኑ፣ መከወን አንዳር አንዳንዴ/ አልፎ አልፎ/፣ አሁንም /በአሁኑ ሰዓት/ ቀድሞ /ከዚያ በፊት/ ከሌሊቱ /በጠኋት በማታ/ በሚሉ ጊዜ ጠቀስ የሆኑ የጊዜ ቅደም ተከተልን የሚያሳዩና የሚያመለክቱ ምሳሌዎች ናቸው::

በምድብ “ሀ” ስር የታዩ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን የአጠቃቀም ስህተቶች በምሳሌ አስደግፈን ለማየት እንሞክር:: በጥናቱ አራሚዎች በስህተትነት ከተመዘገቡት የምድብ ሀ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መካከል የተወሰኑትን በማቅረብ ባሳዩት ጉድለት ላይ ትንተና ተደርጓል::

ምሳሌ (11) . . . እሷም ምንም ችግር የለም ብላ ተጠጋች:: ከዚያ በኋላ ወሬው ቀጠለ:: ከዚያ በኋላ አንድ ቀልድ ቢጤ ጣል ሳደርግላት የወተት አረፋ የመሳሰሉትን . . . (የካ 139)

ምሳሌ (12) . . . የምትማርበት ትምህርት ቤት ሊሴ ሲሆን አሁን በጣም ጎበዝና ታታሪ ልጅ ናት:: አሁን የ11ኛ ክፍል ተማሪ ናት:: የትምህርት ውጤቷም በጣም ጥሩ ነው:: (እናት 41)

ምሳሌ (13) . . . ቀን ከትምህርት ቤት መልስ ወደ ቤት ገብቶ መክሰስ ከበላ በኋላ ጓደኞቹን ጠርቶ ውሃ ከወንዝ በአህያ አንድ ላይ ካመጡ በኋላ ጀምበር ልትጠልቅ ስትል ወደ ጨፌ በሩጫ ሄደው ከብት ያመጣሉ . . . (እናት 70)

በምሳሌ (11) ውስጥ የቀረበውን አያያዥ አገባብ ስንመለከት አላስፈላጊ የሆነ ድግግሞሽ ታይቶበታል:: “ከዚያ በኋላ” በሚል የገባው አያያዥ ተደጋግሞ ባላስፈላጊ ቦታ በመግባቱ የአገባብ ስህተት ፈጥሯል:: ከአንድ ጊዜ በላይ ተደግሞ መግባት አልነበረበትም::

ምሳሌ (12)ን ስንመለከት ደግሞ “አሁን” የሚለው አያያዥ ሁለት ጊዜ ተደግሞ ገብቷል:: ይህ ድግግሞሽ አላስፈላጊ መሆኑን የምንረዳው አያያዡ በገባበት ቦታ የሰጠው አገልግሎት የለም::

በዚህ መሠረት በመጀመሪያ ላይ የገባው "አሁን" አላስፈላጊ ቦታ ላይ ገብቶ ጊዜዋን /ባለታሪኳ/ ያለችበትን ሁኔታ ለመግለፅ በመሞከሩ ሀሳቡን ወይም መልዕክቱን በማደነቃቀፍ አደብዝዞታል::

በምሳሌ (13)ም የታየው ይኸው ነው:: ድግግሞሹን በማስቀረት ሀሳቦቹን እርስ በርስ ማያያዝ ይቻል ነበር:: በተለይ በሁለተኛ ላይ የገባው "በኋላ" አላስፈላጊ ነው::

ይህን ሃሳብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በዚሁ ምድብ ስር እንደስህተት የተቆጠሩ ምሳሌዎችን እንጨምር:-

**ምሳሌ (14)** . . . 10ኛ ክፍል ላይ ግን በጣም ቀነሰች ማትሪክ እንኳን ልታልፍ ቀርቶ አሁን 2ተኛ ዓመት ሞያ በመማር ላይ ትገኛለች . . . (ከፍ 002)

**ምሳሌ (15)** . . . የዚህም አዳራሽ ዋና አላማው አሁን በቅርብ ጊዜ ሳለፈው የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዝግጅት . . . (እናት 51)

በምሳሌ (14) የቀረበውን ሀሳብ ስንመለከት መልእክቱን በትክክል ለማስተላለፍ የአቀራረብ ችግር አለበት:: ያም ሆኖ ከጊዜ ጠቀስ አያያዥ አጠቃቀሙ አንፃር ስንመለከት በቀዳሚው አረፍተ ነገር የተነሳው /እየተወሳ/ ያለው ያለፈ ታሪክ በወጉ አልተቋጨም:: በተከታዩ አረፍተ ነገር ሀሳብ መነሻ ላይ የገባው አያያዥ ጊዜ ከማመልከት አኳያ በቀዳሚው
አረፍተ ነገርና በተከታዩ አረፍተ ነገር ሀሳብ መካከል ሆኖ ሊፈፅመው የሚገባውን ሥራ በትክክል ለመወጣት አልቻለም:: የሀሳብ ፍሰቱ የራሱ የሆነ ችግር ስላለበት ሀሳቡ ከጊዜ ቅደም ተከተል ጋር በግልፅ ለማሳየት እንቅፋት ገጥሞታል::

ምሳሌ (14) በዚህ ምሳሌ ውስጥ ጊዜ ጠቀስ አመልካቾቹ አሁን፣ በቅርብ ጊዜ የሚሉት ናቸው:: በዚህ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተከታትለው በመግባታቸው በሀሳብ ፍሰቱ ላይ የራሳቸውን ተፅእኖ አሳድረዋል:: አያያዦች ያለ ቦታቸው ሲገቡ የሚያስከትሉት ችግር እንደሚኖር ከዚህ ምሳሌ መገንዘብ እንችላለን:: "አሁን" የሚለው አያያዥ ተደርቦ መግባቱ ጊዜው ካለፈ በጣም ቅርብ እንደሆነ አድርጎ የሚገልፅ ይምሰለን እንጂ ተደራርቦ መግባቱ አላስፈላጊ ነው:: በመሆኑም አሁን የሚለው ጊዜ ጠቀስ አያያዥ በዚህ ምሳሌ ውስጥ ተደርቦ መግባቱ እንደስህተት ሊቆጠር ችሏል::

ማጠቃለያ 1:- የምድብ "ሀ" የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም

| ምድብ | ትምህርት ቤቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግል ት/ቤት | | | | | | የመንግስት ትምህርት ቤት | | | | | | የግልና የመንግስት ት/ቤቶች | | | | | |
| | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ሀ | 192 | 84.96 | 34 | 15.04 | 226 | 100 | 258 | 93.82 | 17 | 6.18 | 275 | 100 | 450 | 89.82 | 51 | 10.82 | 51 | 100 |

መግለጫ

1. ተገቢ አጠቃቀም
2. ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም
3. ድምር

ከዚህ ቀጥሎ በምድብ "ለ" ስር የተካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ከተማሪዎች አላማ አንፃር በምድቡ ንዑስ ክፍሎች ተካተው ቀርበዋል::

### 4.2.2 ምድብ "ለ" የፀሐፊው የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሃረጋት

በምድብ "ለ" የፀሀፊውን የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ለፅሁፍ አደረጃጀት ስልት ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር በተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ተገቢ አጠቃቀም ያላቸውንና በሶስቱ አራሚዎች የጋራ ስምምነት የተደረሰባቸውን ምሳሌዎች ከዚህ በታች ለማዬት ተሞክሯል አያያገሮቹ ለፅሁፍ አደጃጀት ካላቸው አስተዋፅኦ አንፃርም ትንተናው ተካሂዷል:: (አባሪ 9ን ይመለከቷል)

በምድቡ ስር በምሳሌነት የተጠቀሱ አያያዥ ቃላትና ሃረጋት (ለምሳሌ፣ ለማጠቃለል ያህል፣ ይህም ማለት፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ፣ ለአጭሩ . . . ወዘተ) የመሳሰሉት ናቸው:: በምድብ "ለ" ስር የሚካተቱት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ቀደም ሲል በምድብ "ሀ" እንደተጠቀሱት አያያገሮች ሁሉ የዘገባው አካል ሳይሆኑ አንድ ፀሀፊ በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙትን ዓረፍተ ነገሮች አገልግሎት /Function/ አንባቢው እንዲረዳቸው ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ውጫዊ ተግባርን የሚያከናውኑ አያያገሮች ናቸው:: በአይነታቸው መለያዬት የተነሳም በስምንት ንዑስ ክፍሎች

ተከፋፍለዋል:: እነዚህን የምድብ "ለ" ስምንት ንዑስ ክፍሎች ከዚህ በታች ባላቸው ቅደም ተከተል መሠረት በምሳሌዎች በማስደገፍ ተተንትነው ቀርበዋል::

#### 4.2.2.1 ክትትሎሽን አመልካች /Sequencing/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

በዚህ ንዑስ ክፍል የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት (በቅድሚያ፣ በአጠቃላይ፣ ቀጥሎ፣ በመጨረሻ . . . ወዘተ) የመሳሰሉ ናቸው:: ከቀረበው መረጃ የተሰበሰቡትን ቅደም ተከተል አመልካቾች በተለያዩ ምሳሌዎች በመታገዝ ለመተንተን እንሞክር:-

**ምሳሌ (16)** . . . የመጀመሪያ ዲግሪዋን ያዘች ከትንሽ ጊዜ በኋላ በአንድ የግል ባንክ ውስጥ የ1800 ብር ደሞዝተኛ በመሆን ተቀጠረች:: በመቀጠልም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው ክፍል እየተማረች . . . (እናት 055/01)

**ምሳሌ (17)** . . . ከቤት እንስሳት ድመት እወዳለሁ ጨዋታቸው፣ ቁጣቸው፣ በአጠቃላይ ሥራቸው ሁሉ ያስደስተኛል:: ... (ኮከብ 094/01)

**ምሳሌ (18)** . . . ዝም ብለን ቁመቱን ስንመለከት መካከለኛ የወንድ ቁመና አለው በመጠኑም ቢሆን ውበቱን የቀነሱ ነገሮች ከተክለ ሰውነቱ በሙሉ ስንፈልግ የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ፀጉሩ ይሆናል . . . (ኮከብ 102)

**ምሳሌ (19)** . . . መንገድ ያለመሰራት የውሃ በተፈለገ ጊዜና ሁኔታ ያለመገኘት እናም ስንቱ ይነገራል ብቻ በአጠቃላይ በኑሮ ዝቅተኛ ማህበረሰብ ሁሉ እኛ ሰፈር ተለቅመው ተሰብስበው የሚኖሩ ይመስላል . . . (ክፍ 027/02)

**ምሳሌ (20)** . . . አጠገቤ አንድ ጠና ያለ ሰውዬ መጥተው ተቀመጡ:: ሰውየው ጠየም ያሉ ሆነው ቢማም ናቸው:: አውቶቡሷ በሚቀጥለው ፌርማታ ላይ ቆማ አዳዲስ ተሳፋሪዎችን ታስገባለች:: የሚወርድ ግን የለም. . . (የካ 157)

በምሳሌ (16) ውስጥ በቀዳሚው አረፍተ ነገር የቀረበው ሀሳብ የባንክ ሰራተኛ ሆና መቀጠሯና በተከታዩ አረፍተ ነገር ውስጥ ደግሞ ለሌላ እድገት /መሻሻል/ የሚያበቃትን ትምህርት መቀጠሏን ይገልፃል:: ይህም በቅድሚያ ካከናወነቻቸው ከተጨማሪ ሌላ ተከታይ ወይም ቀጣይ ድርጊት እየፈፀመች መሆኑንና ከነበረው ነገር በመነሳት የሚደረግ ቀጣይ ክንውን መሆኑን ያብራራል:: ስለዚህም ይህ አያያዥ ተከታይ የሆነ አካሄድ እንዳለ ያመለክታል::

በምሳሌ (17) ውስጥ ተከታትለው የተጠቀሱት ወይም የቀረቡት ሀሳቦች በቀዳሚው አረፍተ ነገር ውስጥ የተደረደሩና የተገለፁ ናቸው:: እነዚህን ለመሰብሰብና ለማጠቃለል የገባው አያያዥ ሰብሰብ ወይም ጠቅለል አድርጎ ለመቋጨት ሞክሯል:: ወይም አግዟል ይህ ደግሞ የሀሳብ አደረጃጀትን በጉልህ ያሳያል::

በምሳሌ (18) ደግሞ የባለታሪኩ ቁመናና ተክለ ሰውነት በቀዳሚው አረፍተ ነገር ከገለፀልን በኋላ በመጠኑም ቢሆን ውበቱን ከቀነሱት ነገሮች መካከል ቀዳሚውንና የመጀመሪያ ያለውን በተከታዩ ሀሳብ ውስጥ ግልፅ ያደርግልናል:: ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው በውበት ዙሪያ የሚነሱ የተለያዩ ነጥቦችን በደረጃ ከማቅረብ አኳያ የተነሳውን ሀሳብ ለማደራጀት ቀዳሚና ተከታይ . . . እያልን ሀሳብን ለማደራጀት እንደምንችል እንገነዘባለን::

በምሳሌ (19) እንደችግር የተነሱ የተለያዩ ነጥቦች ተዘርዝረዋል:: ከብዛታቸው የተነሳም ስንቱ ይነገራል ብሎ ካለ በኋላ በአጠቃላይ የችግሩን ተጠቂዎች የኑሮ ሁኔታ መሠረት በማድረግ አሰፋፈራቸው ላይ የራሱን አስተያየት ሰጥቷል:: ፀሀፊው ያነሳቸውን የተለያዩ ነጥቦች ሰብሰብ አድርጎ በማጠቃለልና ካለው ሁኔታ ተነስቶ ሀሳቡን እንዲቋጭ በማድረግ አያያዥ ቃላት ያላቸውን ጠቀሜታ መገንዘብ ይቻላል::

ምሳሌ (20) የባለታሪኩን የአውቶቡስ ጉዞ ተቀዳሚው አረፍተ ነገር ተረድተናል:: በጉዞ ላይ ያለው አውቶቡስ ከፊት ለፊቱ ባሉት ፌርማታዎች በሙሉ አዳዲስ ተሳፋሪዎችን እንደሚጭንና የሚወርድ እንደሌለም ከቀዳሚው አረፍተ ነገር ተረድተናል:: በዚህ ምሳሌ ውስጥ የገባው "በሚቀጥለው" የሚለው አያያዥ ድርጊቱ ተከታይ እንደሆነና በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ተመሳሳይ ስራ ወይም ክንውን እንደሚኖርና እንደሚከናወን እንገነዘባለን::

ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የክንውኖችን ክትትሎሻዊ አካሄድ ለማሳየት አያያዦች የረዱ መሆናቸውን /በመቀጠልም በአጠቃላይ በመጀመሪያ በሚቀጥለው/ የሚሉት የድርጊት ክትትሎሹ ተጠየቃዊ የሆነ አካሄድ እንዲኖረው አግዘዋል:: አንድ አረፍተ ነገር ከሌላው አረፍተ ነገር ቀድሞ የመገኘቱ /የመምጣቱ/ ነገር እንዲሁ በዘፈቀደ መሆን የለበትም:: በተፈጥሮ ውስጥ ያለ ተጠየቃዊ አካሄድ ከቦታ አንፃር፣ ከጊዜ አኳያ የምክንያትና የውጤት ቅደም ተከተል መጀመሪያና ቀጣይ እያለ የሚሄድ እንደሆነ (Trimble, 1985:52-54) ይገልፃሉ:: በፅሁፍ አደረጃጀት ውስጥ አመልካቾች አስፈላጊዎች ናቸው:: በመሆኑም ከአጠቃቀም አንፃር ተገቢ ቦታቸውን መያዝ እንዳለባቸው እንገነዘባለን::

### 4.2.2.2 በድጋሚ መግለፅ /Re-expressing/

ይህ በምድብ "ለ" ስር በንዑስ ክፍልነት የሚገኘው "ሀሳብን በድጋሚ" ለመግለፅ የሚረዱ /የሚያግዙ/ አያያዦች የተካተቱበት ንዑስ ምድብ በፅሁፍ አደረጃጀት ረገድ ያለውን ጠቀሜታ ለማዬት ይረዳን ዘንድ ከተጠኚዎች ድርሰት የተወሰኑትን በምሳሌ እያነሳን እንመለከታለን::

በንዑስ ምድቡ ስር ይጠቃለላሉ ብለው ምሁራኑ እንዳምሳሌ ያቀረባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በሌላ አነጋር፣ ይህም ማለት፣ ታዲያ፣ መቼም . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ከዚህ በታች በሁሉም አራሚዎች ስምምነት ካገኙት መረጃዎች መካከል የ"በድጋሚ መግለፅ" ምሳሌዎችን በማቅረብ ለመተንተን ተሞክሯል::

ምሳሌ (21) . . . እኔ ወይም በአካባቢዬ የምንኖር ሰዎች በጣም ነው የምንደሰተው <u>በሌላ አነጋገር</u> ከመኪናና ከሰዎች ጫጫታ ፍፁም የራቀ ሲሆን በዚህ አጋጣሚ ንፁህ አየርንም . . . (ኮከብ 98/2)

ምሳሌ (22) . . . ከተለያየ ሰፈር የመጡ ሸማቾች ሲከራከሩ ይስተዋላሉ:: በዚያው ልክ ጫጫታው አጭበርባሪው፣ ቀማኛው፣ በስፋት ይስተዋላል በተለይ አንዳንዶቹ የሰዎችን ዘንቢል እና ኪስ ሲፈትሹ መመልከት አዲስ አይደለም ዳር ሆኖ ለሚያስተውል አንድ አስገራሚ የህንድ ፊልም የመመልከት ያህል ነው:: መቼም በአል ሲመጣ ሀብታሙም ሆነ ደሀው የአቅሙን ያህል ወደ ገበያ በመውጣት ሲሸምት መመለከት አዲስ ነገር አይሆንም. . . (ኮከብ 106/01)

ምሳሌ (23) . . . ስለመርካቶ "ይህን ያህል ካልኳችሁ አይቀር" በዚህ ግዙፍ የገበያ ማዕከል ብዙ አስደናቂ ነገሮች አሉ:: <u>ከነዚህም</u> አንዳንዶቹ የስም አወጣጥ ዘይቤ ምጣም ያስደንቀኛል:: ለምሳሌ ሱማሌ ተራ፣ ምናለሽ ተራ፣ ተራ . . . ተራ . . . (ከፍ 32)

በምሳሌ (21) ውስጥ ነዋሪዎቹ የሚደሰቱበትና የሚረኩበት ነገር በቀዳሚው አረፍተ ነገር ሃሳብ ተገልጿል:: ይህንኑ ቀዳሚ ሀሳብ በሌላ አገላለፅ ለማቅረብ ሞክሯል:: ለደስታው መገኘት ምክንያት የሆኑትን በመጠቆም ሀሳቡን በድጋሚ ለማቅረብ ችሏል::

በምሳሌ (22) ደግሞ የሸማቾችን የግብይት ሂደት ከቀማኛውና ከዘራፊው ሁኔታ ጋር በማስተያየት አቅርቦታል:: በዚህ ትዕይንት ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑትን ደግሞ በተለይ በበአል ሰሞን ያለውን ሁኔታ "መቼም" በሚል ለማቅረብ ይሞክሯል:: በዚህም አቅም ያለውም

የሌለውም በበአል ሰሞን ወደ ገበያ መውጣቱንና እንደፍላጎቱና እንደችሎታው የሚያደርገውን ተሳትፎና በቀዳሚዎቹ አረፍተ ነገሮች የተወሳውን ሀሳብ በመድገም አቅርቧል።

ምሳሌ (23) ባለታሪኩ "ስለመርካቶ ይህን ያህል ካልኳችሁ" በማለት የገበያ ማዕከሉን የተለያዩ አስደናቂ ነገሮች ከቀዳሚው አረፍተ ነገር ሀሳብ በመነሳት ደግሞ ለማቅረብ የተወሰኑትን በስም በመጥራት "ከነዚህም" አንዳንዶቹ በሚል በተከታዩ ሀረፍተ ነገር ሀሳብ ውስጥ ዝርዝራቸውን ለማቅረብ ሞክሯል። በዚህም ሀሳብን በድጋሚ ለመግለፅ የፅሁፍ መልዕክትን ማደራጀት እንደሚቻል ልንገነዘብ እንችላለን። ጌታቸው (1987:105) አንድ ዲስኩር አመልካች ለአንድ ተግባር ወይም ዝምድና ብቻ የተወከለ እንዳልሆነ ገልፀዋል። ከፍ ሲል በቀረበው ንዑስ ምድብ ስር ግልጋሎት ላይ የዋሉት አያያዦች ይህንኑ ተግባር ሲፈፅሙ ተስተውለዋል።

### 4.2.2.3 ነጥሎ ማመልከት (Specifying)

በዚህ "ነጥሎ ማመልከት" ንዑስ ምድብ ስር የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /እነዚህም፣ በስም ለመጥቀስ፣ ለምሳሌ፣ ከነዚህም መካከል . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው። በተሰበሰበው መረጃ አማካይነት "በዝርዝር መግለፅን" ለማስረዳትና ለመተንተን ይረዳ ዘንድ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት:-

**ምሳሌ (24)** . . . በዚሁ ሽሮ ሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ብዙ ነገሮች ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል በጣም ትልቁ የገበያ ማዕከል ይገኛል። የተለያዩ ለአይን የሚማርኩ . . . (የካ/60/02)

**ምሳሌ (25)** . . . እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ የበሽታ ዓይነቶች ቢኖሩም ከነዚህም አብላጫውን የሚይዙት በፆታም ግንኙነት የሚመጡ በሽታዎች ናቸው . . . (የካ135/01)

**ምሳሌ (26)** . . . ከጥቅማቸው ባሻገር አንዳንዴም እንደመጎረሪያም ማገልገል ከጀመሩ ውለው አድርዋል። . . . (እናት 046/1)

**ምሳሌ (27)** . . . አክሱም በውስጧ የተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የሆኑ ቅርሶች የያዘች ከተማ ናት። ከነዚህም ቅርሶች አንዱና ዋነኛው የአክሱም ሃውልት ነው። . . . (እናት 046/1)

**ምሳሌ (28)** . . . በቸርችል ጎዳና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲኖሩ ለአብነት ያህል ለመጥቀስ መንግስታዊ ከሆኑት መከላከያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ጥቁር አንበሳ ት/ቤት . . . (ከፍ/015/1)

ከፍ ሲል ከቀረቡት አምስት የተለያዩ ምሳሌዎች ለመረዳት የሚቻለው ሀሳብን ለይቶ ለመጠቆም /ለመግለፅ/ የሚረዱ አያያገሮችን መጠቀም እንደሚቻል ነው። እነዚህም እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

ምሳሌ (24) በዚህ ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሰው አያያዥ "ከነዚህም መካከል" የሚል ሲሆን በቀዳሚው ሀሳብ የተገለፁ በርካታና ተለይተው ከማይታወቁት ውስጥ /መካከል/ ለይቶ በማውጣት ለማቅረብ መቻሉን እናስታውላለን። በዚህ መሠረት በምሳሌ (25) ከሚገኙ ብዙ ነገሮች መካከል በጣም ትልቅ የገበያ ማዕከል መገኘቱን ከሌሎች ጋር በማስተያዬት ዝርዝር ሀሳብ ለመስጠት አስችሏል።

በምሳሌ (25) ደግሞ "ከነዚህም" የሚለው አያያዥ ቀድሞ ከተገለፀው ሀሳብ በመነሳት ከብዙ የበሽታ አይነቶች መካከል የተወሰኑት ብቻ የሚከሰቱት በዖታዊ ግንኙነት እንደሆነ ለይቶ በመጠቆም ያስረዳል። ይህንንም በቀረበው ምሳሌ መሠረት እጅግ በጣም ብዙ በሽታዎች መኖራቸውንና ከነዚህ ሁሉ የሚበልጥ መሆኑንና የሚስፋፋበትን መንገድ ሳይቀር በግልፅ ተጠቁሞ እናገኘዋለን። እዚህ ላይ ፅሁፍን ለማደራጀት ቀድመው የተነሱ ሀሳቦችን ይበልጥ ለይቶ በማመልከት ማቅረብና ማደራጀት መቻሉን ልናስተውል እንችላለን።

ምሳሌ (26) ከምሳሌው እንደምንረዳው ከጥቅማቸው ባሻገር ሌላ ነገርን አንዳንዴ/አልፎ አልፎ/ መገልገል እንደጀመሩ ያሳያል። "እንደመጎረሪያም" ይህ አባባል መደበኛውን የቋንቋ አጠቃቀም የተከተለ ባይሆንም በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ከተገለፀው ጥቅም ሌላ ጉራ/እንደመታያ/ እየተገለገሉበት እንደሆነና ይህንንም የሚጠቀሙበት አንዳንዴ እንደሆነ ይገልፅልናል። ይህን ለመጠቆም /ለመግለፅ/ የረዳው አያያገ መቼ እና እንዴት ባለ ሁኔታ የሚለውን ሀሳብ ለመመለስ በማስቻሉ ነው።

ምሳሌ (27) ይህም ምሳሌ ደግሞ ከተማዋ ከያዘቻቸው ቅርሶች ውስጥ ለይቶ ለማመልከትና ማንነቱ ለመጠቆም /ለመግለፅ/ ለመግለፅ "ከነዚህም" የሚለው አያያዥ ገብቷል። በከተማዋ ካሉት ውስጥ አንዱና ዋነኛው በማለት ለይቶ ለማሳየትና ስለማንነቱ ለመጠቆምና ለመዘርዘር "ከነዚህም ቅርሶች አንዱና ዋነኛው" በሚል ማንነቱን በግልፅ አስቀምጧል።

ምሳሌ (28) በዚህ ምሳሌ ደግሞ "ለአብነት ያህል ለመጥቀስ" የተፈለጉ ነገሮች መኖራቸውን ያሳያል ይህ ለአብነት ያህል "ለመጥቀስ" የሚሉት አያያገሮች ቀደም ሲል በጥቅል ከቀረቡት ውስጥ በግል ለይቶ በስም ለማቅረብ የሚረዱ ናቸው። በዚህ መሠረት የቀረበውን ምሳሌ ብንመለከት በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር በርካታ ድርጅቶች ሲኖሩ ከአያያገ ቀጥሎ የገባውን ሀሳብ በዝርዝር ለማስረዳትና ለመተንተን ያግዛል። ይኸውም በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ድርጅቶቹ

መንግስታዊ የሆኑ ወይም ያልሆኑ በስም ያልተጠቀሱ ናቸው፡፡ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር ግን ሊጠቀስ የተፈለገው መንግስታዊ ከሆኑት በመሆኑና ከነዚህም ለአብነት ያህል በሚል በስም ለመጥቀስ የተሞከረበት መሆኑን እናስታውሳለን፡፡ ይህም ሀሳብን በዝርዝር በመግለፅና በማቅረብ አንድን ፅሁፍ ማደራጀት እንደሚቻል ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

#### 4.2.2.4 ለይቶ ማመልከት (Referring)

በዚህ "ለይቶ ማመልከት" በሚል ንዑስ ምድብ ስር የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ይህን በማመልከት፣ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ ከዚህ በተለየ መንገድ፣ በተለይ . . ./ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

"ለይቶ ማመልከት"ን የሚያሳዩ አያያገሮችን ከተገኘው መረጃ አኳያ በተለያዩ ምሳሌዎች አማካይነት ለመተንተን እንሞክራለን፡-

**ምሳሌ (29)** . . . የተጨናነቀች ከተማ ናት በተለይ በአመት በዓል አካባቢ ታይተው በማይታወቁ አዳዲስ ልብሶች ያሸበረቁ ሱቆች አይንን ይማርካል. . . (እናት 050/1)

**ምሳሌ (30)** . . . የፊቷ ልስላሴ ጉንጯ ላይ ያለው ስርጉድ በጣም ሰውን እንድትስብ አድርጓታል፡፡ በተለይ ቁመናዋ ፣ ዳሌዋ፣ ቁመቷ እንዲሁም አጠቃላይ ቅርጿ ሰውን እንድትማርክ . . . (ከፍ 002/01)

**ምሳሌ (31)** . . . ከየት እንደሆነች እርስ በርስ እየተንሾካሾከ ይመለከታታል፡፡ በደንብ ለተመለከታት ሰው ወጣቷ ከደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም ከሐመር ብሔረሰብ እንደመጣች ይገምታል . . . (የካ146/01)

**ምሳሌ (32)** . . . የትምህርት ነገር በዛው ቀረ፡፡ ደና መልበስ፣ ማጌጥ፣ መኳኳል ሁኔታዋ ሁሉ ለየት አለ፡፡ ከቤተሰቦቿ ቁጥጥር ውጭ ሆነች፡፡ በተለይ ለወንዶች ልዩ ቦታ አላት እንደሷ የለበሰ ያማረ የሁል ጊዜ ምርጫዋ ሆነ . . . (እናት 042/1)

**ምሳሌ (33)** . . . ከጭቅጭቃቸው የተነሳ ይፈሯቸዋል፡፡ በተለይ የግቢው ተከራዮችማ አይጣል ያለባቸው መከራ . . . (ኮከብ 110/01)

ምሳሌ (29) በዚህ ምሳሌ የቀረበው አያያዥ "በተለይ" የተሰኘ ነው፡፡ አያያገሩን ቀድሞ የገባውን ሀሳብ ስንመለከት የከተማዋን መጨናነቅ እንረዳለን ከአያያገሩ ቀጥሎ የገባው ሀሳብ ታይቶ የማይታወቅ በሚል የቀረበ ሀሳብ አለ፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ከተማዋ የተጨናነቀች ብትሆንም እንኳ "በተለይ" ተብሎ ተለይቶ የተገለፀው በአመት በአል የሚታዬው ታይቶ የማይታወቅ

መጨናነቅ ነው:: በዚህ ንዑስ ምድብ ሀሳብን ለይቶ በማመልከት የፅሁፍ መልዕክት ማደራጀት እንደሚቻል ከቀረበው ምሳሌ እንረዳለን::

ምሳሌ (30) በቀዳሚው አረፍተ ነገር የተነሰው ውበት እንዳለ ሆኖ በተከታዩ አረፍተ ነገር ውስጥ ለተጠቆመው ቁመና እና ቅርፅ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ “በተለይ” በሚል ለመግለፅ ሞክሯል:: በመሆኑም ለይቶ ለማሳየት የሞከረውና ትኩረት የሰጠው የልጅቷን ተክለ ሰውነት ይህም ሰውን እንድትማርክ የረዳት መሆኑን በምሳሌ አቀራረብ እንረዳለን::

ምሳሌ (31) በቀዳሚው አረፍተ ነገር የልጅቷን ማንነት ከየት እንደመጣችና ከየት እንደሆነች ተመልካቹ እየተንሾካሾከ እርስ በርስ መጠያየቁን በተከታዩ አረፍተ ነገር ደግሞ በደንብ ለተመለከታት ከደቡብ “በተለይም” ብሎ የተገኘችበትን በመግለፅ ለማመልከት ሞክሯል:: በዚህ ንዑስ ምድብ ሀሳብን በማደራጀት የፅሁፍን መልዕክት ለይቶ ለተደራሲው ለማቅረብ መቻሉን እንደመለከታለን::

በምሳሌ (32) የባለታሪኳን ትምህርት ማቋረጥ ከቤተሰብ ቁጥጥር መውጣት፣ የሁኔታዋን መለያየት በቀዳሚው አረፍተ ነገር ሀሳብ ውስጥ ተረድተናል:: በተከታዩ አረፍተ ነገር “በተለይ” ተብሎ የተገለፀው ትኩረት የምትሰጠውና የዘወትር ምርጫዋ የሆነውን ፍላጎትና ስሜት በግልፅ አስፍሮልናል:: በዚህ አያያዥ ተለይቶ ሊጠቆምና ሊቀርብ የተፈለገው ሃሳብ ግልፅ ነው:: ይህን ደግሞ ማድረግ የተቻለው “ለይቶ ማመልከት”ን የሚያስችል አያያዥ በመጠቀሙ ነው::

በምሳሌ (33) ሰውዬው ጨቅጫቃ በመሆናቸው ይፈራሉ:: ከሁሉም በላይ የጊቢው ተከራዮች በተለየ ሁኔታ ችግር እንዳለባቸው ያስረዳሉ:: “በተለይ” ሲል ለይቶ የሚያሳየው የጊቢውን ተከራዮች ነው:: ስለዚህ ይህ በተለይ የሚለው አያያዥ የችግሩን ባለቤቶች በግልፅ ለማሳዩትና ለመለዬት አስችሏል::

እነዚህ ከላይ በየምሳሌዎቹ ውስጥ የተጠቀሱት አያያዦች ብቻ ሳይሆኑ በዚህ ለይቶ በማመልከት ረገድ የሚያገለግሉና ጥቅም ላይ የሚውሉ በርካታ አያያዦች እንዳሉ ከመረጃው ለመረዳት ተችሏል::

### 4.2.2.5 በድጋሚ ማንሳት (Resuming)

በድጋሚ ማንሳት በሚል ንዑስ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ቀደም ሲል ወደተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ፣ በድጋሚ ለማስታወስ፣ ለመሆኑ፣ ታዲያ፣ በነገራችን ላይ . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ከተሰበሰበው መርጃ ውስጥ በወጡ የተለያዩ ምሳሌዎች አማካይነት “በድጋሚ ማንሳት”ን እንመልከት::

ምሳሌ (34) . . . የስሙ አወጣጥ ዘይቤው በጣም ያስደንቀኛል ለምሳሌ ሱማሌ ተራ፣ ምናለሽ ተራ፣ ቦንብ ተራ፣ ተራ ተራ እያሉ የሚያወጡት ስም ይደንቀኛል ለመሆኑ ተራ ተራ እያሉ የሚያወጡት ስም ለምን ይሆን? . . . (ከፍተ 032/2)

ምሳሌ (35) . . . ብዙ ሰዎችን የሚያስተናግድ ግዙፍ የገበያ ማዕከል ነው:: ታዲያ ስለመርካቶ ይህን ያህል ካልኳችሁ አይቀር በዚህ ግዙፍ ገበያ . . . (ከፍተ032/2)

ምሳሌ (36) . . . በመንግስት ብዙ ነገር እየተሰራ ይገኛል:: አዳዲስ ፎቆችን ፣ መፅሐፎችን፣ ወንበሮችን እና የተለያዩ ለተማሪዎች የሚጠቅሙ ነገሮች እየተደረጉ እና ተማሪዎችም ይህንን ተግባር በማየት በትምህርታቸው ብዙ ለውጥ እያመጡ ይገኛሉ:: እናም ያ ሁሉ እንዳልነበረ አሁን ዘመን ተቀይሮ ዘመን ሲለወጥ አዲስ ነገር ማየት እየጀመርን . . . (የካ 130/02)

ከላይ በቀረቡት ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ በድጋሚ ማንሳት በፅሁፍ አደረጃጀት ረገድ ያለውን ፋይዳ ለመረዳት የሚከተለውን ትንታኔ እንመልከት:-

በምሳሌ (34) "ለመሆኑ" ከሚለው አያያዥ ቀድሞ የገባውን ሀሳብ ስንመለከት የስም አወጣጡ ይደንቀኛል የተባለለትን የስም አወጣጥ እናስተወላለን:: ከአያያዥ ቃሉ ተከትሎ የገባውን ሀሳብ ስንመለከት ደግሞ ያንኑ ሀሳብ ደግሞ የሚያነሳና በጥያቄ የሚደመድም ሆኖ እናገኘዋለን::

በምሳሌ (35) በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ውስጥ ብዙ ሰዎችን የሚያስተናግድ ግዙፍ የገበያ ማዕከል እንደሆነ ተገልጿል:: ይህነኑ ሀሳብ "ታዲያ" በሚል አያያዥ የቀጣዩ ዓረፍተ ነገር ሀሳብ ለማደራጀት የቀደመው ሀሳብ ደግሞ "ይህን ያህል ካልኳችሁ አይቀር" በሚል የተቋረጠውን ሀሳብ በድጋሚ በማንሳት ለማቅረብ ተሞክሯል::

በምሳሌ (36) ደግሞ ከአያያዡ ቃል ቀድመው በገቡ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያለው ሀሳብ መንግስት በትምህርት ቤቶች ዙሪያ እያደረገ ያለውን ግንባታ እና የመማሪያ ቁሳቁሶች የማሟላት ሂደት ተማሪዎችን ለለውጥ እንዳነሳሳ ይገልፃል:: በተከታዩ አረፍተ ነገር ሃሳብ ባለፉት ዘመናት የነበረውን ሁኔታ በማንሳት ያ ሁሉ ተቀይሮ ዛሬ አዲስ ነገር መኖሩ "እናም" በሚለው አያያዥ የቀዳሚው ዘመን አንስቶ አሁን አንስቶ ያለውንና አሁን የተገኘውን ለውጥ ይጠቁማል::

በዚህም ሆነ ቀደም ሲል በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት የተቋረጠን ሀሳብ በድጋሚ በማንሳት ሀሳብን ማቅረብና የፅሁፍን ሃሳብ ማደራጀት እንደሚቻል እንረዳለን::

### 4.2.2.6 ምሳሌ መስጠት (Exemplifying)

ምሳሌ በመስጠት የፅሁፍ አደረጃጀትን የበለጠ ግልፅና የተብራራ እንደሆን ማድረግ ይቻላል:: በዚህ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ይህንን በይበልጥ ለመግለፅ፣ ለምሳሌ፣ ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: በተሰበሰቡት መረጃዎች አማካይነት በዚህ ንዑስ ምድብ ስር የቀረበውን ሀሳብ ለመተንተን ለማብራራት እንዲችል የተወሰኑ ምሳሌዎች በማንሳት ለማየት እንሞክራለን:-

**ምሳሌ (37)** . . . በሚሸጡ እቃዎች የተሰየሙ ናቸው:: ለምሳሌ ጫትተራ፣ ጨውተራ፣ ሸራተራ፣ ሚሊተሪ ተራ፣ . . . ወዘተ (እናት 066/2)

**ምሳሌ (38)** . . . የመዝናኛ ክበብ ያለው ትምህርት ቤት ነው:: ለምሳሌ በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚታዩት ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው የተማሪዎች . . . (እናት 060/02)

**ምሳሌ (39)** . . . የልማት ነገሮች ይከናወናሉ:: ለምሳሌ ከቤት ውስጥ (ቤት ሲሰራ) የተቆለሉ አፈሮችን ማንሳት፣ ትምህርት ቤቶችን ማስፋፋት፣ አትክልቶችን መትከል . . . (ኮከብ 095/1)

ምሳሌ (37) በምሳሌው ውስጥ ካለው አያያዥ ቀድሞ የገባው ሀሳብ በሚሸጡ እቃዎች ላይ የተሰየሙ ስያሜዎች መኖራቸውን ሲገልፅ በውል እነማን እንደሆኑ አያስረዳም ነገር ግን ይህ ስያሜ በየትኞቹ እቃዎች የተሰየመ እንደሆነ የምንረዳው በምሳሌነት ከተጠቀሱትና በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ ላይ ነው:: ስለዚህ እነማን እንደሆኑና ምን ተብለው እንደሚጠሩ በምሳሌው ስር በግልፅ ሰፍረዋል:: በዚህ መሠረት ምሳሌ በመስጠት ሀሳብ በመግለፅና በማብራራት ፅሁፍን ማደራጀት ይቻላል::

ምሳሌ (38) እና (39) ስንመለከት ደግሞ በምሳሌ (38) በትምህርት ቤቱ ውስጥ እንደምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮችን በሁለተኛው /በተከታዩ/ ዓረፍተ ነገር በምሳሌ ሊቀርቡ ችለዋል:: በምሳሌ (39) ደግሞ የልማትን መከናወን በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ተገልጿል:: ይህንኑ አስመልክቶ በምሳሌ የተገለፀውንና የተብራራውን እንመለከታለን::

ከዚህ በላይ የቀረቡት ምሳሌ በመስጠት ሀሳብን ማደራጀትና ማብራራትን የሚያስችሉ አያያዦች በቀዳሚውና በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መካከል በመግባት ቀድሞ የተነሳውን ሀሳብ በምሳሌና በማብራሪያ አስደግፎ ማቅረብ እንደሚቻል ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል:: የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን ቀጥለን እንመልከት:-

ምሳሌ (40) . . . ዝግጅታቸውን ለማቅረብ ለሚፈልጉ ክፍት ነው . . . ለምሳሌ እንደባለፈው ቢዮንሴ መጥታ እንዳዘጋጀቸው ኮንሰርት ለተለያዩ ነገሮች አስተዋፅኦ ያደርጋል . . . (ከፍት 003/01)

ምሳሌ (41) . . . እርምጃ መውሰድ አለባቸው:: ለምሳሌ ወንበሮችን በመጨመር የሰው ኃይል ማዳበር . . . (እናት 060/1)

ምሳሌ (42) . . . ይህን እያባባሱት ይገኛሉ:: ለምሳሌ የአባላዘር በሽታ ኤድስን ለማስፋፋት እንደመንስኤ . . . (የካቲ 135/01)

ምሳሌ (40) ቀድሞ የተነሳው ሀሳብ እንዳለ ሆኖ "ለምሳሌ" የሚለው አያያዥ የገለፀው እንደባለፈው እንደቢዮንሴ ዝግጅት ሌሎች የተለያዩ ነገሮች አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ነው:: ስለዚህ ለቀዳሚው ሀሳብ ድጋፍ ለመስጠት የገባው ምሳሌ በግልፅ አሳይቷል::

ምሳሌ (41) ማድረግ /መውሰድ/ አለባቸው የተባለው እርምጃ ምን መሆን እንዳለበትና ምን እንደሆነ በምሳሌው ውስጥ በዝርዝር ተቀምጧል:: ይህንንም ለምሳሌ "ወንበሮችን በመጨመር፣ የሰው ኃይል በማዳበር . . ." እያለ የሚቀጥል እንደሆነ እንገነዘባለን:: ምሳሌ በመስጠት የፅሁፍ አደጃጀትን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ረድቷል::

ምሳሌ (42) የሚያባብሱት ነገሮች እያባባሱ እንደሆነ ቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ይነግረናል በተከታዩ ዓረፍተ ነገር ግን አባባሾቹ ማን ማን እንደሆነ ለምሳሌ በሚል ሠፍረዋል:: የዋናውን ሀሳብ መልዕክት ግልፅ በሚያደርጉና በሚያብራሩ ምሳሌዎች በመታገዝ ፅሁፍን ማደራጀት ይቻላል::

ከፍ ሲል በተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደመለከትነው በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ለተነሱት ሀሳቦች ማብራሪያና ምሳሌ በመስጠት ዝርዝር ሀሳብን በግልፅ እንድናገኝ ያደርገናል:: ምሳሌ በሚል የቀረበትን ስንመለከት ከቀዳሚው ሀሳብ በመነሳት ሀሳቡን ግልፅ ለማድረግ ሲባል ምሳሌ የተሰጠባቸው ናቸው::

#### 4.2.2.7 ማጠቃለያ (Summarizing)

በዚህ "ማጠቃለያ" (Summarizing) በሚል ንዑስ ምድብ ስር የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት (ለማጠቃለል፣ በአጭሩ፣ ለመቋጨት . . .) የመሳሰሉት ናቸው::

ምሳሌ (43) . . . ሰውን ቶሎ የምትረዳ ልጅ ስትሆን እኔም በዚህ ውበቷ እንድደነቅባት ተገድጃለሁ:: በአጠቃላይ ሂሩት ሰዎች ሁሉ የተማረኩላት አማላይና ቀምበጥ የሆነች ልጅ ናት (ከፍት 014/2)

ምሳሌ (44) . . . በሰአቱ ትምህርት ቤት መገኘቷ፤ አስተማሪዋን ማክበሩ፤ ስለማንም ሰው አስተያደት አለመስጠቷ የሚያስደስት ባህሪዋ ነው። ባጠቃላይ ስርዓቷና ለትምህርት ትኩረት መስጠቷ በጣም እንድወዳትና የበለጠ እንድቀርባት . . . (እናት 062/01)

ምሳሌ (45) . . . አለማስረዳት፣ ተማሪዎችን አለማሳተፍ፤ በጥቂቱ ብቋጨው ችግሩን ለመፍታት ምን ማድረግ እንደሚገባን . . . (ኮከብ 113/02)

ከዚህ በላይ የቀረቡትን ሦስት የተለያዩ ምሳሌዎች እንዳቀማመጣቸው ቅደም ተከተል በዝርዝር ለማዬት እንሞክር፡-

በምሳሌ (43) የቀረበው ሀሳብ በቀዳሚው ክፍል አድናቂው ሊያደንቅ የተገደደበትን ምክንያት ሲዘረዝር የቆዬ በመሆኑ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር የአድናቆቱን ሁሉ ማጠቃለያ የገለፀበት ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንንም ሲገልፅ እሱ ብቻ ሳይሆን ሰው ሁሉ ለማድነቅ የተገደደበትንና የተማረከበትን ጉዳይ በግልፅ አስቀምጧል። ይህንንም "በአጠቃላይ" በሚል የሀሳብ ማደራጃና ማጠናቀቂያ አያያዥ ሀሳቡን ወደፍፃሜ ሊያደርስ የሞከረበትንና እንዲያደንቅ የተገደደበትን ሁሉ በዝርዝር ገለፃ የደመደመበት ነው።

ምሳሌ (44) ስንመለከት በቀዳሚው አረፍተ ነገር ብዙ የተባሉ ሀሳቦች መኖራቸውን ብንገምትም ከነዚህ ከተገለፁት ውስጥ አንዱ የሚያስደስተው "ባህሪዋ" እንደሆነ ያስረዳል። እዚህ ላይ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ሲባሉ የቆዩትን ሁሉ ስብስብ አድርጎ ማጠቃለያ ለመስጠት ባጠቃላይ በሚል አያያዥ ጎላ ጎላ ያሉ ተጨማሪና አዳዲስ እንዲሁም ሲዘረዝር ከቆዬው ይበልጥ ዋና ዋና ነው ያለውን በማጠቃለያው መልሶ በመድገም ሀሳቡን ለመቋጨትና ለመደምደም ይሞክራል።

በምሳሌ (44)ትም ሆነ ከፍ ሲል በቀረበው ምሳሌ ውስጥ እንደተገነዘብነው ጉዳዮች ተነስተው ወደ መደምደሚያቸው ሲደርሱ ማጠቃለያ ሀሳቡ ቀደም ሲል ሲገለፁ ከነበሩት ዝርዝር ሀሳቦች ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ሀሳቦች በመጭመቅ መቋጨት ይቻላል። በዚህ ጊዜ ግን ሀሳቡ መጠቃለሉን የሚያመለክቱ አያያዦችን በመጠቀም ሀሳብን መቋጨት እንደሚቻል ከቀረቡት ምሳሌዎች ልንረዳ እንችላለን።

ምሳሌ (45) በዚህ ምሳሌ ቀዳሚ ክፍል "አለማስረዳት፣ አለማሳተፍ" እያለ ሲደረደር የቆዬን ሀሳብ ለመደምደምና መፍትሄ ለመፈለግ በሁለቱ ክፍሎች ማለትም በቀዳሚው ዓረፍተ ነገርና በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መካከል የገባው አያያዥ እልባት ለመስጠትና ለመደምደም ሲደረደሩ የነበሩ ችግሮችን ወይም ጉድለቶችን እንዳሉ አምኖ ተቀብሎ ወደ መፍትሄው ለመሄድና

በመፍትሄውም አፈላለግ ላይ ምን መደረግ እንዳለበት ለመግለፅ ችግሩን ቀድሞ ሲቀበል “በጥቂቱ ብንቋጨው” መፍትሄ ብንሻ በሚል የጀመረ ይመስላል::

እዚህ ላይም ወደማጠቃለያ ወይም ወደ መቋጫ ሀሳብ ከመሄድ በፊት ሊነሱ የሚገቡ መነሻ ሀሶቦች በተለያዩ መልክና ሁኔታ ሊቀርቡ እንደሚችሉና በመጨረሻው ወደ መደምደሚያ /ወደማጠቃለያ/ ሊደርስ የሚችል መሆኑን እንረዳለን:: በዚህ የፅሁፍ አደረጃጀት ስልት ውስጥ ማጠቃለያ የራሱ ቦታና ስፍራ አለው ማለት ነው::

ይህን ንዑስ ምድብ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ሌላ ምሳሌ በተጨማሪነት ለማዬት እንሞክር:-

ምሳሌ (46) . . . የቤቶችን መደዳ ይዘን ስንጓዝ ከመደዳዎቹ ቤቶች አምስተኛ ው በር የኛ ቤት ነው:: ደግሞ ድንገር ለሚለው ሰው ተጨማሪ ማስረጃ የምትሆን ከበራችን ቀጥሎ ከአጥር ጋር የተያያዘች እንዳትነቃነቂ ተብላ ማስጠንቀቂያ የደረሳት የምትመስል አንዲት ብቸኛ ኮባ አለች:: በአጭሩ የቀኝ አቅጣጫውን ይዘው ትንሽ ይጓዙ ብለን ብንዘጋ ይቀለናል . . . (የካ 140/01)

ምሳሌ (46) በዝርዝር ሲገለፅ የቆዬው ሰፋ ያለ ሀሳብ በመጨረሻው ዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ በመግባትና ጠቅለል በማድረግ “በአጭሩ” በሚል አያያዥ ሀሳቡን ለመቋጨት ወይም ለማጠቃለል ሲሞክር ተስተውሏል::

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች እንደተመለከትነው የማጠቃለያ ሀሳብ ለመሰንዘርና ለመቋጨት ሲፈለግ ሲዘረዘሩ የቆዩ ሀሳቦችን ለመደምደም የሚያግዙ አያያዦችን መጠቀም ይገባል:: በዝርዝርና በስፋት ሲገለፅ የነበረን ሀሳብ ሰብሰብ አድርጎ እልባት ለመስጠት /ለመቋጨት/ ሲፈለግ ተገቢ የሆኑና ለማጠቃለል የሚያስችሉ አያያዦችን ለይተን ልንገለገልባቸው ይገባል::

#### 4.2.2.8 ትኩረት መስጠት (Focusing)

በዚህ ትኩረት መስጠት (Focusing) በሚል ንዑስ ምድብ ስር ሀሳብን በፅሁፍ ለማቅረብ ፀሀፊው ፅሁፉን ሲያደራጅ ትኩረት የሚሰጣቸውን ሀሳቦችና መልዕክቶች ለማካተት እንዴት ባሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ሊገለገል ወይም ሊጠቀም ይችላል የሚለውን በተሰበሰቡት መረጃዎች አማካይነት ለመተንተንና ለማብራራት ከመሞከራችን በፊት በዚህ ውስጥ ምድብ ስር የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት (በዚህ ምዕራፍ ለማሳት የሚሞከረው፣ ቀጥሎ የምንሸጋገረው፣ በተለይ . . . ወዘተ) የሚሉ ናቸው::

ቀጥለን ከተገኙት መረጃዎች አንዳር ምሳሌዎች እየሰጠን እንመርምር

ምሳሌ (47) . . . ሌላ ነገር ለማድረግ አቅሙ ከድቶታል:: በተለይ ያችን ቀን አይረሳትም የሰቀቀንና የጭንቅ ኑሮ የጀመረባትን . . . (የካቲ 24/1)

ምሳሌ (48) . . . የሀገራችንን ባህል የሚያንፀባርቁ ልብሶች ጫማዎች የሸክላ ውጤቶች ወዘተ. ይገኙበታል:: በዚያው አካባቢ በተለይ የወላይታ ብሔረሰቦች ሰፊ ቦታ ይዘዋል . . . (ኮከብ 160/02)

በምሳሌ (47) ውስጥ የተጠቀሰው አያያዥ "በተለይ" የሚል ነው:: ይህ አያያዥ በቀዳሚ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተነሳው ሀሳብ ማለትም ሌላ ነገር ማድረግ አለመቻል የአቅም ማጣት/መክዳት/ ሁሉ እንዳለ ሆኖ በተለይ ብሎ ትኩረት ሰጥቶ የገለፃት ያችን ቀን ያላትን የማትረሳ የሰቀቀን የጭንቅ ኑሮ የተጀመረበትን ያችን ቀን በተለይ ብሎ ትኩረት ሰጥቶ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር ያች ቀን ምን ያመጣችው ወዘተ. የሚለውን በትኩረት ለመግለፅ የረዳው አያያዥ ቃሉ መሆኑን በግልፅ እንረዳለን::

ምሳሌ (48) በዚህ ምሳሌ ደግሞ የንግድ ቦታው የተለያዩ የሀገር ባህል ምርቶች መሸጫ እንደሆነ ያስረዳናል:: በቀጣዩ ሀሳብ መነሻ ላይ በተለይ በሚል የተገለፀውን ስንመለከት በዚህ የንግድ ቦታ አካባቢ የወላይታ ብሔረሰቦች መኖራቸውና ከብዛታቸው አንፃር ሰፊ ቦታ መያዛቸውን ከሌላው አካባቢ ይልቅ እዛ አካባቢ በርካታ መሆናቸውን ይገልፃል::

ከላይ የቀረቡትን አያያዦችና የገቡባቸውን ምሳሌዎች ጠቅለል አድርገን ስንመለከት ፀሀፊው በአንባቢው ዘንድ ትኩረት አግኝተው መነበብ ወይም መታወቅ አለባቸው ብሎ ያሰባቸውን የፅሁፍ መልዕክቶች ፅሁፉን በሚያደራጅበት ጊዜም የትኞቹን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መጠቀም ወይም ሊጠቀም እንደሚገባው ለይቶ ማወቅ ይጠይቀዋል:: በመሆኑም ከቀረቡት ምሳሌዎች ይህን ትኩረት በመስጠት ፅሁፍን የማደራጀት አስፈላጊነት እና ከላይ በዚህ ምድብ ስር የተጠቀሱትን ሰባት ንኡሳን ክፍሎች እንደየምድብ ባህሪያቸው በተገቢው መንገድ ልንገለገልባቸው ይገባል:: ምድቡ በስምንት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ይቅረብ እንጂ ሁሉም ሃሳብን በፅሁፍ ለማደራጀት የሚያገለግሉና የሚጠቅሙ አያያዦች ናቸው:: ከላይ ባየናቸው ምሳሌዎች መሠረት አያያዦች ውስን የሆነ /ቋሚ/ ቦታ የላቸውም በተለያዩ ንዑስ ክፍሎች ውስጥ ሲገቡ በስፋት ተስተውለዋል:: ይህንንም ጌታቸው (1987:105) አንድ መስተፃምር ለአንድ ተግባር ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነና በተለያየ ተግባርና በተለያየ የዝምድና ምድቦች ስር ተደጋግሞ ሊገባ እንደሚችል በጥናታቸው ውስጥ ጠቁመዋል::

በምድብ "ለ" ስር የታዩ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት የአጠቃቀም ስህተቶችን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን:: በጥናቱ አራሚዎች ተለቅመው ከወጡት የምድብ "ለ" የአጠቃቀም ስህተቶች መካከል የተወሰኑትን በምሳሌ መልክ እናንሳ:-

ምሳሌ (49) . . . ከወጣሁ በኋላ ለጥቂት ጊዜያት ያህል እዚያው ሰፍራ ተቀመጥኩኝ:: ከዚያም ሆዴና አናቴ ይጮሁብኝ ጀመር:: ከዚያም በአፋጣኝ ከት/ቤት ፍቃድ አስወጥቼ ወደ ቤቴ . . . (ከፍ 084/01)

ምሳሌ (50) . . . የትምህርት ቤቱ ኃላፊዎች የተማሪዎች ተወካዮች ብሎም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች ችግሩን አጢነው ከዚያም አሳማኝ እርምጃ መውሰድ አለባቸው:: . . . (እናት 060)

ምሳሌ (51) . . . እጃቸው አንድም ቀን ስራ ሰርተውበት የሚያውቁ አይመስሉ:: "በአብዛኛው"፣ "እንዲሁም" አጠቃላይ ማለት ይቻላል:: የሰፈራቸው ሰው . . . (ኮከብ 089)

ምሳሌ (52) . . . በሚኖሩት ሰዎች ፀባይ ብዙ ማወቅ ይቻላል:: ከነዚህም ፀባዮች አንዱ አንዳንዶቹ ባይታወቁም የእግዜር ሰላምታ . . . (ኮከብ 95)

ምሳሌ (53) . . . በመጀመሪያ ሲቱና ማለት የሰፈሯ ልጅ ናት እናም ለሲቱና በመቀጠል ጥቂት ነገር ልበላችሁ:: . . . (ኮከብ 85)

ምሳሌ (49) ውስጥ ያለው አያያዥ ቃል ተደጋግሞ ገብቷል:: የምሳሌውም መልዕክት ለመረዳትና ለመከታተል የድርጊት ቅደም ተከተሉን "ከዚያም" በሚለው አያያዥ ግልፅ ሊያደርግልን ሞክሯል:: ሆኖም ተደጋግሞ በመግባቱ የተሰለቸ እንዲሆን ያደርገዋል:: ከዚህም ምሳሌ የምንገነዘበው ይህንኑ ነው::

በምሳሌ (50) ውስጥ የገባው አያያዥ ያለቦታው ወይም ባላስፈላጊ ሁኔታ ነው:: ይህ ምሳሌ ፈፅሞ በዚህ አያያዥ ሊዋቀር አይገባውም:: ምክንያቱም የቀዳሚውን አረፍተ ነገር ሀሳብ ፍሰት የሚያውቅና ከቀጣዩ አረፍተ ነገር ሀሳብ ጋር የማያያዝ በመሆኑ ነው::
በምሳሌ (51) በዚህ ምሳሌ ውስጥ የተለያዩ አያያገሮች ተከታትለው ገብተዋል:: ካላቸው የተለያየ ባህሪ አኳያም ሆነ ተከታትለው በመደርደራቸው ያራመዱት ወይም የሰሩት ስራ የለም:: አያያዥ ቃላትን በተገቢ ቦታና ሁኔታ መርጠን ልንገለገልባቸው ይገባል:: በዚህ ምሳሌ ውስጥ መልዕክቱ እንዲድበሰበስና ሊባል የተፈለገው እንዳይባል አያያገሮቹ ችግር ፈጥረዋል::

በምሳሌ (52) የቀዳሚውን አረፍተ ነገር ሃሳብ ከተከታዩ ጋር ለማያያዝ የገባው "ከነዚህም" የሚለው አያያዥ ቀጥሎ ካሉት ጋር ያለው ስምሙነት ተገቢ ያለመሆን ችግር ውስጥ

ጥሎታል:: እነዚህም “ፀባዮች አንዱ አንዳንዶቹ” የሚሉት በስርአት ያልተደራጁ ከመሆናቸው አኳያ “ከነዚህም” ብሎ ሊጠቅሳቸውና ሊደረድራቸው የፈለገ ቢመስልም ሀሳቡ በወጉ ባለመደራጀቱ አያያዡ ተግባሩን አልተወጣም::

በምሳሌ (53) በዚህ ምሳሌ ውስጥ “በመጀመሪያ”፣ “እናም” እና “በመቀጠል” የሚሉ አያያዦች ተከታትለው ገብተዋል:: ይህ ደግሞ አያያዦችን በተገቢው ሁኔታ እንዳንገለገልባቸው ያደርጋል:: ሁሉም አያያዦች ሀሳብን ለማደራጀት የሚያግዙ ናቸው:: ነገር ግን በአስፈላጊ ቦታና ሁኔታ ጥቅም ላይ ባመዋላቸው እንደስህተት ተቆጥረዋል::

ከፍ ሲል በተለያዩ ምሳሌዎች ስር የቀረቡ አያያዦችን አገባብ ለማየት ሞክረናል:: በምድብ ለ ስር ተጠኚዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ ምን ያህል አያያዦችን ከአጠቃቀም ተገቢ መሆን እና አለመሆን አኳያ በማጠቃለያ መልክ ለማቅረብ ተሞክሯል::

ማጠቃለያ 2:- የምድብ “ለ” አያያዥ ቃላት አጠቃቀም

| ምድብ | ትምህርት ቤቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግል ት/ቤት | | | | | | የመንግስት ትምህርት ቤት | | | | | | የግልና የመንግስት ት/ቤቶች | | | | | |
| | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ለ | 238 | 74.14 | 83 | 25.86 | 321 | 100 | 200 | 82.64 | 42 | 17.36 | 242 | 100 | 438 | 77.80 | 125 | 22.20 | 563 | 100 |

*መግለጫ*

1. ተገቢ አጠቃቀም
2. ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም
3. ድምር

### 4.2.3 ምድብ “ሐ” የፀሀፊውን አተያይ /አመለካከት/ የሚያመላክቱ አያያዦች

አንድ ፀሀፊ በፅሁፉ ስላሰፈራቸው መረጃዎች ወይም ሀሳቦች . . . ወዘተ ያለውን አተያይ የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ:: እነዚህም በሶስት ንዑስ ምድቦችና ከነዚህ ንዑስ ምድቦች የተወጣጡ/የወጡ/ “12” ንዑሳን ምድቦች ወይም ክፍሎች እንዳሉአቸው የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ:: በምድቡ ስር ከሚካተቱት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መካከል (በተመሳሳይ፣ ስለሆነም፣ ምንም እንኳ፣ የሆኖ ሆኖ፣ እና ፣ . . . ) ጥቂቶቹ ናቸው::

በንዑስ ክፍልነት ተለይተው የሚታወቁት 1. አካይ (Additive) 2. ልየታ (Adversative) 3. ሰበባዊ (Causal) ናቸው:: እነዚህን በቀረበበት ቅደም ተከተል መሠረት በዝርዝር እንመለከታቸዋለን::

### 4.2.3.1 አካይ (Additive)

በዚህ ምድብ ስር የሚካተቱ አያያዦች ፀሀፊው ለሚፅፈው ጉዳይ ተጨማሪ መረጃዎች ወይም ሀሳቦች ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ዲስኩር አመልካቾች ናቸው:: ጌታቸው (1987፣58) Halliday and Hassan (1976)ን ጠቅሰው "ማከል" ወይም "መጨመር" ቀድሞ በተነሳ ሀሳብ /መረጃ/ ላይ ሌላ አዲስ ተጨማሪ መረጃ ወይም በመጀመሪያው ላይ ያልተገለፀ መረጃ ተከትሎት ሲቀርብ የሚታይ ዝምድና እንደሆነ ገልፀዋል:: ከዚህ በታች በአካይ ንዑስ ምድብ ስር የሚካተቱት ንዑሳን ክፍሎች በዝርዝር ቀርበዋል::

#### 4.2.3.1.1 ተጨማሪ ማስረጃን መጥቀስ (Aducing further evidence)

በዚህ ተጨማሪ የማስረጃ ማቅረብ ሂደት የምንጠቀምባቸው አያያዦች (በተጨማሪም፣ ከዚህ ሌላ፣ እንዲሁም፣ እና፣ እናም፣ . . . ወዘተ) የመሳሰሉት ናቸው:: ይህን ከተሰበሰበው መረጃ አኳያ ለመተንተንና ለመመርመር እንሞክር

**ምሳሌ (54)** . . . በተለይ በደኞቿ በጣም የሚደነቀውና የሚበረታታው ግልፅነቷ፣ የዋህነቷ፣ እንዲሁም በጎ አስተሳሰቧ እንድትወደድና ሰው አይን እንድትገባ አድርጓታል:: . . . (እናት 062/2)

**ምሳሌ (55)** . . . ሳሙኤል መልከ መልካምና ሸንቃጣ ልጅ ነው:: ለሰዎችም ብዙ በጎ ተግባራትን አድርጓል:: ከዚያም ባሻገር ሳሙኤልን በአንክሮ ለተመለከተ ሰው . . . (እናት 065/2)

**ምሳሌ (56)** . . . አፍንጫዋ ስልክክ ብሎ ከርዝመቱ ጋር ልዩ ውበትን ሰጥቷታል:: ከንፈሮቿ እንደ እንጆሪ ያማሩ ከመሆናቸውም በላይ የአቀማመጣቸው ቅርፅ በጣም የሚያምር ነው:: . . . (እናት 077/1)

**ምሳሌ (57)** . . . የመፃህፍትን ርዕስ የደራሲውን ስም ይዞ የመፃህፍት ማውጫ ካርዶች ወደሚቀመጡበት ሣጥን ይሄዳል፣ በተጨማሪም የቤተመፃህፍት ወይም የላይብረሪ ሠራተኛ /ኃላፊ/. . . (የካ 127/01)

**ምሳሌ (58)** . . . መቼም በእነሱ ዘፈን ሳይስቅ የሚያልፍ የለም:: ይህ ለእነርሱ ደሞዛቸው ነው:: ደግሞ መለስ ብለው በተከታታይ ማለትም አንዷን ሲጋራ ለአምስት ወይም ከዚያ በላይ ሲስቧት

ላይ አንዲት እንጀራ ጋጋሪ የምታነደውን የቅጠል ጢስ . . .
(ኮከብ 103/01)

ምሳሌ (54) በዚህ ምሳሌ ውስጥ ያለው አያያዥ “እንዲሁም” የሚለው ሲሆን ከአያያዡ ቀድሞ የገባውን ሃሳብ ስንመለከት የልጅቷን የተለዩ ጥሩ ባህሪዋን የሚገልፅ ነው:: ከአያያዡ ቀጥሎ የገባውን ስንመለከት ደግሞ በአያያዡ ተጨማሪ እንዲሆን የተደረገውን ሀሳብ “ሌላው ደግሞ” በሚል አይነት አገላለፅ የቀረበ በመሆኑ እንድትወደድ ብሎም በሰው አይን እንድትገባ ያስችላትን በጎ አስተሳሰብ እንዲሁም በሚል ታክሎ እናገኘዋለን:: ይህም ተጨማሪ ማስረጃን ለማቅረብ በግልፅ ረድቷል::

ምሳሌ (55) በመጀመሪያው ሀሳብ ያደረገውና ያከናወነው በግልፅ ተቀምጧል:: በአያያዥነት የገባው “ከዚያም ባሻገር” ብሎ ሊያክል የፈለገውን ሁሉ ሰው በአንክሮ እንዲመለከት በሚል ተጨማሪው ሀሳብ ለማከል ሞክሯል:: እዚህ ላይ ተጨማሪ ሀሳብን ለማቅረብ እንደመነሻ የሚሆን ሀሳብ መኖር እንደለበትና ከዚያ ሀሳብ ጋር ሊታከል የሚችል ሀሳብ ማቅረብ እንደሚቻል መረዳት ይቻላል::

ምሳሌ (56) በዚህ ምሳሌ ደግሞ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ የተገለፀው እንደ እንጆሪ ያማረ ከንፈር የሚለው እንዳለ ሆኖ ከዚህ ሌላ ተጨማሪ ውበት ሊሰጧት የሚችለትን “ከመሆናቸውም በላይ” ሌላ የአቀማመጥ ወበትና ቅርፅ በጣም . . .እንዲሆኑ አድርጎ ለመግለፅና ተጨማሪ መረጃን ለመደርደር /ለማከል/ መሞከሩን እንመለከታለን::

ምሳሌ (57)ና(58) ደግሞ እያንዳዳቸው የተነሱበት ሀሳብ የተለያዩ ቢሆንም “በተጨማሪም” ከዚያ በላይ በሚሉ አያያዦች በቀዳሚዎቹ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ከተነሱት ነጥቦች በመነሳት ተጨማሪ በመጨመር ለመግለፅና ለማሳዩት ይሞክራሉ:: እስካሁን ከላይ ባየናቸው ምሳሌዎች ውስጥ ቀደመው በተነሱ ሀሳቦች ላይ ተጨማሪ ሀሳብን ወይም ማስረጃን ለማከል በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መነሻ ላይ አያያዥ ቃላትን በማስገባት ሀሳብን ለማቅረብ እንደሚቻል ተመልክተናል::

#### 4.2.3.1.2 የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር (De-emphasizing)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ርዕስ ስር የተነገረውን ሀሳብ ለመሸርሸር የምንጠቀምባቸው አያያዦች /በተመሳሳይ፣ ባጋጣሚ ቢያንስ . . .ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ከተሰበሰቡት መርጃዎች ውስጥ በተገኙ ምሳሌዎች በመታገዝ ለማዬት እንሞክር:-

ምሳሌ (59) . . . እሱም በቋፍ ያለችው ልቡን አነሳስቶ በቀጥታ ወደ አዲስ
አበባ መጣ:: ግን እንዳሰበው ነገሮች ምቹ አልሆኑለትም::

እንኳንስ በአንዴ ሰርቶ ቤተሰቡን ሊቀይር ቀርቶ ለራሱም የቀን ጉሮሮ መሙያ ሊያገኝ አልቻለም:: . . . (ከፍ 30)

**ምሳሌ (60)** . . . ስለተነቀሰችው ከድርድር ጥርሶቿ ጋር ተዳምረው ልዩ ውበት ሰጥተዋታል:: ቁመናዋ የሰጠ ነው:: ቀጠን ብላ እረዘም ያለች ያያት የሚደነግጥላት አይነት ሴት ናት በአጋጣሚ በልጅነቷ ስትጫወት ወድቃ የግራ እጇ ተሰብሯል . . . (ኮከብ 091)

**ምሳሌ (61)** . . . ወይዘሮ ይመኙሻል በዚያች ቤት ውር ውር ሲሉ የ68 ዓመት አዛውንት አይመስሉም ደንበኞቻቸውን ለማስተናገድ የማያደርጉት ጥረት የለም:: በኑሯቸው ደስተኛ ባይሆኑም ከፊታቸው ፈገግታ አይለያቸውም:: . . . (እናት 47)

**ምሳሌ (62)** . . . ከኛም ሆነ ከጎረቤታችን ቤት ፊት ለፊት የሚገኝ ድንጋያማና ጎርበጥባጣ ሜዳ ነው:: ሜዳው ይህን ያህል ሰፊ ሰው ባይባልም በቁጥራቸው መጠን ላልተገኘላቸው እና ጨዋታ ለማይጠግቡት ህፃናት የሚያንሳቸው አይደለም::. . . (እናት 75)

**ምሳሌ (63)** . . . ባውቶቡስ ውስጥ ሆነን የኤሊ ጉዞ ተጉዘን መውረጃችን ጋ ስንደርስ ያለው ትግል አያድርስ ነው:: በአጋጣሚ አንዳንዱ ከመጨናነቁ የተነሳ እቃውን ረስቶ የሚወርድ አይጠፋም:: . . . (እናት 74/01)

በምሳሌ (59) ቀዳሚ ክፍል የተወሳው ሀሳብ ባለታሪኩ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ቀድሞም ፍላጎት እንደነበረውና ያለውን ምኞት ለማሳካት እንደሞከረና እንዳሰበው እንዳልሆነለት ይገልፃል:: ከአያያዡ ቀጥሎ የቀረበው ሀሳብ የእለት ወጪውን ለመሸፈን እንደተቸገረ ይገልፃል:: “እንኳንስ” በሚል መነሻ የቀረበው ተከታይ አረፍተ ነገር በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ያለውን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ይህ ምሳሌ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው::

ምሳሌ (60) “በአጋጣሚ” ከሚለው አያያዥ ቀድሞ የተገለፀው ሀሳብ ያያት ሁሉ የሚደነግጥላትና ውብ ቁመና ስላላት ሴት ያትታል:: አያያዡን ተከትሎ የገባው ሀሳብ ግን በልጅነቷ ስለደረሰባት ጉዳት የሚገልፅ ነው:: በቀዳሚው እና በተከታዩ ሀሳብ መካከል ገብቶ ከድሞ የተነገረውን /የተገለፀውን/ ሀሳብ በተከታዩ ጋር ከማያያዝ ባሻገር እንደ አዲስ ያነሳውን ክስተት በቀዳሚው አረፍተ ነገር ሲገለፅ የነበረውን ሀሳብ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ይሸረሽረዋል::

በምሳሌ (61) ውስጥ ከተነሳው ቀዳሚ ሀሳብ ተከትሎ በመጨረሻው አረፍተ ነገር ላይ ያለው “ባይሆኑም” የሚለው አያያዥ ወ/ሮ ይመኙሻል በኑሮአቸው ደስታና እርካታ አይኑራቸው እንጂ ከፊታቸው ፈገግታ አለመለየቱን ይገልፃል፡፡ ቀድሞ የተገለፀው ሀሳብ በተከታዩ ሃሳብ ጋር መለያየቱ “ባይሆኑም” በሚለው አያያዥ ነው፡፡ የቀዳሚውን ሀሳብ ችግርና ውጣ ውረድ የኑሮ ጫና መቋቋም የተለየ ሁኔታ ማሳየትን ወይም ደስተኛ መስሎ መኖርን በግልፅ እንመለከታለን፡፡

ምሳሌ (62) ሜዳው ድንጋያማና ጎርበጥባጣ ነው፡፡ ሰፊ አይደለም፡፡ ሆኖም ከህፃናቱ ቁጥር መብዛትና ጨዋታ መውደድ አኳያ ሜዳው አያንሳቸውም የሚል ሀሳብ ሰፍሯል፡፡ በዚህ ምሳሌ ውስጥ “ባይባልም” በሚል የገባው አያያዥ ሰፊ አይደለም፡፡ ሆኖም ካለው የህፃናት ቁጥር እና የጨዋታ ፍቅር አንፃር ምቹም ባይሆን አያንሳቸውም የሚል ሀሳብ አለ፡፡ የሜዳውን አገልግሎት ከስፋት፣ ከምቹነት ፣ ከመሳሰሉት አኳያ ዝቅ አድርጎ ለማቅረብ መሞከሩ እንገነዘባለን፡፡

ምሳሌ (63) የአውቶቡስ ጉዞ ፍጥነትና ምቾች የሌለው ትግል የበዛበት እንደሆነ በቀዳሚው አረፍተ ነገር ውስጥ ሲገለፅ በተከታዩ አረፍተ ነገር ደግሞ አንዳንዳ ተሳታፊ በትንቅንቁ መሃል እቃውን እረስቶ እንደሚወርድ ተጠቁሟል፡፡ በሁለቱ አረፍተ ነገሮች መካከል የገባው አያያዥ ይህን ሁኔታ ምቾትና ፍጥነት ከማጣት ባሻገር ትግል የበዛበትን ጉዞ በአጋጣሚ ለሌላ ኪሳራ ሰዎችን /ተሳፋሪዎችን/ እንደሚዳርግ ያስረዳናል፡፡ ይህ ምሳሌ በቀዳሚው አረፍተ ነገር ውስጥ ከተነሱት የተሳፋሪዎች በደል በተጨማሪ ሌላ የንብረት መጥፋት ሊያጋጥም እንደሚችል ይነግረናል፡፡ በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ውስጥ የተመለከትናቸው ምሳሌዎች የየራሳቸውን መልዕክት የያዙና የተደራጁ ቢሆንም በቀዳሚው አረፍተ ነገር የተነገረን ወይም የቀረበን ሀሳብ መልዕክት ለመሸርሸር የገቡ ተከታታይ አረፍተ ነገር የገቡ ናቸው፡፡ በየምሳሌዎቹ ስር የተሰመረባቸው አያያዦች እንደየገቡበት አረፍተ ነገር መልዕክት የየራሳቸው ተግባር ሲያከናውኑ ተስተውለዋል፡፡

#### 4.2.3.2 ልየታ (Adversative)

በምድብ “ሐ” ስር ከተካተቱት ንዑስ ምድቦች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ልየታ (Adversative) ስር የሚካተቱ አያያዦች ፀሀፊው በሚፅፈው ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ነው የሚለውን ሀሳብ ወይም መረጃ ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ ጌታቸው (1998) Halliday and Hassan (1976)ን ጠቅሰው ከሚገመተው ወይም ከሚጠበቀው ሀሳብ ውጭ /beyond expectation/ የሆነ ሀሳብ ከመጀመሪያው አረፍተ ነገር ቀጥሎ በመጣው አረፍተ ነገር መገለፁን የሚያመለክት ቃላዊ ዲስኩር ነው፡፡ ይህ ከሚገመተው/ከሚጠበቀው/ ሀሳብ ውጭ የሚቀርበው ሀሳብ የሚገባው ከመጀመሪያው ጋር በአለው አንድ አይነት ዝምድና በመሆኑ በመካከላቸው የሚገባው አመልካች የሚያመለክተው /ይፋ የሚያደርገው/ ይህንኑ ዝምድና ነው ይላሉ፡፡ በዚህ ንዑስ ምድብ ውስጥ

አምስት ንዑሳን ክፍሎች አሉ:: እነርሱንም በየተራ ከተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ በተገኙ ምሳሌዎች አማካይነት ለማብራራብት እንሞክራለን:-

### 4.2.3.2.1 መካድ /ማስተባበል/ (Denying expectation)

በዚህ የንዑስ ምድብ ስር የምንጠቀምባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /ምንም እንኳን ቢሆንም፣ . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ይህን የልየታ ንዑስ ክፍል በተመለከተ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከል "መካድ /ማስተባበል/"ን በተመለከተ ከተገኙ መረጃዎች አኳያ እንደሚከተለው ተተንትኗል::

**ምሳሌ (64)** . . . ቀኑ እሁድ ነበር ልክ አራት ሰዓት ሲል የቤቴን ጣጣ ጨርሼ ዘመድ ለመጠየቅ ወደ ፒያሳ አቀናሁ በተሳፈርኩበት ባስ ውስጥ ብዙ አይነት ሰዎች አሉ:: ግን አይኔ ከአንዲት ሴት ላይ ቀረ:: አይኗ እንደጨረቃ የሚያበራ አፍንጫዋ የፀበል ቁልቁለት ከንፈሯ ደም የቋጠረ . . . (የካ 139)

**ምሳሌ (65)** . . . እለተ እሁድ ከረፋዱ 3:30 ነበር:: የቤት የወጣሁት ያም ሆኖ ግን ሰላማዊ ሰልፍ የመሰለው የትራንስፖርት ወረፋ ችግር አጋጠመኝ እንደመሰላቸት አልኩና ሰአቴን ገልበጥ አደረኳት እፍረት የሌላት ፍጡር አይደለች 4:25 ትላለች:: . . . (የካ 134)

**ምሳሌ (66)** . . . ጠግባ ስትሯሯጥ የማይንቀሳቀሰውን ነገር ሁሉ በራሷ ፈቃድ እያንቀሳቀሰች ስትደሰት ላያት በደስታ ከሚቦርቅ ሕፃን ልጅ ጋር አነፃፅራታለሁ:: ቁጣዋ ግን አይጣል ነው:: በነዚያ እረጃጅምና ቀጫጭን ጥፍሮቿ . . . (ኮከብ 094/01)

**ምሳሌ (67)** . . . ነጋ አልነጋ ብለው ወፍ ሳይንጫጫ ተነስተው ቤታቸውን ማስተካከል ጀመሩ:: ወንበር ጠረጴዛው ቡፌሽና ቀለሙ መሳያ ሽራው ሁሉም ተዝረክርኮ ለማስተካከል በጣም አስቸግሯል ቢሆንም ግን እኩለ ቀን ላይ ሁሉንም አስተካክለው ጨረሱ . . . (ኮከብ 099/2)

ምሳሌ (64) በቀዳሚው አረፍተ ነገር ውስጥ ባለታሪኩ በተሳፈረበት አውቶቡስ የተለያዩ ሰዎችን እንደተመለከተ ገልጿል:: በተከታዩ አረፍተ ነገር ውስጥ ካሉትና ከተመለከታቸው ተጓገኞች መካከል አንዷን አይቶ በውበቷ እንደተማረከ እንረዳለን:: እዚህ ላይ "ግን" በአያያዥነት ስራው የልየታ ተግባር ፈፅሟል:: ከጠቅላላው ተጓዥ ውስጥ አንዷን ውብ ከአሉት ውስጥ ለመለየት ባለታሪኩ ተጠቅሞበታል::

በምሳሌ (65) ውስጥ ደግሞ “ያም ሆኖ ግን” በሚል የገባው አያያዥ ቀዳሚ አረፍተ ነገር ሀሳብ እንዳለ ሆኖ አሁን ያለውንና የተለየውን ሁኔታ በግልፅ ለማሳየት ረድቷል። ይኸውም ባለጉዳዩ በጥፋት መነሳቱን ሆኖም በአለው ትራንስፖርት ችግር አሁን ያለበትን ሁኔታ ይገልፃል። ቀድሞ በመነሳቱ ያመጣው ለውጥ እንደሌለ እንረዳለን።

ምሳሌ (66) በቀዳሚው ሀሳብ ምንም ከማያውቅ የዋህ ህፃን ጋር አመሳስሏታል። በቀጣዩ ሀሳብ ውስጥ ያለው ድርጊት የህፃን ባህሪ አለመሆኑ ያሳያል። ቁጣዋም ሀይለኛና አይጣል የሚያሰኝ ነው። ከዚህ አንፃር በ“ግን” አያያዥነት ሁለት የተለያዩ ባህሪ የተላበሰች እንደህፃን የምትነፃፀርና ኃይለኛና ቁጡ ባህሪ ያላት መሆኗን ያሳያል በዚህ ፀሀፊው ተቃራኒ ሀሳቦች ለመለየት ህፃን ገራገረና በተቃራኒው ቁጡና ኃይለኛ ባህሪን “ግን” ለመለዬት አስችሏል።

ምሳሌ (67) “ቢሆንም ግን” የሚለው አያያዥ በቀዳሚው ሀሳብ የተነሳውንና በተከታዩ የተነሳውን ሀሳብ መለያዬት ያሳያል። አስቸግሮ የነበረውን እኩለ ቀን ላይ አስተካክለው መጨረሳቸውን ያሳያል እንዲህ ሆኖ የነበረው ቢሆንም ግን ትንሽ ቆይቶ እንዲህ ሆነ የሚል ሀሳብ አለው ይህም እስከመጨረሻ ያለን ጥረት የሚያሳይ ሀሳብን ያካተተ ነው።

ከዚህ በላይ የገቡትን አያያዦች ስንመለከት “ቢያንስኝም፣ ባይባልም፣ ግን፣ ቢሆንም ግን” የሚሉት እንደየገቡበት ሀሳብ መለያዬት ይለያዩ እንጂ ሁሉም በልየታ ምድብ ስር በተገቢው ሁኔታ አገልግለዋል። ይህ ሲባል ከዚህ ምድብ ውጪ በሌሎች ዘንድ ቦታ የላቸውም ማለት አይደለም። ስለዚህ ከዚህ የንዑስ ምድብ ውጭ በሌሎች ንዑሳን ምድቦች ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉ ማስተዋል ተገቢ ነው።

#### 4.2.3.2.2 ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል (admitting the unexpected)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /እርግጥ ነው፣ በአጋጣሚ፣ ምናልባት፣ ቢሆንም . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ ቀጥለን በተለያዩ ምሳሌዎች ለማበራራትና ለመተንተን እንሞክር፡-

**ምሳሌ (68)** . . . እያንዳንዱ ውበቱን እያጣ መጥቷል። ቢሆንም ያንን የመሰለ ግርማ ሞገሱን ይጣ . . . (እናት 057/2)

**ምሳሌ (69)** . . . አይኖቹ በእንባ ተሞልተው ነበር። ለልጁ አዘንኩ እርግጥ ነው ለሱ እሷ ቆንጆ ናት ውበት እንደተመልካቹ . . . (ከፍ005/1)

በምሳሌ (68) ውስጥ ያለው ቀዳሚ ዓረፍተ ነገር ሀሳብ እያንዳንዱ ውበት ቀስ በቀስ እየጠፋ መሄዱን ይገልፃል:: በቀጣዩ ዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ያለውን "ቢሆንም" የሚለውን አያያዥ ተከትሎ የገባው ሀሳብ ቁጭት አዘል ሀሳብ ይስነዝራል:: በቀዳሚውም ሆነ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር የተነሳው ውበትና ግርማ ሞገስ እንዳልሆነ መሆን ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰት መቀበል የሚለውን ሀሳብ "ቢሆንም" በሚል የቀረበው ሀሳብ ያንን የመሰለ ግርማ ሞገስና ውበት ቀስ በቀስ እየጠፋ መሄድንና ይህም ያልተጠበቀ ነገር እንደሚከሰትና ሊኖር እንደሚችል ቢሆንም በሚል አያያዥ ተጠቅሞ አቅርቦልናል::

በምሳሌ (69) በዚህ ምሳሌ ደግሞ በመጀመሪያው ሀሳብ የተነሳው አይኖቹ በእምባ የተሞሉና ለልጁ ያዘነ ሰው መኖሩን እንረዳለን:: በአያያዥ ቃላትና ከአያያዡ በኋላ የቀረበው ሀሳብ ደግሞ በምናልባት ሀሳብ የሚሰነዝረው ሰው እሷ ለእሱ ቆንጆ እንደሆነች ይነገረናል:: በዚህ ሁኔታ ተመልካቹ ያዘነው እሱ ቆንጆ ሆኖ ሳለ ቁንጅና ከሌላት ጋር ያለን ሰው ተመልክቶ የሚነግረንን ነው:: በዚህ ተመልካች ያልተጠበቀው ነገር እንደሚከሰትና ይህንን ለመቀበል ያለን ሁኔታ ነው የምናስተውለው አያያዡን በተመለከተ "ምናልባት ለሱ እሷ ቆንጆ ናት" የሚለውን ስንመለከት ተመልካቹ ያልተቀበለው ነገር ግን እሱ የተባለው እሱ በቁንጅናዋ ተማርኮ እናየዋለን::

#### 4.2.3.2.3 የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሊከሰት እንደሚችል መንገር (Correcting from expected to un expected)

በዚህ ንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በምትኩ፣ በተቃራኒው . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው::

ከዚህ በታች በቀረቡት የተለያዩ ምሳሌዎች መሠረት ከፍ ሲል የቀረበውን ሀሳብ ለመተንተን እንሞክር

**ምሳሌ (70)** . . . ከውጭ ሲያይዋት እንኳን የሰው ይቅር እና የዶሮ የማትመስለው ቤት በውስጧ ያልያዘችው ነገር የለም:: ጠላ የሚጠምቁበት ሰባራ እንስራ የጠባቧን ክፍል ግራ ጎን ይዟል የደከመ ወገባቸውን የሚያሳርፉበት ሸቦ አልጋ . . . (እናት 047/02)

**ምሳሌ (71)** . . . እስከ ሞት አንለያይም ብላ ቃል የገባችለት ፍቅረኛው እንኳ ከራቀችው አመታት አልፈዋል:: ስላለፈው ማሰብ፣ መናደድ፣ መበሳጨት፣ መቆጨት፣ እንጂ ሌላ ነገር ለማድረግ አቅሙ ከድቶታል . . . (የካ፡ 124/01)

ከዚህ በላይ የቀረቡት ምሳሌዎች ከላይ በንዑስ ንዑስ ክፍልነት ለቀረበው ሀሳብ ማስረጃነት የቀረቡ ናቸው:: እነዚህን በየተራ ለመተንተንና ለማብራራት እንሞክራለን:-

ምሳሌ (70) በውጭ ሲመለከቷት ወይም ሲያስተውሏት ለሰው ልጅ ቤት የማትሆን መምሰሏን ይልቁንም የዶሮ ቤት የምትመስል እንደሆነች ተገልጿል:: ሆኖም በዚህች በተናቀች ቤት ውስጥ በውስጧ የማትይዘው ወይም ያልያዘችው ነገር እንደሌለ ለመግለፅ ተሞክሯል:: ከዚህ ንዑስ ክፍል ሀሳብ ጋር የተጣጠመ ምሳሌ ነው:: ምክንያቱም የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ሀሳብ በመከሰቱ ነው:: አያያዝንም ስንመለከት የሰው "ይቅርና" የዶሮ የማትመስለው በሚል የተገለፀው በውስጧ ያልየዘችው በሚል አዲስ ያልተጠበቀ ነገርን ይገልፃል::

ምሳሌ (71) በዚህ ምሳሌ መሰረት የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር መጥቷል ተከስቷል አሁን ስላለፈ ነገር ማሰብ መናደድ መበሳጨትና መቆጨት እንጅ ሌላ ትርፍ እንደሌለው ያስረዳል:: ሌላው ቀርቶ ካልተጠበቀው ነገር ለመውጣት አቅም እንደሌለውም በግልፅ ያስረዳል::

ይህም ሀሳብ ከቀረበው ንዑስ ክፍል ሀሳብ ጋር የተጣጣመ በመሆኑ ከዚህ ምሳሌ አንፃር በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዦችንም ሆነ አጠቃቀማቸውን መረዳት ይቻላል::

### 4.2.3.2.4 ማነፃፀር (Contrasting)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በሌላ በኩል፣ በተመሳሳይ መልኩ፣ ነገር ግን . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው::
"ማነፃፀርን" በተመለከተ ከመረጃዎች የተገኙ ምሳሌዎችን በመተንተነና በማበራራት ለማየት እንሞክር::

**ምሳሌ (72)** . . .ሣቂታና ደስተኛ ነች ነገር ግን ሂሩት ስትናደድ ወይም ስትበሳጭ በጣም . . . (ከፍ014/2)

**ምሳሌ (73)** . . . እላይዋ ላይ ብጠመጠምባት ደስ ይለኝ ነበር:: ግን ምን ዋጋ አለው አላውቃትም:: . . . (ከፍ040/1)

**ምሳሌ (74)** . . . የመከፋት ባህሪ አላት ግን ቂም አትይዝም:: . . . **(ከፍ023/02)**

**ምሳሌ (75)** . . . ለቤት አከራዬ የሚሆን ገንዘብ መበደር አለብኝ ነገር ግን ከማውቃቸው ጓደኞቼ ሁሉ ተበድሬአለሁ . . . (እ042/1)

ከዚህ በላይ የቀረቡ አራት ምሳሌዎችን በቅደም ተከተላቸው መሠረት ለመተንተንና ለማብራራት እንሞክር::

ምሳሌ (72) በዚህ ምሳሌ መሠረት ሂሩት ሳቂታና ደስተኛ መሆኗን ይገልፃል:: በተነፃፃሪው ግን ስትናደድና ስትበሳጭ የተለየች መሆኗን በግልፅ ያሳየናል:: "ነገር ግን" የሚለው ከደስታውም ከሳቁም ሌላ በብስጭት ጊዜ ያለ ሌላ ክስተት መኖሩን በማነፃፀር በግልፅ ያስረዳል::

ምሳሌ (73) በዚህ ምሳሌ ደግሞ "ግን" የማነፃፀር ተግባር ሰርቷል እላይዋ ላይ ቢዘል እንደሚደሰት ከገለፀ በኋላ ምን ዋጋ አለው አላውቃትም ይላል:: ይህ ደስታው እሷን ባለማወቅ ምክንያት መቅረቱን"ግን" በገልፅ አሳይታናለች::

ምሳሌ (74) የመከፋት ባህሪ እንዳላት ከባህሪዋም አንዱ እንደሆነ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ ተገልጿል:: ይሁን እንጂ ተከፍታም ቂም አትይዝም የሚለው የሁለተኛው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ ነው ይህን ሀሳብ በማያያዝ ትከፋለች "ግን" ቂም አትይዝም በማለት በማነፃፀር አስቀምጦታል::

ምሳሌ (75) በ"ነገር ግን" አያያዥነት የቀረበው ሀሳብ ገንዘብ መበደር አለብኝ ነገር ግን ከሁሉም ጓደኞቼ ተበድሬአለሁ የሚል ነው:: በዚህ ሀሳብ መካከል የገባው አያያዥ የመጀመሪያውን ፍላጎት ለማሳካት የሚችሉት ሰዎች ከዚህ ስላበደሩት ማበደር የሚሳካ አይነት አይደለም ይኸንንም "ነገር ግን" ይህ በመሆኑ በሚል በቀደመው ዓረፍተ ነገር የተነሳውን ሀሳብ እንደማይሳካ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር በግልፅ ቀርቧል::

ከላይ በተለያዩ ምሳሌዎች የቀረቡትን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀምና ከምሁራኑ አከፋፈል አመዳደብ አኳያ ያላቸውን ስፍራ ለማዬትና ለመመልከት ሞክረናል::

#### 4.2.3.2.5 የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ (Dismissing)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /የሆኖ ሆኖ፣ በሁሉም አቅጣጫ፣ በማንኛውም መልኩ . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው::

"የነበረን እንዳልነበረ ማድረግን በተመለከተ" ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ የተገኙ ምሳሌዎችን በማቅረብ ለመተንተንና ለማብራራት እንሞክራለን:-

**ምሳሌ (76)** . . . ቤቱ ካየኋቸው አስፈሪ የሆረር ፊልሞች መካከል አንዱ የተሰራበት ነው የሚመስለው እንደተረዳሁት ከሆነ <u>ግን</u> ቤቱ በአንድ ወቅት ጫካውን የሚጠብቁ . . . (ኮከብ115/2)

**ምሳሌ (77)** . . . ስንት ንብረት ዘረፈ . . . አካል ጉዳቱ ከፋ አማረረ <u>ግን</u> ምን ያደረጋል ቅስሙ ተሰበረ ያን የሚያህል ጉልበት . . . (ኮከብ109/2)

በሁለቱ ምሳሌዎች የቀረቡትን ሀሳቦች ተራ በተራ ለመተንተን እንሞክር:-

ምሳሌ (76) የቤቱ እጅግ ከመጠን በላይ ማስፈራራት ከአስፈሪ ፊልሞች መካከል እንደ አንዱ እንዲፈረጅ መደረጉን ከቀዳሚው ዐረፍተ ነገር ሀሳብ እንረዳለን:: ነገር ግን በተከታዩ ዐረፍተ ነገር ሀሳብ ተረዳሁት ያለንን የአንድ ወቅት ሌላ ስራ ቤቱ ከነበረበትና ከተሰጠው ስም እንዲሁም ይሆነኝ ተብሎ ለማስፈራሪያ ስራ አለመሰራቱን ተከታዩ ሀሳብ ገልፆልናል:: ይህም ሲሆን ግን እንዳልነበረ በማድረግ ወደ አዲሱ ሀሳብና መርጃ አድርሳናለች::

ምሳሌ (77) ጠንካራውና ጉልበታሙ ሰንቱን ንብረት እንዳልዘረፈ አካል ጉዳቱ ከፍቶ ማማረሩንና የቀድሞ ስራውን ሊሰራ /ሊፈፅም/ በማይችልበት ሁኔታና ደረጃ ላይ እንዳለና የነበረው እንዳልነበረ መሆኑን ያሳያል:: "ግን ምን ያደረጋል" በሚል የቀድሞውን ብርታትና የአሁኑን የከፋ የአካል ጉዳት በማዬት በነበረ መቀረቱን ያሳያል::

#### 4.2.3.3 ሰበባዊ (Causal)

በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ አያያገሮች የምክንያትን፣ የውጤትን፣ የዓላማንና እና የሁኔታን እርስ በርሳዊ ግንኙነትን የሚያመላክቱ ናቸው:: እነዚህም ፀሀፊው ከሚያነሳቸው ጉዳዮች ውጭ ያሉ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ እና ፀሀፊው በሚፅፋቸው ጉዳዮች ላይ በሚነሱት ውስጣዊ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል:: ጌታቸው (1987፣57) ምክንያታዊ ዝምድና በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዓረፍተ ነገር መካከል የተፈጠረው ዝምድና የሰበብና የውጤት ዝምድና የተገለፀበት መሆኑን የሚያመለክት ነው:: በአጠቃላይ አንድ ፀሀፊ አተያዩን ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ቃላትና ሀረጋት በሚከተለው መልኩ ተከፋፍለው ሊታዩ ይችላሉ::

በዚህ መሠረት በአምስት የተለያዩ ክፍሎች ተከፋፍለዋል እነዚህንም በቅደም ተከተል:: እንመልከት:-

##### 4.2.3.3.1 አጠቃላይ (General)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በመሆኑም፣ ስለዚህ፣ በዚህ የተነሳ ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው:: ይህን ንዑስ ርዕስ ለመተንተንና ለማብራራት ያመቸን ዘንድ የአራሚዎች የጋራ ስምምነት ባገኙ ምሳሌዎች በመታገዝ እናቅርብ:-

ምሳሌ (78) . . . የስራ ባልደረቦቹ የሚመክሩትን የማይሰማ በመሆኑ ባለቤቱ አየለች ጥላው ለመሄድ . . . (ኮ090/1)

ምሳሌ (79) . . . ነጋዴዎችንና ሽማቾችን የሚያገናኝ ስፍራ እንደመሆኑ መጠን በውስጡ የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦች . . . (ኮከብ 100/1)

ምሳሌ (80) . . . የበለጡ ወላጆች አርሶ አደሮች ናቸው:: በለጡን በጥሩ ስነምግባር አንፀው አሳድገዋታል:: በመሆኑም ልጃቸው በእነርሱ

ብቻ ሳይሆን በዘመዶቿ እና በአካባቢው ሕብረተሰብ ጠባይዋ የተመሰገነች ልትሆን ችላለች፡፡ . . . (ኮከብ 105/1)

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በቀረቡበት ቅደም ተከተል መሠረት ይተነተናሉ፡፡

ምሳሌ (78) በዚህ ምሳሌ በቀዳሚው የዐረፍተ ነገሩ ክፍል የሚመክሩትን የማይሰማ በመሆኑ ባለቤቱ ጥላው እንደምትሄድ ይገልፃል፡፡ በዓረፍተ ነገሩ መነሻ የተሞከሩት ሙከራዎች ባለመሳካታቸው የመጨረሻው ውጤት ጥሎ እስከመሄድ እንደሚደርስ ያሳያል ያህም ወደ መደምደሚያው ውጤት /ወደማጠቃለያ ሀሳቡ/ ይወስደናል፡፡

ምሳሌ (79) ይህ ሰፊ ገበያ ሁሉንም በጋራ ሊያገበያይ የሚችል በመሆኑ ከስፋቱ አንፃር የተለያዩ ሸቀጦችን በውስጡ ሊይዝ እንደሚችል ያሳያል አያያገዞንም ስንመለከት “እንደመሆኑ መጠን” ይህን-ይህን ሊያደረግ /ሊይዝ/ ይችላል የሚል ሀሳብ አለው፡፡

ምሳሌ (80) በቀዳሚው አረፍተ ነገር በለጡን ወልጆቿ በተሟላ ስነምግባር እንዳሳደጓት ያስረዳናል፡፡ በተከታዩ ሀሳብ ደግሞ በመልካም ፀባይዋ ምክንያት የተገኘ ተወዳጅነትና ምስጋና ከነዋሪዎችና ከዘመዶቿ እንደተለገሳት /እያገኘች/ እንዳለች ያስረዳል፡፡

#### 4.2.3.3.2 ምክንያታዊ (Reason)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት /በዚህ ምክንያት፣ ምክንያቱም ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ የተገኙትን ምሳሌዎች ለማዬት እንሞክር፡-

ምሳሌ (81) . . . አካባቢው አዲስ ስለሆነ እምብዛም አይግባቡም ለዚሁም ሌላው ምክንያት የሁሉም ሰዎች ቤት ለየብቻ . . . (ኮከብ 095/2)

ምሳሌ (82) . . . ግቢው በጣም ሰፊ ነው ከመሰፋቱም የተነሳ አጥሮቹ ከጥግ እስከጥግ አይታዩም . . . (ከፍተ 001/1)

ምሳሌ (83) . . . አይኗ ጎላ ያለ የሚያምር ነው ምን እንደፈለገች አወቀሁኝ ቆዳዋ በጣም ከመለሰለሱ የተነሳ ለመንካት ያሳሳል . . . (ኮከብ 087/2)

ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎች በቅደም ተከተል ማዬት እንሞክር፡-

ምሳሌ (81) የአካባቢው አዲስነት እንዳይገባቡ ሰበብ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም እንደምክንያት የቀረበው የሰዎቹ የመኖሪያ ቤት መራራቅ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር የገባው አያያዥርም ሆነ በተከታዩ ዓረፍተ ነገር የገባው ምክንያታዊ አያያዥ ሁሉም ምክንያታዊነት ያስረዳሉ፡፡

ምሳሌ (82) ከመሰፋቱ የተነሳ አጥሩ ከጥግ እስከ ጥግ በአይን እንደማይታይ ያስረዳል። በዚህ ሁኔታ አያያዥ ቃሉ በተገቢው ቦታ በመግባት ምክንያታዊ አገልግሎት ሰጥቷል።

ምሳሌ (83) በቆዳዋ መለሰለስ የተነሳ ለመንካት ማሳሳቱን ይገልፃል። ይህ ምክንያታዊ አገላለፅ ቀዳሚው ሀሳብና ተከታዩን ሀሳብ በጥሩ ምክንያታዊ ዝምድና መስርቷቸዋል።

#### 4.2.3.3.3 ውጤት (Result)

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሃረጋት /ከተገኘው ውጤት በመነሳት፣ ከዚህ በመነሳት . . . ወዘተ/ የመሳሰሉት ናቸው። ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ የተወሰኑትን ምሳሌዎች በመውሰድ ለመተንተን እንሞክር:-

**ምሳሌ (84)** . . . ካላት መልካም አመለካከት በላይ ሰውን ሁሉ ታከብራለች። ከዚህ በመተነሳ ሰፈርተኛው በሙሉ እንዲወድዳትና እንዲያከብራት . . . (ኮከብ 081/02)

**ምሳሌ (85)** . . . እኔ የምኖርበት አካባቢ በጣም ደስ የሚል ሲሆን ከአካባቢው ፀጥታና አረንጓዴ ተክሎች የተነሳ ከኔ አልፎ በሰፈሩ አዲስ የሆኑትን ሰዎች . . . (ኮከብ 098/02)

**ምሳሌ (86)** . . . ወገቧ በጣም የቀጠነ ከመሆኑ የተነሳ መሶበወርቅ አስመስሏታል። . . . (የካቲ148/2)

**ምሳሌ (87)** . . . የክፍሎቹ ውበት ጠፍቷል። በዚህ የተነሳ ብዙ ተማሪዎች ትምህርት ቤቱን ለቀው . . . (የካቲ130/02)

ከላይ የቀረቡትን አራት የተለያዩ ምሳሌዎች ለመተንተንና ለማብራራት እንሞክር:-
ምሳሌ (84) በቀዳሚው ሀሳብ የተነሳው ፍሬ ነገር መልካም አመለካከቷና ሰውን ሁሉ ማክበሯ ያስገኘላት ውጤት በሰዎች ዘንድ መወደድ መከበር መሆኑን እናስተውላለን። በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መነሻ ላይ የገባው "ከዚህ የተነሳ" የሚለው የሚለውን ውጤት አመላካች "አያያዥ" የተገኘ ውን ውጤት በግልፅ እንድንገነዘብ አድርጓል።

ምሳሌ (85) ከአካባቢው ፀጥታ እና አረንጓዴ ተክሎች መኖር የተነሳ ባለታሪኩም ሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች በአካባቢው ውበትና ልምላሜ ተማርከዋል ይለናል።ይህ ደግሞ በቀዳሚው አረፍተ ነገር ምክንያት የተከታዩ አረፍተ ነገር ሀሳብ ውጤት ሆኖ ቀርቧል።

ምሳሌ (86) ቀጭን ከመሆኑ "የተነሳ" መሶበወርቅ አሰመሰሏታል። ምን አስመስሏታል ለሚለው ጥያቄ መልስ የሆነው "መሶበ ወርቅ" ከወገባ ቅጥነት የተነሳ የተሰጣት ተምሳሌታዊ መግለጫ በውጤትነት አቅርቦልና።

ምሳሌ (87) ውስጥም "በዚህ የተነሳ" በሚል የገባው አያያዥ ተከታዩ ሀሳብ ውጤት አድርጎታል። ይህም በክፍሎቹ ውበት ማጣት ብዙ ተማሪዎች ት/ቤት ሊቀይሩ ችለዋል በሚል በግልፅ ቀርቧል።

በ4.2.3.3. እና በ4.2.3.3.3 መካከል ከንዑስ ምድባቸው የጋራ ባህሪ ባሻገር ምክንያትና ውጤት የማይነጣጠሉ በመሆናቸው ለምሳሌዎች አቀራረብ ረገድ ተመሳስሎና ቅርርብ እንዲኖር አስገድዷል። ይህንንም በተመለከተ መስተፃምራን ወይም ዲስኩር አመልካቾችም በተመለከተ ውስን ቦታ ወይም አገባብ እንደሌላቸው የመስኩ ምሁራንን ጠቅሰን ለመግለፅ ሞክረናል።

**4.2.3.3.4 ዓላማ (Purpose)**

ከዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተቱ የሚችሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት (ይህንን መሠረት በማድረግ፣ ይህንን ለማሳካት . . . ወዘተ) የመሳሰሉት ናቸው።
ከሁሉም አራሚዎች የተገኘው መረጃ በሚያመለክተው በግልም ሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች ድርሰት ውስጥ በዚህ ንዑስ ምድብ ስር የተጠቀሱትን አያያዥ ቃላት ተጠቅመው መረጃዎቻቸውን ወይም ሀሳቦቻቸውን እንዳላሰፈሩባቸው ወይም እንዳልተገለገሉባቸው የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።

**4.2.3.3.5 ሁኔታ (Condition)**

በዚህ የንዑስ ንዑስ ምድብ ስር ሊካተት የሚችሉ አያያዥ ቃላተና ሃረጋት (ከሆነ፣ አለበለዚያ . . . ወዘተ) የመሳሰሉት ናቸው።
ከመረጃዎች መካከል ምሳሌዎችን በመውሰድ ለማዬት እንሞክራለን፡-

**ምሳሌ (88)** እስካሁን የሚያውቁት ሰዎች እንደሚናገሩት <u>ከሆነ</u> ለብሶት የሚያውቀው ልብስ አንድ . . . (እናት 069/2)

ምሳሌ (88) "ሰዎች እንደሚናገሩት ከሆነ" በሚል የቀደመ ታሪኩ ሀሳብ ቀርቧል። ይህም የባለታሪኩን ያለፈ ሁኔታ የሚያስረዳ ነው። እነሱ "እንደሚሉት ከሆነ" በሚል የቀረበው ሀሳብ ያለውን ሁኔታ በግልፅ ለማስረዳት "ከሆነ" የሚል አያያዥን ተጠቅሞ ለመግለፅ ችሏል።

በምድብ ሐ ስር ከተካተቱት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት መካከል በተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ የታዩ የአጠቃቀም ጉድለቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች አማካይነት ለማየት ተሞክሯል።

**ምሳሌ (89)** . . . አውራ ጎዳና መንገድ ላይ ከሚገኘው ጠጅ ቤት ጠጥቶ ሲጋራ እያጨሰ ወደ ቤት መግባቱ የዕለት ተዕለት ተግባሩ ከሆነ ሰነባብቷል። <u>ስለዚህ</u> ባለቤቱ አየለች ቀይ ረዘም ቀጠን ያለች ስትሆን . . . (ኮከብ 090/01)

ምሳሌ (90) . . . ቁንጅናም እንደተመልካቹና እንደ አመለካከቱ ልዩነት አለው ይህ ደግሞ በምክንያት ሲደገፍ ደግሞ ለአንዱ በጣም ቆንጆ የሆነችው ለአንዱ ደግሞ በጣም ፉንጋ ልትሆን ትችላለች . . . (ከፍ 007/01)

ምሳሌ (91) . . . የእኔ ጓደኛ በጊዜያዊና አብረቅራቂ ነገር የማትታለል ጥሩ ጓደኛዬ ብትኖር እሷ ናት። ስለዚህ የጓደኛዬን ጥሩ ምክር በመስማት እዚህ ደረጃ ላይ ደርሻለሁ። . . . (ከፍ 004/01)

ምሳሌ (92) . . . በጨዋታው ላይ ካለኝ ትኩረት የተነሳ ማንነቱን በአፋጣኝ ወይም በቅጡ ለመረዳት ባልችልም ሆኖ ግን በደንብ አየሁት ልጁም በልቡላ ነበር። . . . (የንቲት 147)

ምሳሌ (93) . . . አልማዝ የተወለደችው በትንሽየ ገጠራማ ከተማ ነው። እንዲሁም ለእናቷና ለአባቷ ብቸኛ ልጅ ናት . . . (የካቲት 145)

ምሳሌ (94) . . . በዚህ ቦታ ፈልገን የምናጣው ነገር የለም በሌላ ቦታ ታጣ የሚባል ነገር በዚህ ግን በአዲስ መልኩ ከታጣ በአሮጌ መልኩ ግን ይገኛል . . . (የካቲት 145)

ምሳሌ (89) በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ መሠረት ሲጋራ ማጨስን መጠጥ መጠጣት ተግባሩ ስላደረገ አባወራ ያትታል በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መነሻ ላይ የገባው አያያዥ “ስለዚህ” የሚል ነው። በዚህ መሠረት የተከታዩ ዓረፍተ ነገር ሀሳብ መሆን ያለበት ከቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ተግባርና ሀሳብ ጋር በተስማማ መልኩ የሚቀጥል ተከታይ ሀሳብ መራመድ አለበት። በዚህ ምሳሌ ግን የተከታዩ ዓረፍተ ነገር ሀሳብ የአየለችን ቅለት፣ ርዝመት እና ቅጥነት የሚገልፅ ነው። በመሆኑም አያያዡ በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ አለመዋሉን እንረዳለን።

ምሳሌ (90) አላስፈላጊ የአያያዥ ቃል ድግግሞሽ ይስተዋልበታል ተደጋግሞ የገባው አያያዥ ተደግሞ በመግባቱ የመልዕክቱን ፍሰት የተሟላ ወይም የተሻለ ሲያደርገው አልተስተዋለም። እንድያውም ተደጋግሞ መግባቱ የሀሳብ መቆራረጥንና መደነቃቀፍን አስከትሏል።

ምሳሌ (91) በዚህ ምሳሌ ውስጥ ደግሞ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር የነሳው ሀሳብና በተከታዩ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው ሀሳብ በአያያዡ አማካይነት ማያያዝና መደጋገፍ ነበረባቸው ሆኖም የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ሀሳብ የባለታሪኩ ጓደኛ “በጊዜያዊና አብርቅራቂ” ነገር የማትታለል መሆኗን ሲገልፅ “ስለዚህ” በሚል አያያዥ መራመድ ያለበት ሀሳብ ናለመታለል ጋር የሚጣጣም ሀሳብ መሆን ነበረበት ነገር ግን በተከታዩ ዓረፍተ ነገር የቀረበው ሀሳብ ባለታሪኩ የሷን ምክር

በመስማቱ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱን ይገልፁናል:: አያያዡን በተገቢው ሁኔታ እንዳልተጠቀሙበት በግልፅ እንረዳለን::

ምሳሌ (92) እና (93) በነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ የቀረቡትን ሀሳቦች ለማያያዝ የገቡትን አያያዦች ተግባር ስንመለከት በቀደሚው ዓረፍተ ነገርና በተከታዩ ዓረፍተ ነገር መካከል ያለውን ሀሳብ በተገቢው ሁኔታ ለማያያዝ አልቻሉም ምክንያቱም ለቦታው የሚያስፈልጉ አይደሉም::

ምሳሌ (94) በዚህ ምሳሌ ውስጥ "ግን" ተደጋግሞ ገብቷል:: ከዚህ ምሳሌ የሀሳብ አደረጃጀቱ የራሱ የሆነ ችግር አለበት ያም ሆኖ "ግን"ን በተገቢ ሁኔታና ቦታ ጥቅም ላይ አልዋለም::

በምድብ "ሐ" ስር ተጠኝዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸውን አያያዥ በተመለከተ ከዚህ በታች ማጠቃለያ ቀርቧል::

ማጠቃለያ 3:- የምድብ "ሐ" አያያዥ ቃላት አጠቃቀም

| ምድብ | ትምህርት ቤቶች | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የግል ት/ቤት | | | | | | የመንግስት ትምህርት ቤት | | | | | | የግልና የመንግስት ት/ቤቶች | | | | | |
| | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | | 1 | | 2 | | 3 | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| ሐ | 241 | 84.98 | 131 | 15.02 | 872 | 100 | 857 | 89.74 | 98 | 10.25 | 955 | 100 | 1598 | 87.47 | 229 | 12.53 | 1827 | 100 |

መግለጫ

4. ተገቢ አጠቃቀም
5. ተገቢ ያልሆነ አጠቃቀም
6. ድምር

በአጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ በተጠኝዎች ድርሰት መነሻነት በሶስቱም ምድቦች ስር ያሉ የአያያዥ ቃላትን /ዲስኩር አመልካቾችን/ አከፋፋፈልና አመዳደብ ለማየት ሞክረናል:: ተጠኝዎች የተጠቀሙባቸው አያያዦች በተለያዩ ምድቦችና ክፍሎች ስር ያላቸውን አገባብ በተለያዩ ምሳሌዎች ውስጥ ተመልክተናል:: ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉም ምድቦችና ንዑስ ክፍሎች ከተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ በቂ መረጃ ተገኝቶላቸዋል:: አነስተኛ /ጥቂት/ መረጃ ብቻ ከተገኘ ላቸው ክፍሎች ውስጥ በ4.2.3.3.4 ስር ያለው ዓላማ (Purpse)፣ በ4.2.3.3.5 ስር ያለው ሁኔታ

(Condition)ን ለመግለፅ የሚረዱ ምሳሌዎች በተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ በበቂ ሁኔታ አልተገኙም::

ከዚህ ቀጥሎ በተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና በመምህራን ቃል መጠይቅ ላይ የተደረገ ትንተና በተከታታይ ቀርቧል::

## 4.3 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና የመምህራን ቃለመጠይቅ ትንተና

ከዚህ በታች በ4.3.1 ስር የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እና የመምህራን ቃለመጠይቅ ትንተና ተካሂዷል:: የተማሪዎችም ሆነ የመምህራኑ መጠይቆች ትንተና በየመጠይቁቹ ስር ያሉት ጥያቄዎች በቀረቡበት ቅደም ተከተል መሠረት የተደረገ ነው:: በፅሁፍ መጠይቁም ሆነ በቃለ መጠይቁ ውስጥ ያሉት ጥያቄዎች መሠረታዊ ሀሳብ በአያያዥ ቃላት ምንነት፣ አጠቃቀም፣ ተግባር፣ ጠቀሜታ፣ ዝርዝር አከፋፈልና አመዳደብ፣ እንዲሁም ስለድርሰት ምንነት፣ አፃፃፍና ምጋቤምላሽ አሰጣጥ ባጠቃላይ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ስላሉ የአያያዥ ቃላት መልመጃዎች አቀራረብ፣ ብዛትና ትኩረት . . . ወዘተ የሚጠይቁ ናቸው::

### 4.3.1 የፅሁፍ መጠይቅና የቃለ መጠይቅ ትንተና

ከዚህ ቀጥሎ ለግልም ሆነ ለመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚ ተማሪዎች እና መምህራን የቀረቡ መጠይቆች ይተነተናሉ::

ሠንጠረዥ 11:- ተተኳሪዎች ስለአያያዥ ቃላት ምንነትና አከፋፈል መማር አለመማራቸውን የገለፁበት ምላሽ::

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ስለአያያዥ ቃላትና ሃረጋት ምንነትና አጠቃቀም ተምረሀ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 80 | 100 | 750 | 93.75 |
| | ለ. የለም | - | - | 5 | 6.25 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 2 | የአያያዥ ቃላትና ሃረጋት በስንት እንደ ሚከፈሉ የተማርከው/ሽው/ ነገር አለ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 35 | 43.75 | 51 | 63.75 |
| | ለ. የለም | 45 | 56.25 | 29 | 36.25 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |

በሠንጠረዥ 11 የቀረበውን የተጠኝዎች ምላሽ ስንመለከት በጥያቄ ቁጥር "1" መሠረት የግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአያያዥ ቃላትን ምንነትና አጠቃቀም መማራቸውን ሙሉ በሙሉ /መቶ በመቶ/ "አዎ" በማለት መልስ ሠጥተዋል:: ይህንኑ ጥያቄ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 93.75% ያህሉ "አዎ" ተምረነዋል የሚል ምላሽ ሲሰጡ 6.25% ያህሉ ደግሞ "ለ

የለም" ተምረነው አናውቅም የሚል ምላሽ ሠጥተዋል:: በተገኘው መረጃ መሠረት በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል የተወሰነ ልዩነት ያለ ቢመስልም 5(6.25%) ያህሉ የሰጡት ምላሽ አስተማማኝ አይደለም:: ምክንያቱም ትምህርቱ የሚሰጠው በተናጠል ባለመሆኑ ጥቂቶቹ አልተማርም/ተምረን አናውቅም/ የሚል ምላሽ የሰጡበት የተለያዩ ምክንያት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል:: በጋራ እየተማሩ ያሉ ተማሪዎች በመሆናቸው ምላሻቸው ከጥርጣሬ ውስጥ ይጥለናል::

**ይኸው ጥያቄ ለመምህራን ቀርቦ ከመምህራን የተገኘ ምላሽ**

**ጥያቄ ቁጥር 1:** በዕህፈት ክሂል ትምህርት ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ምንነትና አጠቃቀም አስተምረው ያውቃሉ?

**መልስ:-** የግል ትምህርት ቤት መምህራን ለቀረበላቸው ክፍት ጥያቄ የሰጡት መልስ በፅህፈት ክሂል ትምህርት ጊዜ ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት ምንነትና አጠቃቀም-ተማሪዎቻቸውን ማስተማራቸውን በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል:: አያያዥ ቃላትን ተማሪዎቻቸው ጠንቅቀው እንዲያውቋቸውና እንዲጠቀሙባቸው በተለያዩ የፅሁፍ ስራዎቻቸውና በሚፅፏቸው ድርሰቶች ሁሉ እንዲገለገሉባቸው ማስተማራቸውን ገልፀዋል:: የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ምላሽ ቀደም ሲል ከቀረበው የግል ትምህርት ቤት መምህራን መልስ የተለየ አይደለም፤ ከፅህፈት ክሂል ጋር በተያያዘ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ማስተማራቸውን በመግለፅ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ሰፊ ሽፋን ባያገኝም ባለው ሁኔታ ግን ትምህርቱን መስጠታቸውን ጠቅሰዋል::

በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤቶች መምህራን የተሰጠው ምላሽ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በፅህፈት ክሂል ትምህርቱ ወቅት ከሞላጎደል ማስተማራቸውን እንገነዘባለን:: በሰንጠረዥ 11 ጥያቄ ቁጥር 1 የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ስለአያያዥ ቃላት ምንነትና አጠቃቀም መማራቸውን የገለፁት ተማሪዎች ብዛት ከፍተኛ ሲሆን የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎችን ምላሽ ስንመለከት የተወሰኑት አለመማራቸውን የገለፁ ሲሆን ባጠቃላይ ከመምህራኑም ሆነ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ መምህራን ማስተማራቸውን ተማሪዎችም መማራቸውን በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል::

ሰንጠረዥ 11 ጥያቄ ቁጥር 2 የተሰጠው መልስ ስንመለከት ደግሞ ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ውስጥ 35(43.75%) ያህሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በስንት እንደሚከፈሉ /እንደሚመደቡ/ ተምሬአለሁ ወይም (ሀ. አዎ) በሚል መልስ የሰጡ ሲሆን 45(56.25%) ደግሞ ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልም ሆነ አመዳደብ የተማርኩት "ለ. የለም" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: ይህንኑ ጥያቄ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል 51(63.75%) ያህሉ አያያዥ ቃላት በስንት እንደሚከፈሉ/እንደሚመደቡ/ ተምሬአለሁ ማለትም (ሀ. አዎ) ሲሉ

መልሰዋል:: ቀሪዎቹ 29(36.25%) ያህሉ ደግሞ “ለ. የለም” ወይም በስንት እንደሚከፍሉ የተማርኩት ነገር የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል:: በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አመዳደብ ዙሪያ የተወሰነ ልዩነት እንዳለ በሰጡት መልስ ተረጋግጦአል::

ሠንጠረዥ 12:- አያያዥ ቃላትና ሐረጋት በስንት ይከፈላሉ /ይመደባሉ/

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል/ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ “ሀ. አዎ” ከሆነ በስንት እንደሚከፍሉ ገልፀህ/ሽ/ ዝርዝራቸውን አስቀምጥ/ጪ/ | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የፃፉ | 4 | 5 | 2 | 2.5 |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መፃፍ ያልቻሉ | 76 | 95 | 78 | 97.5 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |

በሠንጠረዥ 12 ጥያቄ ቁጥር 3 ከግል ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጠቅላላ ብዛት 4(5%) ያህሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በስንት እንደሚከፈሉ ገልፀው ዝርዝራቸውን ከሞላ ጎደል ለመጥቀስ ችለዋል 95% ያህሉ ተጠኝዎች በስንት እንደሚከፈሉም ሆነ ዝርዝራቸውን መጥቀስ አልቻሉም:: በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎችም ዘንድ ዝርዝራቸውን ለመጥቀስም ሆነ በስንት እንደሚመደቡ ለመግለፅ የቻሉት 2(2.5) ያህሉ ብቻ ናቸው:: እነዚህ ተጠኝዎች ብቻ አመዳደቡንም ሆነ ዝርዝሩን ለመጥቀስ መሞከራቸወን ከተገኘው መረጃ ተረጋግጧል:: በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን አመደደብና አከፋፈል በተመለከተ አለመማራቸውን /አለማወቃቸውን/ በተገኘው መረጃ ውስጥ (6ቱ) ተማሪዎች ብቻ የአያያዥ ቃላቱን ዝርዝር ሲፅፉ ከ95% እስከ 97.5% ያህሉ ደግሞ ዝርዝራቸውን መፃፍ አለመቻላቸው ከሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል::

በሰንጠረዥ 11 በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ውስጥ ለቀረበው ጥያቄ ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል 35(43.75) እንዲሁም ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 51(63.75) ያህሉ ስለአከፋፈልና አመዳደብ ተምረናል የሚል መልስ የሰጡ ቢሆንም በሠንጠረዥ 12 ጥያቄ ቁጥር 3 ላይ ለቀረበው ጥያቄ በድምሩ 6(7.5%) የሚሆኑ ተማሪዎች ብቻ ትክክለኛውን መልስ ለመጠት ችለዋል:: እዚህ ላይ ስለአያያዥ ቃላት አከፋፈልና አመዳደብ ተምረናል ብለው ካሉት ውስጥ የአያያገሮችን ምድብና ዝርዝር ለመግለፅ የሞከሩት ተጠኝዎች ቁጥር ማነስ በአያያገሮች አከፋፈልና አመዳደብ ዙሪያ የተሰጠው ትምህርት አጥጋቢ አለመሆኑን ወይም ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው አለመከታተላቸውን አለበለዚያም በአያያገሮች አከፋፈልና አመዳደብ ዙሪያ

ትምህርት አለመሠጠቱን እንድንገምትና እንድንጠረጥር ያደርገናል፡፡ የመረጃውንም አስተማማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሊጥለው ይችላል፡፡

**ጥያቄ ቁጥር 2፡-** ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ ተማሪዎችን አስተምረዋቸው ያውቃሉ?

**መልስ፡-** የግል ትምህርት ቤት መምህራን ስለ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈልና አመዳደብ ተማሪዎቻቸውን እንዳላስተማሯቸው ሲገልፁ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ስለአከፋፈልና አመዳደብ የሚገልፅ ነገር ባለመኖሩ አጠቃላይ የሆነ የአያያዥ ቃላትን ተግባር በሚመለከት እንደሚያስተምሯቸው አስረድተዋል፡፡ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራንም የገለፁት ይህንኑ ነው፡፡ አያያዥ ቃላት ካላቸው ተግባርና አገልግሎት አኳያ ጠቅለል አድርገው ከማስተማር ውጪ መድበውና ከፋፍለው አለማስተማራቸውን ገልፀዋል፡፡ በሰንጠረዥ 11 ጥያቄ ቁጥር 2 እና በሰንጠረዥ 12 ጥያቄ ቁጥር 3 የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ ላይ እንደተመለከትነው በስንት እንደሚከፈሉ ገልፀህ/ሽ ዘርዝራቸውን ጥቀስ የሚል ጥያቄ በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ከግልም ሆነ ከመንግስት ት/ቤት ተጠኝዎች የተገኘው መረጃ ይህን አረጋግጧል፡፡ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 13 ስር ለቀረቡ ጊዜ ጠቀስ ጥያቄዎች ተጠኝዎች የሰጡትን ምላሽ እንመለከታለን፡፡

**ሠንጠረዥ 13፡-** የፅሁፍ ሁነት (event) ጊዜን ለማመልከት የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላትን በተመለከተ፡-

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግልት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ፅሁፍ ስትፅፍ/ፊ/ ጊዜን ለማመልከት /ለመጠቆም/ የምትጠቀምባቸው /ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | **67** | **83.75** | **60** | **75** |
| | ለ. የለም | **13** | **16.25** | **20** | **25** |
| | ድምር | **80** | **100** | **80** | **100** |
| 5 | በጥያቄ ተራ ቁጥር "4" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "አዎ" ከሆነ ለአብነት ያህል የተወሰኑትን ዘርዝር/ሪ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የጻፉ | **37** | **55.22** | **46** | **6.67** |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መጻፍ ያልቻሉ | **30** | **44.78** | **14** | **23.33** |
| | ድምር | **67** | **100** | **60** | **100** |

ከሠንጠረዥ 13 ጥያቄ ቁጥር “4” መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ጠቅላላ ብዛት ውስጥ 83.75% ያህሉ “ሀ. አዎ” በማለት ጊዜ ጠቀስ አመልካቾች መኖራቸውን ገልፀዋል:: የተቀሩት 16.25% ያህሉ ደግሞ “ለ. የለም” በማለት ጊዜን ለማመልከት /ለመጠቆም/ የሚያገለግሉ አያያዦች “የሉም” የሚል ምላሽ ሰጥዋል:: እዚህ ላይ በዚህ ጥያቄ ምላሻቸው ውስጥ “ለ. የለም” የሚለውን መልስ ይስጡን እንጂ ከድርሰት ፅሁፋቸው ማረጋገጥ እንደተቻለው በጊዜ ጠቀስ አመልካቾች መገልገላቸውን ነው:: ምናልባት ጊዜ ጠቀስ አመልካቾችን ለይተው /ከፋፍለው/ እንዳልተማሯቸውና እንዳልተነገሩባቸው ልንገምት እንችላለን::

በጥያቄ ቁጥር “4” ጥያቄ ላይ “ሀ. አዎ” ብለው ከመለሱት 67 ተማሪዎች ውስጥ ለጥያቄ ቁጥር “5” የአያያዦችን ዝርዝር በመጥቀስ መልስ የሰጡ 37 (55.22%) ያህሉ ብቻ ናቸው:: ቀሪዎቹ 30(44.78%) ጊዜ ጠቀስ አመልካቾች መኖራቸውን ይወቁ እንጂ ዝርዝራቸውን መጥቀስ አልቻሉም:: የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎችን ስንመለከት ደግሞ አያያዦች አሉ? ለሚለው ጥያቄ “ሀ አዎ” የሚል መልስ የሰጡት 60(75%) ያህሉ ናቸው:: የተቀሩት 25 ያህሉ “ለ. የለም” የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: በጥያቄ ቁጥር “4” ላይ ተመስርቶ ለቀረበው ጥያቄ ቁጥር “5” የሰጡትን ምላሽ ስንመለከት ደግሞ ጊዜ ጠቀስ አያያዦች አሉ (“ሀ አዎ”) ብለው ከመለሱት 60(75%)ቱ ውስጥ የአያያዦችን ዝርዝር መጥቀስ የቻሉትና ጥያቄ ቁጥር “5” በትክክል የመለሱት 46 ብቻ ናቸው:: ቀሪዎቹ 14ቱ ግን ጥያቄውን በትክክል አልመለሱም:: በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል ያለውን ልዩነት ስንመለከት ጊዜን ለማመልከት የምንጠቀምባቸው አያያዥ ቃላት አሉ በማለት ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 67 (83.75%) ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 60(75%) ሲመልሱ ዝርዝራቸውን ጥቀሱ በሚል ለቀረበው ጥያቄ ቁጥር 5 መልስ የሰጡት ከግል 37 ተጠኝዎች ከመንግስት 46 ተጠኝዎች ናቸው:: እዚህ ላይ ጊዜ አመልካች አያያዦች “አሉ” በሚል የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የተወሰነ ብልጫ ቢያሳዩም “አዎ” ብለው ከመለሱት ተጠኝዎች ውስጥ የአያያዥ ቃላቱን ዝርዝር በትክክል በመጥቀስ ብልጫ ያሳዩት የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ናቸው:: ይኸውም ከመንግስት ትምህርት ቤት 46 ተጠኝዎች ከግል ትምህርት ቤት 37 ተጠኝዎች ጊዜን ለማመልከት /ለመጠቆም/ ጥቅም ላይ የሚለውሉትን አያያዦች ዝርዝር ለመፃፍ ችለዋል:: (ተጠኝዎች ለጥያቄ ቁጥር “5” የሰጡት መልስ በአባሪ 6 ተካቷል)::

ሰንጠረዥ 14:- ዕሁፍን ለማደራጀት የሀሳብ ቅደም ተከተልን ለመጠበቅ የሚያገለግል አያያዥ ቃላትን በተመለከተ::

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ዕሁፍን/ሽን/ ለማደራጀት ወይም የሀሳብ ቅደም ተከተል ለመጠበቅ የምትጠቀምባቸው /ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 64 | 80 | 51 | 63.75 |
| | ለ. የለም | 16 | 20 | 29 | 36.25 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 7 | በተራ ቁጥር "6" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ የምታስተውላቸውን /ሺያቸውን ዘርዝር/ሪ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የፃፉ | 58 | 90.62 | 42 | 82.35 |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መፃፍ ያልቻሉ | 6 | 9.36 | 9 | 17.65 |
| | ድምር | 64 | 100 | 51 | 100 |

ከሰንጠረዥ 14 ጥያቄ ቁጥር "6" መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ዕሁፍን ለማደራጀትና የሀሳብን ቅደም ተከተልን ለመጠበቅ የሚረዱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 64(80%) ያህሉ "ሀ. አዎ" ብለው ሲመልሱ 16(20%) ያህሉ ደግሞ "ለ. የለም" የሚለውን መልስ መርጠዋል:: በሌላ በኩል የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎችን ምላሽ ስንመለከት 51(63.74%)ቱ "ሀ. አዎ" ሲሉ፤ "ለ. የለም" በማለት መልስ የሰጡት ደግሞ 29(26.25%) ናቸው:: በግልና በመንግስት ት/ቤት መላሾች መካከል የ13 (16.25%) ያህል የግል ትምህርት ቤት በመላሾች ብዛት ልዩነት አሳይቷል::

በጥያቄ ቁጥር 7 የቀረበውን ጥያቄ ከመመለስ አኳያም የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ልቀው /ተሽለው/ ታይተዋል:: ምክንያቱም ጥያቄው "ዕሁፍን/ሽን/ ለማደራጀት ወይም የሀሳብ ቅደም ተከተል ለመጠበቅ የምትጠቀምባቸውን /ሚባቸውን/ አያያዥ ቃላት ዝርዝር ፃፍ/ፊ/?" የሚል ነው:: በዚህ ጥያቄ መልስ የሰጡት ተማሪዎች ብዛት ከግል ት/ቤት 58 ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 42 ብቻ በመሆናቸው ልዩነቱ ተስተውሏል:: እዚህ ላይ የሀሳብ ቅደም ተከተልን ለመጠበቅና ዕሁፍን ለማደራጀት የምንጠቀምባቸውን አያያዦች አስታውሶ ዝርዝራቸውን ለመፃፍም ሆነ ለመለየት ደጋግሞ መጠቀምን ይጠይቃል:: ከዚህ አኳያ የግል

ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ለጥያቄ ቁጥር 6 እና 7 ከሰጡት መልስ አንፃር በተሻለ ሁኔታ ዝርዝራቸውን መፃፋቸው ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 15፡- የፀሀፊውን አተያይ አመለካከት ለማሳዬት የሚረዱ አያያዥ ቃላት ሀረጋት፡፡**

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ፅሁፍ ስትፅፍ/ፊ/ የራስህን/ሽን/ አተያይ/ አመለካከት/ለማመልከት (ለመጠቆም) የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 62 | 77.5 | 48 | 60 |
| | ለ. የለም | 18 | 22.5 | 32 | 40 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 9 | በተራ ቁጥር "8" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" ከሆነ የምታውቃቸውን/ቂያቸውን ዘርዝር/ሪ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የፃፉ | 55 | 88.71 | 42 | 87.5 |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መፃፍ ያልቻሉ | 7 | 11.29 | 6 | 12.5 |
| | ድምር | 62 | 100 | 48 | 100 |

ከሰንጠረዥ 15 ጥያቄ ቁጥር "8 እና 9" መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው የፀሀፊውን አተያይ /አመለካከት/ የማሳዬት የሚረዱ/የሚያግዙ/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? ካሉ ዝርዝራቸውን ጥቀስ/ሺ/ በሚል ለቀረቡ ጥያቄዎች የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የፀሀፊውን አተያይ ለመጠቆም የሚረዱ አያያዦች አሉ? ለሚለው 62(77.5%) ያህሉ "ሀ. አዎ" ሲሉ 18 (22.5%) ደግሞ "ለ. የለም" በማለት መልሰዋል፡፡ ይህንኑ ጥያቄ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ሲመልሱ 48(60%) "ሀ. አዎ" 32 (40%) ያህሉ ደግሞ "ለ. የለም" ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ምላሽ መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ በመሆኑም የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 14(17.5%) ያህል በመላሾች ቁጥር ብዛት ብልጫ /ልዩነት/ ማሳየቱን መረጃው ይጠቁማል፡፡

በጥያቄ ቁጥር "9" መሠረት ከፍ ሲል ለቀረበው ጥያቄ ቁጥር 8 "ሀ. አዎ" የሚል ምላሽ ከሰጡ ተማሪዎች መካከል ለጥያቄ ቁጥር 9 ተገቢ መልስ የሰጡት ከግል ትምህርት ቤቶች "ሀ. አዎ" ብለው ከመለሱት ጠቅላላ ብዛት 67 ውስጥ 55 ያህሉ ዝርዝራቸውን ሲፅፉ 7 ተጠኝዎች ደግሞ ዝርዝራቸውን ሳይፅፉ ቀርተዋል፡፡ በሌላ በኩል ከመንግስት ት/ቤት ተጠኝዎች መካከል "ሀ. አዎ" የሚል ምላሽ የሰጡት 48 ሲሆኑ ዝርዝራቸውን የፃፉት "42" ያህሉ ሲሆኑ 6ቱ ደግሞ ዝርዝራቸውን ሳይፅፉ ቀርተዋል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር “8” “ለ. የለም” የሚል ምላሽ የሰጡትን ተጠኝዎች ብዛት ብንመለከት ከግል ትምህርት ቤት 18(22%) ያህል ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤት ደግሞ 32(40%) ያህል ናቸው:: አያያዥ ቃላት የፀሀፊውን አተያይ /አመለካከት/ ለማሳዬት ያላቸውን ጠቀሜታ አለመረዳታቸውንና እንዲህ አይነት ጠቀሜታና ግልጋሎት የሚሰጡ አያያዦች እንዳሉ አለመረዳታቸውን ከሰጡት መልስ ለመረዳት ይቻላል::

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ 13፣ 14 ስር ለተማሪዎች ከቀረቡላቸውን ጥያቄዎች ጋር በተመሳሰለ መልኩ ለመምህራን ጥያቄ ቀርቦ የተገኘውን ምላሽ በጥያቄ ቁጥር 3 ስር ቀርቧል::

**ጥያቄ ቁጥር 3:-** ተማሪዎችዎ ድርሰት ሲፅፉ ጊዜን ለማመልከት፣ ፅሁፋቸውን ለማደራጀት ወይም ለማዋቀር፣ የራሳቸውን አተያይ /አመለካከት/ ለማመልከት /ለመጠቆም/ ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስተምረዋቸው ያውቃሉ?

**መልስ:-** አዎ! የአያያዦችን ጥቅምና ተግባር ስገልፅ በተናጠልም ባይሆን ጠቅለል አድርጌ አያያዦች ያላቸውን ጠቀሜታ አስረዳቸዋለሁ በሚል መምህራኑ መልስ ሰጥተዋል:: አያያዥ ቃላትን እንዴት ሊጠቀሙባቸው እንደሚችሉ ስለአገባባቸውና ጠቀሜታቸው ማስተማራቸውን በግልም ሆነ በመንግስት ት/ቤት ከሚያስተምሩ መምህራን የተገኘው መረጃ ያስረዳል:: ሆኖም በየትኛው የአመዳደብና የአከፋፈል ስልት መድበውና ከፋፍለው እንዳስተማሯቸው ሁሉም መምህራን ከሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል::

ሠንጠረዥ 16:- ተጨማሪ ሀሳብን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የሚረዱ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | ፅሁፍ ስትፅፍ/ፊ/ ተጨማሪ ሀሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት/ለመጠቆም ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 73 | 91.25 | 58 | 72.5 |
| | ለ. የለም | 7 | 8.75 | 22 | 27.5 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 11 | በተራ ቁጥር “10” ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ “ሀ. አዎ” ከሆነ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዘርዝር/ሪ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የፃፉ | 67 | 91.78 | 51 | 87.93 |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መፃፍ ያልቻሉ | 6 | 8.22 | 7 | 12.07 |
| | ድምር | 73 | 100 | 58 | 100 |

ሠንጠረዥ 16 ጥያቄ ቁጥር 10 እና 11 መሠረት ተጠኝ ተማሪዎች ተጨማሪ ሀሳብን ለመጠቆም (ለማመልከት) የሚጠቀሙ አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን ለይተው እንደሚያውቋቸውና እንደሚጠቀሙባቸው ከቀረበው መረጃ መገንዘብ ይቻላል:: በመሆኑም ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል 73(91.25%) ያህሉ ተጨማሪ ሀሳብን ለመግለፅ የሚረዱ አያያዦችን ለይተው እንደሚያውቁና እንደሚጠቀሙባቸው ሲገልፁ 7(8.75%) ያህሉ ደግሞ "ለ የለም" የሚለውን መልስ መርጠዋል:: በሌላ በኩል የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎችን መልስ ስንመለከት ደግሞ 58(72.5%) ያህሉ "ሀ. አዎ" የሚል መልስ ሲሰጡ 22(27.5%) የሚሆኑት ደግሞ "ለ. የለም" የሚለውን መልስ መርጠዋል:: ይህንን መልስ ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መልስ ጋር ስናስተያየው ተጨማሪ ሀሳብን ለመግለፅ የሚረዱ አያያዦችን እንደማያውቋቸውና እንደማይጠቀሙባቸው የገለፁት ተጠኝዎች ቁጥር በ15(18.75%) ያህል ከፍ ብሎ ይታያል:: ይህን ልዩነት በሁለቱ ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል ሲፈጥር የቻለው የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት የትምህርት አሰጣጥ፣ አቀራረብ፣ አቀባበል፣ አቀራረፅ . . . ወዘተ መሆን አለመሆኑን እንድንመረምርና እንድንፈትሽ ይጋብዘናል::

ሠንጠረዥ 17:- ተቃራኒ ሀሳብን ለመግለፅ የሚያገለግሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግስት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | ፅሁፍ ስትፅፍ/ፊ/ ተቃራኒ ሀሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት/ለመጠቆም/ ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 73 | 91.25 | 54 | 67.5 |
| | ለ. የለም | 7 | 8.75 | 26 | 35.5 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 13 | በተራ ቁጥር "12" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ የምታስታውሳቸውን/ሺያቸውን/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዘርዝር/ሪ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዝርዝራቸውን የፃፉ | 66 | 90.41 | 48 | 88.89 |
| | ለ. ዝርዝራቸውን መፃፍ ያልቻሉ | 7 | 90.41 | 6 | 11.11 |
| | ድምር | 73 | 100 | 58 | 100 |

በጠንጠረዥ 17 ጥያቄ ቁጥር 12 የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች "ሀ. አዎ" በማለት የመለሱት ብዛት 73(91.25%) ሲሆን፣ "ለ. የለም" በሚል መልስ የሰጡት ደግሞ 7(8.75%) ያህሉ ናቸው። የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ደግሞ 54(67.5%) ያህሉ ተቃራኒ ሀሳብን ለመጠቆም የሚያገለግሉ አያያዦች መኖራቸውን "ሀ. አዎ" የሚል መልስ በመስጠት ሲያረጋግጡ 26(35.5%) ያህሉ ደግሞ "ለ. የለም" የሚለውን መርጠዋል። በግልም ሆነ በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ዘንድ ተቃራኒ ሀሳብን ለመጠቆም የሚያገለግሉ አያያዦች መኖራቸውንና በነዚህ አያያዦች መገልገላቸውን ከሰጡት መልስ ለማረጋገጥ ተችሏል። በጥያቄ 12 ውስጥ ለተጠየቀው መሠረታዊ ጥያቄ ከተገኘው ምላሽ አንፃር የተለያዩ ጥያቄዎችን እንድናነሳ ይገፋፋናል። በመሆኑም ተጠኝው አያያዦችን ከፋፍለውና ለይተው አያውቷቸውም፤ ቢያውቀቸውም አሉ የሉም ለማለት ያዳግተዋል፣ ተከፋፍለውና ተመድበው አልቀረቡላቸውም። በጥቅሉ /በአጠቃላይ/ ይማራቸዋል እንጂ በምድቡ ለይተው ተምረዋቸው አያውቁም . . . ወዘተ የመሣሰሉትን ይበልጥ ተንትኖ ለማዬት ከመምህራን ቃለመጠይቅ ትንተና ጋር ማዬቱ ተገቢ ነው። በሰንጠረዥ 16 እና 18 ስር ከተነሱትና ከሚነሱት ጥያቄዎች ጋር የተቀራረቡ ጥያቄዎች ለመምህራን በጥያቄ ቁጥር 4 ቀርበውላቸዋል።

**ጥያቄ ቁጥር 4፡-** *ተማሪዎችም ተጨማሪ ሐሳብ ተቃራኒ ሀሳብና ምክንያታዊ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን ለማመልከት ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አስተምረው ያውቃሉ።*

**መልስ፡-** *የመማሪያ መፅሀፉ የሚሰጠው መግለጫ የለም፤ ቢኖርም መልመጃውን እንዴት ሊሰሩት እንደሚገባ ነው። ከላይ የተጠየቀው ጥያቄ የተለያዩ አያያዦችን ሲጠቀሙ ጥቅም ላይ የሚያውላቸውን አያያዦች ለይተውና ተግባራቸውን ተረድተው ነው ወይ የሚል ይመስላል በርግጥ ተማሪዎች የአያያዥ ቃላቱን ተግባርና ጠቀሜታ ተረድተው የትኛው አያያዥ ከየትኛው ሀሳብ ጋር ይሄዳል በሚል አስበው ይጠቀሙባቸዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ይህን ሀሳብ ለማመልከት እነዚያ ያን ሀሳብ ለማመልከት በሚል ተከፋፍሎ ቀርቦላቸው አልተማሩም ወይም አላስተማርኩም በሚል የግልና የመንግስት ት/ቤት መምህራን መልስ ሰጥተዋል። አክለውም ተጨማሪ ሀሳብን ተቃራኒና ምክንያታዊ ሀሳብን ለማቅረብ የሚረዱ አያያዦች መኖራቸውን እነዚህን የሚገለገሉባቸው በተለያዩ መልመጃዎች ባዶ ቦታ በመሙላትና የዓረፍተ ነገሮች የአንቀፆችን . . . ወዘተ የተጓደለ አያያዥ በማስተካከል በተሰጡት አያያዦች ተጠቅሞ ዓረፍተ ነገርን መስረት የሚሉ በመሆናቸው ለያይተውና ከፋፍለው እንዳላስተማሯቸው ገልፀዋል።*

ሠንጠረዥ 18:- ምክንያትን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የሚጠቅሙ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግሥት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 14 | በአማርኛ ቋንቋ ፅሁፍ ስትፅፍ/ፊ/ ምክንያታዊ ሀሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት/ለመጠቆም ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው /ሚባቸው/ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 71 | 88.75 | 55 | 68.75 |
| | ለ. የለም | 9 | 11.25 | 25 | 31.25 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 15 | በተራ ቁጥር "14" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ አዎ" የሚል ከሆነ የምታስታውሳቸውን/ሺያቸውን/አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ዘርዝር /ሪ/:: | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. ዘርዝራቸውን የጻፉ | 67 | 94.37 | 50 | 90.91 |
| | ለ. ዘርዝራቸውን መጻፍ ያልቻሉ | 4 | 5.63 | 5 | 9.09 |
| | ድምር | 71 | 100 | 55 | 100 |

በሠንጠረዥ 18 መሠረት ምክንያትን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የምትጠቀምባቸው /ሚባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አሉ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ የግል ትምህርት ቤት ተጠኚዎች 71(88.75%) ያህሉ "ሀ አዎ" የሚል መልስ ሲሰጡ 9(11.25%) ያህሉ ደግሞ "ለ የለም" የሚል መልስ ሰጥተዋል:: የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎችን ስንመለከት ደግሞ 55(68.75%) ያህሉ "ሀ አዎ" በሚል ሲመልሱ 25(31.25%) "ለ የለም" የሚል መልስ ሰጥተዋል፣ በግልና በመንግስት ት/ቤት ተጠኚዎች የተሰጠው ምላሽ ምክንያታዊ ሀሳብን ለመጠቆም የሚረዱ አያያዦች አሉ? ለሚለው ጥያቄ "ሀ አዎ" በሚል የመለሱት የግል ትምህርት ቤት ተጠኚዎች 16(20%) ያህል ልዩነት/ብልጫ/ አሳይተዋል:: በጥናቱ ከተካተቱት የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች መካከል 25(31.25%) ምክንያትን ለመጠቆም /ለማመልከት/ የሚረዱ አያያዦች የሉም በሚል ምላሽ መስጠታቸውን መረጃው አረጋግጧል::

በተራ ቁጥር "15" ለቀረበው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የሰጡ የግል ትምህርት ቤት ተጠኚዎች ስልሳ ሰባት (67) ያህል ሲሆኑ አራቱ (4) ደግሞ የተጠየቁትን ያልመለሱና የአያያዦችን ዝርዝር መፃፍ ያልቻሉ ናቸው:: በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች በኩል ሀምሳ (50) ያህሉ የአያያዥ ቃላቱን ዝርዝር የገለፁ ወይም የፃፉ ሲሆን አምስት (5)ቱ ደግሞ የአያያዦቹን ዝርዝር አለመፃፋቸውን መረጃው ይጠቁማል::

ሠንጠረዥ 19: ስለ ድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ ተማሪዎች ተምረው ያውቃሉ?

ለተማሪዎች የድርሰት እርማት ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀም አኳያ ተሰጧቸው ያውቃል?

| ተ.ቁ | የቀረበው ጥያቄ | የግል ት/ቤት | | የመንግሥት ት/ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 16 | ስለ ድርሰት ምንነትና የአፃፃፍ ዘዴ ተምረሀ/ሽ/ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 78 | 97.5 | 64 | 80 |
| | ለ. የለም | 2 | 2.5 | 16 | 20 |
| | ድምር | 80 | 100 | 80 | 100 |
| 17 | በተራ ቁጥር "16" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ አዎ" የሚል ከሆነ ድርሰት ፅፈሀ/ሽ/ ታውቃለህ/ታውቂያለሽ/? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 65 | 83.33 | 37 | 57.81 |
| | ለ. የለም | 13 | 16.67 | 27 | 42.19 |
| | ድምር | 78 | 100 | 64 | 100 |
| 19 | በተራ ቁጥር "17" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ አዎ" የሚል ከሆነ በፃፍካቸው /ሻቸው/ ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምህን/ሽን/ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ እርማት ሰጥተውህ/ሽ/ ያውቃሉ? | ብዛት | % | ብዛት | % |
| | ሀ. አዎ | 43 | 66.15 | 27 | 72.97 |
| | ለ. የለም | 22 | 33.85 | 10 | 27.03 |
| | ድምር | 65 | 100 | 37 | 100 |

በሰንጠረዥ 19 ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 18 የተዘለለበት ምክንያት ጥያቄው ምን ያህል ጊዜ ድርሰት ፅፋችኋል? የሚል ሲሆን ከተማሪው የተገኘው ምላሽ የክፍል ጊዜ ማነስ የተማሪ ቁጥር መብዛትና ከትምህርት ይዘቶች መብዛት አኳያ ለተማሪዎቹ የተሰጡት የድርሰት መፃፍ ስራዎች ውስንና ተመሳሳይ ሆነው በመገኘታቸው በሰንጠረዡ ውስጥ ተካቶ ሳይተነተን ቀርቷል። ሰንጠረዥ 19 ጥያቄ ቁጥር 16 እና 17ን በተመለከተ ለመምህራን ተመሳሳይ ጥያቄ በጥያቄ ቁጥር 5 ቀርቦ የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው ነው።

ጥያቄ ቁጥር 5፦ ተማሪዎችዎን ድርሰት አፅፈው ሲያበቁ በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ዙሪያ እርማት ሰጥተው ያውቃሉ? የሚሰጡ ከሆነ በምን ያህል ጊዜ? ሁልጊዜ ወይስ አልፎ አልፎ?

መልስ፡- እርማት ሁልጊዜ እንደሚሰጡ ገልፀዋል። ነገር ግን የድርሰት እርማት በተደረገ ጊዜ ሁሉ የአያያዥ ቃላት እርማት ሊኖር እንደሚችል ገልፀዋል። የአያያዥ ቃላት እርማት የሚኖረው ድርሰቱ ሲፃፍ ለአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸው ትኩረት ተሰጥቶ እርማቱ የአያያዥ ቃላት እርማት እንደሆነ በዕቅዳቸው ላይ ሲያሰፍሩት የሚተገብሩት ተግባር እንደሆነ ያስረዳሉ። የድርሰት እርማት ሲደረግ እንዳጠቃላይ አያያዥ ቃላትም እንደማንኛውም የቋንቋ አጠቃቀም እርማት ይታረማሉ የሚል ምላሽ ከግልም ከመንግስትም መምህራን ተገኝቷል። ለአያያዥ ቃላትም ሆነ ለሌላው የድርሰት ስራ እርማት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች እንዳሉም ጠቁመዋል። የተማሪ መብዛት፣ የክፍለ ጊዜ ማነስ፣ የመምህራን የስራ ጫና የተማሪዎች ትኩረት አለመኖር . . . ወዘተ ለድርሰት ስራ ችግር ከሚፈጥሩት መካከል ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ገልፀዋል።

በሰንጠረዥ 19 ውስጥ ጥያቄ ቁጥር 16 ስለድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ ተምረሃል/ሻል/ የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች በተገኘው ምላሽ መሠረት ከግል ትምህርት ቤት ተጠኚዎች 78(97.5%) ያህሉ "ሀ አዎ" በማለት ስለድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ መማራቸውን 2(2.5%) ያህሉ ደግሞ "ለ የለም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች መካከል 64(80%) ያህሉ "ሀ አዎ" የሚለውን መልስ ሲመርጡ 16(20%) ያህሉ "ለ የለም" በማለት መልሰዋል።

ጥያቄ ቁጥር "17" የተመሠረተው በጥያቄ ቁጥር "16" ምላሽ ላይ ነው። ይኸውም ከግልም ሆነ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች ውስጥ የጥያቄ ቁጥር "16" መልሳቸው "ሀ አዎ" የሚል ከሆነ በጥያቄ ቁጥር "17" ትዕዛዝ መሠረት ጥያቄውን ለመመለስ ይችላሉ። ማለትም ድርሰት ፅፈህ/ሽ/ ታውቃለህ/ሽ/ በሚል ለተነሳው /ለተጠየቀው/ ጥያቄ "ሀ አዎ" የሚል ምላሽ የሰጡት ብቻ በጥያቄ 17 ይሳተፋሉ። በመሆኑም ከግል ትምህርት ቤት ተጠኚዎች 78(100%) ውስጥ 65(83.33%) ያህሉ ድርሰት ፅፌ አውቃለሁ ወይም "ሀ አዎ" በማለት ሲመልሱ 13(16.67%) ደግሞ "ለ የለም" በማለት መልሰዋል። ከመንግሥት ትምህርት ቤት ተጠኚዎች የድርሰትን ምንነትና አፃፃፍ ተምሬአለሁ ካሉት 64(100%) ውስጥ 37(57.81%) ድርሰት ጽፌ አውቃለሁ "ሀ አዎ" ሲሉ 27(42.19%) ያህሉ ደግሞ "ለ የለም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ጥያቄ ቁጥር "19" በጥያቄ ቁጥር "17" "ሀ አዎ" የሚል ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ብቻ እንዲሳተፉበት ታቅዶ የተዘጋጀ ነው። በዚህ መሠረት ከግል ት/ቤት ተጠኚዎች 65(100%) ውስጥ 43(16.15%) ያህሉ "ሀ አዎ" በማለት የፃፏቸውን ድርሰቶች ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸው አኳያ መምህሮቻቸው እርማት እንደሚሰጧቸው /ሰጥተዋቸው/ እንደሚያውቁ ሲገልፁ 22(33.85%) ያህሉ እርማት እንዳልተሰጣቸው "ለ የለም" በሚል መልሰዋል።

ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች በጥያቄ ቁጥር "17" ውስጥ ድርሰት ዕፌአለሁ ብለው ከመለሱት ጠቅላላ ብዛት 37(100%) መካከል 27(72.97%) ያህሉ "ሀ አዎ" በማለት ድርሰቶቻችንን ከአያያዥ ቃላት አጠቃቀማችን አኳያ መምህራችን እርማት ይሰጡናል በማለት መልሰዋል:: 10(27.03%) ደግሞ "ለ የለም" በሚል እርማት እንዳልተሰጣቸው ከሰጡት መረጃ መረዳት ይቻላል::

ከላይ በጥያቄ ቁጥር 16፣ 17፣ 19 ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመረምር ተያያዥነት ያላቸውና የአንዱ ጥያቄ መልስ ለቀጣዩ ጥያቄ መልስ እንደመነሻ ሆኖ ሲያገለግል ይታያል:: ከዚህ አኳያ በመጀመሪያ ስለድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚመልሱት መልስ በቀጣዩ ጥያቄ ውስጥ በመልስ ሰጪነት እንዲሳተፉ ወይም እንዳይሳተፉ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ማስተዋል ይቻላል:: በዚህ መሠረት ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል በጥያቄ ቁጥር "16" "ሀ አዎ" በሚል ምላሽ የሰጡት 78(97.5%) ያህሉ ሲሆኑ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች መካከል ደግሞ 64(80%) ያህሉ ተምሬአለሁ "ሀ አዎ" በሚል መልስ ሰጥተዋል እዚህ ላይ በግልና በመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች የተሰጠው ምላሽ 14(17.5%) ያህል ልዩነት ያለው መሆኑን እንረዳለን ከጥያቄ ቁጥር "16" መልስ ተናተነስን ለሌሎች ማለትም ለጥያቄ ቁጥር "17" እና 19" የሚሰጠው መልስ ልዩነት እየሰፋ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል::

ጥያቄ ቁጥር 17 ውስጥ (28) ያህል በጥያቄ ቁጥር "19" ደግሞ (16) ያህል በመላሾች ብዛት ልዩነት የግል ት/ቤት ተጠኝዎች የተሻሉና እንዲሆኑ እንረዳለን:: ይህም ማለት ድርሰት ዕፈናል እና እርማት ይሰጠናል የሚሉት ተማሪዎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ በአያያዥ ቃላት አጠቃማቸው ረገድ የተሻሉ ሊሆሉ ይችላሉ ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሰናል:: ምክንያቱም ዕህፈት ተደጋጋሚ ልምምድንና ምጋቤ ምላሽን በዚህ ደረጃም ቢሆን ይፈልጋል::

ጥያቄ ቁጥር "17" ድርሰት ዕፈህ/ሽ ታውቂያለሽ የሚል ነው:: ለዚህ ጥያቄ የግል ት/ቤት ተጠኝዎች 65(83.33%) "ሀ አዎ" ዕፌአለሁ ሲሉ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች 37(57.81%) ያህሉ "ሀ አዎ" ዕፌአለሁ በሚል መልሰዋል::

በጥያቄ ቁጥር "19" ውስጥ የቀረበው ጥያቄ ድርሰቶቻችሁ ከአያያዥ ቃላትና ሃረጋት አጠቃቀም አኳያ በመምህራችሁ እርማት ይታረምላቸዋል? የሚል ነው:: እዚህ ላይ "ሀ አዎ" ብለው የመለሱት ከግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች "43" ያህል ሲሆኑ "22" ያህሉ እርማት አይሰጠንም የሚል መልስ ሰጥተዋል:: የእርማቱ መኖር አለመኖር እንዳለ ሆኖ የግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች "65" ያህሉ ድርሰት ዕፈው ለዕርማት እንዳቀረቡ ከመረጃው እንረዳለን:: በመንግስት

ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ዘንድ "27"ቱ እርማት ይደረግልናል ሲሉ "10" ደግሞ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀማችን በተመለከተ በመምህራችን እርማት አይደረግልንም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: በአጠቃላይ ከመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ውስጥ 27 ያህሉ ብቻ ድርሰት እንደሚፅፉ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ይቻላል::

ከተማሪዎች የፅሁፍም መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ከማጠቃለላችን በፊት ጥያቄ ቁጥር 18 የተዘለለበትን ምክንያት እንግለፅ ጥያቄው ምን ያህል ጊዜ ድርሰት ፅፋችኋል? የሚል ሲሆን ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ ከተማሪዎች ቁጥር መብዛት ከክፍለ ጊዜ ማነስ ከትምህርት ይዘቶች መብዛትና ከመሳሰሉት አኳያ ለተማሪዎቹ የተሰጡት የድርሰት መፃፍ ስራዎች ውስንና ተመሳሳይ ሆነው በመገኘታቸው በሰንጠረገዦቹ ውስጥ ተካቶ ሳይተነተን ቀርቷል::

**ጥያቄ ቁጥር 6፡-** የአያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን አከፋፈልና አመዳደብ ሲያስተምሩ ከ11ኛ ክፍል መርሃ ትምህርትና መማሪያ መፃህፍት ውጭ የተጠቀሙበት ማጣቀሻ መፃህፍት/መርጃ መማሪያ/ አለ? ተጠቅመው ያስተምራሉ? የተጠቀሙባቸውን ካሉ ቢጠቅሱ፣ ሁሉም መምህራን አያያዥ ቃላትን በተመለከተ የተለያዩ የሀገር ውስጥ ስራዎችን እንደተጠቀሙ ገልፀዋል:: ከነዚህም ውስጥ፣ የቀለም ጠብታ፣ የልቦለድ ፅሁፍ መመሪያ፣ ተግባራዊ የፅህፈት መማሪያ፣ የተለያዩ የሰዋስው መፃህፍት እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል:: ከዚህ አኳያ በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህራን በመማሪያ መፅሐፋም ሆነ በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት የሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል:: ይህን ሁኔታም ከመማሪያ መፃህፍቱ ውጪ በሆኑ /የትምህርት መሳሪያዎች/ ማጣቀሻ መፃህፍት መደገፉ ተገቢ ነው:: ማለትም ቁጥር 7 የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎችም በሚፅፉት ድርሰት/ፅሁፍ/ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ጠቅለል ያለ ሀሳብ ቢሰጡኝ::

**ጥያቄ** በተማሪዎች የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ዙሪያ ከአጠቃቀም ተገቢነት፣ ከስርጭት አኳያ ቢገልፁልኝ::

**መልስ፡-** የተማሪዎችን የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም በተመለከተ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ጎልቶ የሚታይ ችግር የለም፤ አልፎ አልፎ ግን ካለቦታ መጠቀምና ተመሳሳይ አያያገሮችን ደጋግመው ጥቅም ላይ ሲያውሉ ይስተዋላል:: ይህ ደግሞ አያያገሮችን መጠቀም የሚገባን አስፈላጊ በሆኑበት ቦታ ብቻ እንደሆነ የግልም ሆነ የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ገልፀዋል:: ተማሪዎችን ድርሰት በማፃፉ ረገድ ችግሮች እንዳሉ ቀደም ብለው ገልፀዋል:: ይሁን እንጂ ባለው ክፍለ ጊዜ የተፃፉት ድርሰቶች ደግሞ ተገቢ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ሊሰጥባቸው ይገባል:: ይህንንም መምህራኑ ከተማሪዎች ቁጥር አንፃር ስራውን ቀልል የሚያደርጉበትን ዘዴና

መንገድ ማፈላለግ አለባቸው ምክንያቱም የፅሁፍ ስራ የተዋጣ የሚሆነው ተደጋጋሚ ሙከራና ልምምድ ሲደረግበት እንደሆነ ከምሁራኑ ሀሳብ ልንረዳ እንችላለን፡፡

**ጥያቄ ቁጥር 8፡-** ስለድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ ተማሪዎች ምን አስተምረዋቸው ያውቃሉ፡፡
**መልስ፡-** ስለድርሰት ምንነትና የአፃፃፍ ዘዴ ለማስተማር ጥረት እንዳደረጉና የድርሰትን የተለያዩ ባህርያት ከመግለፃቸውም በተጨማሪ የድርሰት አፃፃፍ ቴክኒክ በማስረዳት በፅሁፍ ስራው ላይ አያያዞች የራሳቸው የሆነ ተግባርና ጠቀሜታ እንዳላቸው ተገንዝበው ሊጠቀሙባቸው እንደሚገባ ለተማሪዎች እንደሚገልፁ ከግልም ሆነ ከመንግስት ት/ቤት መምህራን ከተገኘው መረጃ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከፍ ሲል በተለያዩ ጥያቄዎች ስር ሰፍረው የሚገኙት የመምህራን ምላሾች ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት ጋር በእጅጉ የተመሳሰሉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በአያያዥ ቃላት አጠቃቀምና አከፋፈል ረገድ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት /የሰጡት ትምህርት አለመኖሩንና በመማሪያ መፃህፍቱ መልመጃ ላይ ብቻ በመመርኮዝ የአያያዦችን ጠቅለል ያለ የአገባብ አገልግሎት ሁኔታን ማለትም በተሰጡ ባዶ ቦታዎች መሙላትና ቀድመው በተሰጡ አያያዥ ቃላት ተደግፈው አረፍተ ነገር (አንቀጽ) እንዲመሰርቱ በማድረግ ትምህርት ሲሰጡ መቆየታቸውን ከመረጃው መረዳት ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ በምዕራፍ አራት በግልና በመንግስት ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል የፃፏቸውን ድርሰቶች መነሻ በማድረግ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅና ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኙ ምላሾችን በመጨመር ተተንትኖአል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በምዕራፍ አምስት በዚህ ጥናት የተደረሰበትን ውጤትና አስተያየት ለማቅረብ እንሞክራለን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አላማ በግልና በመንግስት የመሠናዶ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት /የመስተፃምራን/ አጠቃቀማቸውን መፈተሽ ወይም መመርመር ነው፡፡

ተተኳሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን /መስተፃምራንን/ በተገቢው ሁኔታ ይጠቀሙባቸዋል? የሚጠቀሙባቸውን አያያዥ ቃላት ተግባርና ጠቀሜታ በውል ለይተው ያውቃሉ? የሚሉና የመሳሰሉትን ጥያቄዎችን ለመመለስ ይቻል ዘንድ ይህ ጥናት ተከናወነ፡፡

አጥኚው ጥናቱን ለማከናወን መነሻ አድርጎ የተነሳባቸው ጥያቄዎች፡-

1. ተጠኝዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት ምን ይመስላል?
2. ተጠኝዎች በፃፉቸው ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ከአላማቸው አኳያ በተገቢው መንገድ ይጠቀሙባቸዋል?
3. በግልና በመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት የተሻሉት የትኞቹ ናቸው? የሚሉ ነበሩ፡፡

በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ዲስኩር ውስጥ አያያዦችን /መስተፃምርን/ በተገቢው ቦታና ሁኔታ መጠቀም ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት በትክክል ለማድረስ ይረዳል፡፡ ይህን በማስመልከት McCharty (1991:69) እንደገለፁት ዲስኩር አመልካቾች/አያያዦች/ አንድ ውሁድ አሀድ መናገር /ማስተላለፍ/ ያለበትን አውዳዊ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ያደርጋሉ፡፡ እየተነገረ ወይም እየተፃፈ ያለን ሀሳብ ለማረጋገጥ፣ ለማጠናከር ያስችላሉ፡፡ በተጨማሪም ለአንድ ሀሳብ የተቃውሞም ሆነ የድጋፍ ሀሳብ ለመሠንዘር . . . ወዘተ. ያገለግላሉ፡፡ በሌላ በኩል አማረ (1968) አንድ ዲስኩር በአቀራረቡ ከመጠን በላይ ከሰፋና ከተለጠጠ በውስጡ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ለመቆጣጠር በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ከዚህ ባሻገር አንባቢውም መልዕክቱን በትክክል ለመረዳት ያስቸግረዋል፡፡ ያለመግባባትም ሊፈጠር እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

በዲስኩር ወቅት ሀሳቦች ሲገለፁ የሀሳቦቹ ፍሰት ተያያዥነት እንዲኖረው ሲባል የአያያዥ ቃላት መኖርና ትክክለኛ ቦታ መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡ የአያያዥ ቃላት ትክክለኛ ቦታ አለመያዝ በሀሳቦች ፍሰት ላይ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡ ይህ እንቅፋት የሚፈጠረው በአያያዥ ቃላት ትክክለኛ ቦታ

አለመያዝ ብቻ ሳይሆን በአያያዥ ቃላት ግድፈት ጭምር ነው:: አያያዥ ቃላት ከተገደፉ ሀሳቡ የተቆራረጠና ተያያዥነት የሌለው እንዲሆን ያደርጉታል:: ከዚህ አኳያ በተጠኚ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ያሉ አያያዦችን ተገቢነት ለመመርመር ጥረት ተደርጓል::

የተማሪዎችን የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም በተመለከተ በግል ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በጻፉቸው አንድ መቶ ስልሳ ድርሰቶች ውስጥ 1429 አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ሲጠቀሙ ከነዚህ ውስጥ 1171 ያህሉን በተገቢው ሁኔታ ተጠቅመውባቸዋል:: 258 ያህሉ ደግሞ የአጠቃቀም ጉድለት /ስህተት/ ተስተውሎባቸዋል የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች በፃፏቸው አንድ መቶ ስልሳ ድርሰቶች ውስጥ 1487 አያያዥ ቃላትን ሲጠቀሙ ከነዚህ ውስጥ 1305 ያህሉን በተገቢ ሁኔታ ሲጠቀሙባቸው 157 ያህሉ የአጠቃቀም ጉድለት ተስተውሎባቸዋል::

በአያያዥ ቃላት አጠቃቀም በኩል ተማሪዎች ብዙ ልምምድ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች አለመመቻቸታቸውና ልምምድ ባለማድረጋቸው በድርሰቶቻቸው ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸው ስህተት ተስተውሏል:: በአያያዥ ቃላት አጠቃቀም የተማሪዎች ችግር ሆነው የታዩት፣ የአያያዥ ቃላቱን ተግባርና ጠቀሜታ ለይተው አለማወቅ፣ ምክንያትን ለመግለፅ፣ ተጨማሪ ሀሳብ ለመስጠት፣ ጊዜን ለመጠቆም ሀሳብን ለማደራጀት . . . የሚረዱ አያያዦችን ለይተው መጠቀም አለመቻላቸው ተረጋግጧል::

ለጥናቱ ተተኳሪዎች ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጋት የሚሰጣቸው ትምህርት የአያያዥ ቃላቱን ተግባርና ጠቀሜታ ለይተው እንዲያውቁ አላደረጋቸውም:: ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅም ሆነ ከመምህራኑ ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአያያዥ ቃላቱን ተግባርና ጠቀሜታ በዝርዝር እንዳልተማሯቸውና እንዳላስተማሯቸው ይገልፃል::

ተተኳሪ ተማሪዎች አልፎ አልፎ ለሚፅፏቸው ድርሰቶች የሚሰጠው እርማትም ሆነ ምጋቤ ምላሽ የአያያዥ ቃላትን /የዲስኩር አመልካቾችን/ አጠቃቀም የተመለከተ አለመሆኑ:- ተጠኝዎች በአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸው ላይ ትኩረት እንዳይሰጡ እንዳደረጋቸው መገንዘብ ተችሏል::

ለጠተኝዎች የሚሰጧቸው መልመጃዎች አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን በድርሰቶቻቸው ውስጥ እንዲጠቀሙባቸውና እንዲገለገሉባቸው የሚያስተምሩ፣ የሚያበረታቱና መሠረታዊ እውቀት የሚያስጨብጡ አይደሉም:: የተሰጧቸውን አያያዦች በባዶ ቦታዎች ውስጥ እየሞሉ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሠርቱ የሚያዝዙ ናቸው:: ይህ ደግሞ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ አደራጅተው እንዲገልፁ እድል አይሰጣቸውም::

የአያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን አመዳደብና አከፋፈል በተመለከተ ባለመማራቸው የትኞቹ በምንና ለምን ሁኔታ እንደሚያገለግሉና ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ለይተው አለማወቃቸውንና አለመረዳታቸውን ከተሰበሰቡት መረጃዎች ተረጋግጧል፡፡

የክፍል ደረጃው መርሃ ትምህርትም ሆነ የመማሪያ መፃህፍቱ ከሌሎች የክፍል ደረጃዎች የመርሃ ትምህርትም ሆነ የመማሪያ መፅሐፍት (ከ10 እና 12 ክፍል) በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አኳያ በመጠኑ የተሻለ አቀራረብ ያላቸው ቢሆንም ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ በሚረዳ መልኩ ተዘጋጅተው የቀረቡ ባለመሆኑ (በተለይ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ) ተማሪውንም ሆነ መምህሩን በአያያዥ ቃላት ዙሪያ የተሻለ እንዲሰሩ ያላደረጋቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመንግስትም ሆነ በግል ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ በከፍተኛ መጠን ጥቅም ላይ የዋሉት አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አንድ ፀሀፊ በፅሁፉ ውስጥ ስላሰፈራቸው መረጃዎች (ሀሳቦች) ያለውን አተያይ /አመለካከት/ የሚያመላክቱ አያያዦች ሆነው ተገኝተዋል፡፡

በአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ተገቢነት ዙሪያ የመንግስት ትምህርት ቤት ተጠኝዎች ተሽለው መገኘታችን ከመርጃው መረዳት ተችሏል፡፡ ይኸውም በድርሰቶቻቸው ውስጥ ከተጠቀሙባቸው አጠቃላይ የአያያዥ ቃላት መካከል 157(10.56%) የሚሆን ብቻ የአጠቃቀም ጉድለት ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በመሆኑም በግልና በመንግስት/ቤት ተጠኝዎች ዘንድ የአጠቃቀም ልዩነት ተስተውሏል፡፡

## 5.1 አስተያየት

1. በተጠኝዎች ድርሰት ውስጥ ከተለቀሙት የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ጉድለቶች /ስህተቶች/ መረዳት እንደተቻለው ብዙዎቹ ተማሪዎች አንድ አይነት ስህተትን /ጉድለትን በተደጋጋሚ ፈፅመዋል፡፡ ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን አጠቃቀም በተገቢ ሁኔታ አለመማራቸውን የሚጠቁም ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን ከዘመናዊው የአያያዥ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀም ጋር መተዋወቅ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ለመምህራን የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን፣ አጫጭር ኮርሶችን፣ የተለያዩ ሙያዊ መወያያ መድረኮች ቢዘጋጁላቸው ጠቃሚ ነው፡፡
2. በጥናቱ ውጤት መሠረት መምህራን አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ለተማሪዎቻቸው የሚያስተምሩበት ዘዴ (ሁኔታ) ከዘመናዊው የማስተማር ዘዴ ጋር የተጣጠመ አይደለም፡፡ ይህም ከመምህራኑ ምላሽ የተገኘው መረጃ በግልፅ ይጠቁማል፡፡ በመሆኑም ከወቅታዊ የአያያዥ ቃላት አከፋፈልና አመዳደብ ጋር ተዋውቀው ትምህርቱን የሚሰጡበት መንገድ ቢመቻች፡-

3. ለማስተማሪያ መሣሪያዎች ዝግጅት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዋና የትምህርት ማቅረቢያ መሣሪያዎችም ሆነ በአጋዥ መፃሕፍት ውስጥ አያያዦች /ዲስኩር አመልካቾች/ በበቂ ሁኔታ እንዲካቱቱ በባለሙያ ቢዘጋጁ:-

4. ተማሪዎቹ በክፍል ደረጃቸው 11ኛ የደረሱ ቢሆንም የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ችግር ታይቶባቸዋል:: ይህን ችግር ለማስወገድ የተማሪዎቹን የፅሁፍ ስራ በወቅቱ በማረምና ከአያያዥ ቃላትና ሃረጋት አጠቃቀም አኳያ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት መምህራን የበኩላቸውን እርምጃ ቢወስዱ:-

5. የመርሀ ትምህርት አዘጋጆች በዕህፈት ክሂል የይዘት መረጣ ውስጥ የአያያዥ ቃላትን ምንነት፣ ጠቀሜታና አገልግሎት እንዲሁም አከፋፈልና አመዳደብ አካተው ቢያቀርቡ:-

6. በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርት አቀራረብ ረገድ ተገቢ ትኩረት ቢሰጥ ከተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ ከክፍል ጊዜ ስርጭት ማነስ፣ ከትምህርት ይዘቶች አመራረጥና ምጣኔ አኳያ የሚመለከታቸው ሁሉ ትኩረት ቢሰጡት:-

7. ተማሪዎች በአያያዥ ቃላትና ሐረጋት አጠቃቀም ረገድ ችሎታቸውን ከፍ ለማድረግ በተለያዩ የጽሁፍ ስራዎቻቸው ውስጥ ለሚገለገሉባቸው አያያዦች አገባብ ተገቢ የሆነ ትኩረት በመስጠት ቢገለገሉባቸው:-

## ዋቢ ፅሁፎች


ማረው አለሙ:: (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል በ2ኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፉ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ" አ.አ.ዩ፣ አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ:: /ያልታተመ/::

ሰይድ ይመር:: (1993):: "በ9ኛ ክፍል ለአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የቀረቡት የፅህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ የመማር ማስተማር ሂደት ግምገማ በሰባት አ.አ. ት/ቤቶች ናሙናነት" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ ለአማርኛ ማስተማር ማስተማር ዲግሪ የቀረበ:: /ያልታተመ/::

ስዩም ከበደ:: (1988):: "ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: /ያልታተመ/::

በድሉ ዋቅጅራ:: (1996):: በስነ ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር:: አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ትምህርት ሚኒስቴር (1997):: የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት አስራ አንደኛ ክፍል (ተሻሽሎ የተዘጋጀ):: አዲስ አበባ፤ የቋንቋዎች ት/ሥ/ት/ዝ/ቡድን ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲቲዩት::

አለማዬሁ ፀጋዬ:: (1986):: "በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈፀሙ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች ምንጮች ትንተና::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: /ያልታተመ/::

አለም እሸቱ:: (1986):: "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማር ዝግጅት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች" የ7-8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርትን ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ:: አዲስ አበባ:: ከ/ስ/ት/ዝ/ጥ/ ምርምር ኢንስቲቲዩት /ያልታተመ/::

አማረ ማሞ:: (1976):: የቀለም ጠብታ የኢልቦለድ አፃፃፍ:: አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ መፃህፍት ድርጅት::

__________ :: (1968):: የልቦለድ ድርሰት አፃፃፍ:: አዲስ አበባ፤ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

አስቴር ሳሙኤል:: (1998):: "የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የፅህፈት ክሂል የማስተማር ዘዴ ፍተሻ (በሆሳዕና ከተማ)::" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ:: (ያልታተመ)::

ድንቂሳ ደሬሳና ዕጌ አበበ (አሻሻዮች)። (1998)። አማርኛ መማሪያ አስራ አንድኛ ክፍል። አዲስ አበባ፤ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳቲሚና የትምህርት ሥራዎች አማካሪ ድርጅት ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዳኛቸው ወርቁ። (1977)። የዕሁፍ ጥበብ መመሪያ። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጌታቸው እንዳለማው። (1987)። "በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ተማሪዎች በተፃፉ ተራኪ ውሁድ አሀዶች ውስጥ የዲስኩር አመልካቾች ስርጭትና ተግባር ትንተና። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ የቀረበ።" /ያልታተመ/።

Allen and Cambel (1972). Teaching English as a Second Language. A.A.U. McGraw-Hill Inc.

Bolitho. R, and Tomlinson, B. (1980). Discover English. London: George Allen and Unwin.

Brown, H. D. (1994). Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy. Enegle Wood Clifts, N. J: Prentice Hallregents.

Byrne, D. (1988). Teaching Writing Skills. Hong Kong: Longman Group.

Celce-Murcia, M. (ed.) (1991). Teaching English as a Second Language. Boston: Hemile and Hainle Publishers.

Chapman, L. J. (1983) Reading Development and Cohesion. London: Heinman Educational Books.

Condon, W. and W. Butler, (1997). Writing the Information Super high way. Boston: Avia Company.

Cook, G. (1989). Discourse. Oxford: Oxford University Press.

Crew, W. J. (1990). "The Illogic of Lognical Connectives". ELT Journal. Vol. 4414. Oxford: Oxford University Press.

Halliday and Rugaiya Hasan. (1976). Cohesion in English. London: Longman.

Headge, Tricia. (1988). Writing. Hong Kong: Oxford University Press.

Heaton, J. B. (1991) Writing English Language Test. (New edition) New York: Longman U.K. Ltd.

Kelly, William J. and Debora <. Lawton. (1998). A Guide to Better Writing. New York: Allyn and Bacon.

Lado, R. (1964). Language Teaching. New York: McGraw-Hill Inc.

McCarthy, M. (1991). Discourse Analysis for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Nunan, D. (1989). The Learner. Centre Curriculum. London: Cambridge University Press.

__________ (1993). Introducing to Discourse Analysis. London. Cambridge University Press Penguin English.

Nuttal, Christine. (1982). Teaching Reading Skills in a Foreign Language. London: Heinemann Educational Books.

Parrot, M. (2002). Grammar for English Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Raimes, Ann. (1983). Techniques in Teaching Writing. Oxford: oxford University Press.

Timble , Lewis, (1985). English for Science and Technology: A Discourse Approach. Cambridge: Cambridge University Press.

White, R. (1980) Teaching Written English. London: Hozellwtton and Viney Ltd. Aylesbury Bucks.

White, R. and V. Arndt. (1991). Process of Writing. London: Longman.

Widdowson. H. G. (1978) Teaching Language as Communication. Oxford: Oxford University Press.

# አባሪዎች

# አባሪ 1 የድርሰት አንድ የአጻጻፍ መመሪያ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል
## አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሃ ግብር
## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ውድ ተማሪ:- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአሥራ "አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሚፅፉቸው የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸውን መመርመርን" ይመለከታል:: የአያያዥ ቃላት መስተፃምራን ሲባሉም እንደሚታወቀው (ደግሞ፣ ስለዚህ/ም/፣ ወይ/ም/ስ/፣ ከዚያ/ም/፣ በዚህ-የተነሳ፣ እንዲሁም፣ ሆኖም፣ በተጨማሪ፣ ስለሆነም፣ ማለት/ም/፣ ቢሆንም፣ በኋላ/ም/፣ ለምሳሌ፣ መጀመሪያ፣ ብሎም፣ በመሆኑም፣ ምክንያቱም፣ ነገር/ግን/፣ እ/ና/፣ ይሁን እንጂ . . . ወዘተ) ናቸው:: ስለሆነም አንተ/ቺ/ እነዚህን እና የመሳሰሉትን አያያዥ ቃላት እና ሐረጎች በመጠቀም ከዚህ በታች በቀረበው መመሪያ መሠረት ድርሰት ፃፍ/ፊ/::

ጥናቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚውል ሲሆን ከአንተ/ቺ/ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: በመሆኑም የድርሰቱ ርዕስ እና ፍሬ ሀሳቡ የራስህ/ሽ/ መሆኑ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል:: ድርሰቱም ለተጠቀሰው የጥናት ዓላማ ብቻ እንደሚውል ላረጋግጥል/ልሽ/ እወዳለሁ:: ውድ ጊዜህን/ሽን/ መስዋዕት አድርገህ/ሽ/ ላደረክልኝ/ሽልኝ/ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

*መመሪያ*

- የሚፃፈው ጽሁፍ የድርሰትን የአፃፃፍ ስልትን የተከተለ መሆን አለበት::
- ድርሰቱ ከ150 ቃላት ባላነሰ ከ300 ቃላት ባልበለጠ ሊፃፍ ይገባል::
- የድርሰቱ ርዕስም ሆነ ፍሬ ሐሳብ ያንተ/ቺ/ ነው::
- ረቂቁን በተሰጠህ/ሽ/ ልሙጥ ወረቀት ላይ ማርቀቅ አለብህ/ሽ/::
- በባለ መስመር ወረቀቱ ላይ የመጨረሻው ፅሁፍ ሲፃፍ አንዳንድ መስመር እየተዘለለ ወይም/እየታለፈ/ ይፃፋል::
- የተወሰነው ጊዜ አንድ ክ/ጊዜ ወይም 45 ደቂቃ ብቻ ነው::

# አባሪ 2 የድርሰት ሁለት የአጻጻፍ መመሪያ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል
## አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሃ ግብር
## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ውድ ተማሪ፡- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በሚፅፏቸው የአማርኛ ድርሰቶች ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀማቸውን መመርመርን ይመለከታል። የአያያዥ ቃላት መስተፃምራን ሲባሉም እንደሚታወቀው (ደግሞ፣ ስለዚህ/ም/፣ ወይ/ም/ስ/፣ ከዚያ/ም/፣ በዚህ-የተነሳ፣ እንዲሁም፣ ሆኖም፣ በተጨማሪ፣ ስለሆነም፣ ማለት/ም/፣ ቢሆንም፣ በኋላ/ም/፣ ለምሳሌ፣ መጀመሪያ፣ ብሎም፣ በመሆኑም፣ ምክንያቱም፣ ነገር/ግን/፣ እ/ና/፣ ይሁን እንጂ . . . ወዘተ) ናቸው። ስለሆነም አንተ/ቺ/ እነዚህን እና የመሳሰሉትን አያያዥ ቃላት እና ሐረጎች በመጠቀም ከዚህ በታች በቀረበው መመሪያ መሠረት ድርሰት ፃፍ/ፊ/።

ጥናቱ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሚውል ሲሆን ከአንተ/ቺ/ የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በመሆኑም የድርሰቱ ርዕስ ከተሰጠህ/ሽ/ አማራጭ ርዕሶች መካከል ያፅፈኛል የምትለውን/ይውን/ መርጠህ/ሽ/ ፃፍ/ፊ/። የምትፅፈው/ፊው/ ድርሰት ለተጠቀሰው የጥናት ዓላማ ብቻ እንደሚውል ላረጋግጥል/ልሽ/ እወዳለሁ። ውድ ጊዜህን/ሽን/ መስዋዕት አድርገህ/ሽ/ ላደረክልኝ/ሽልኝ/ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

**መመሪያ**

- የሚፃፈው ፅሁፍ የድርሰትን የአፃፃፍ ስልትን የተከተለ መሆን አለበት።
- ድርሰቱ ከ150 ቃላት ባላነሰ ከ300 ቃላት ባልበለጠ ሲፃፍ ይገባል።
- የድርሰቱ ርዕስም ሆነ ፍሬ ሀሳብ ያንተ/ቺ ነው።
- ረቂቁን በተሰጠህ/ሽ/ ልሙጥ ወረቀት ላይ ማርቀቅ አለብህ/ሽ/።
- በባለ መስመር ወረቀቱ ላይ የመጨረሻው ፅሁፍ ሲፃፍ አንዳንድ መስመር እየተዘለለ ወይም/እየታለፈ/ ይፃፋል።
- የተወሰነው ጊዜ አንድ ክ/ጊዜ ወይም 45 ደቂቃ ብቻ ነው።

- ስለምታደንቀው/ቂው/ አንድ/ኢት/ ወጣት መልክ፣ ቁመና፣ ጠባይ ወዘተ. በሚመለከት ድርሰት ፃፍ/ፊ/።
- የትምህርት ቤትህን/ሽን/ አቀማመጥ፣ የውስጥ ይዘት፣ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ሁኔታ፣ ወዘተ. በሚመለከት ድርሰት ፃፍ/ፊ/።
- የቸርችል ጎዳናን አይቶ ለማያውቅ ሰው በአይነህሊናው እንዲያየው አድርገህ/ሽ/ ፃፍ/ፊ/።
- መርካቶን አይቶ ለማያውቅ ሰው በአይነ ህሊናው እንዲያየው አድርገህ/ሽ/ ድርሰት ፃፍ/ፊ/።
- ስምተጠላው/ይው/ ነገር፣ ሰው . . . ፃፊ/ፊ/

# አባሪ 3 የድርሰት እርማት መመሪያ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል

## አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሃ ግብር

## የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የጥናቱ ዓላማ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉ የአያያዥ ቃላትን ሀረጋትን አጠቃቀም መፈተሽ በመሆኑ የአገባብ ተገቢነት፣ የስርጭትና የድግግሞሽ መጠን መለየትና መመርመር ነው:: ይኸውም ቃላትን ከቃላት፣ ሀረግን ከሀረግ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር እና አንቀፅን ከአንቀፅ በሚያያይዙበት ጊዜ ሊኖራቸው የሚገባውን ትክክለኛ አጠቃቀም መፈተሽና ማረም ነው:: ስለሆነም የእርስዎ እርማት ለጥናቱ ወሳኝ በመሆኑ እርማቱን በታማኝነት እንዲያርሙት አደራ ተጥሎብዎታል::

አጥኚው

### የእርማት መመሪያ

1. እርማቱ ዝርዝር የድርሰት እርማት አይደለም:: ማለትም የተማሪዎች የግል የድርሰት ችሎታን የሚፈትሽ አይደለም::
2. ድርሰቶች ውስጥ የገቡት አያያዥ ቃላትና ሐረጋት አገባብ ትክክል ከሆነ /✓/ ትክክል ካልሆነ /X/ ማድረግ፣ ትክክል ላልሆኑት አያያዦች ተገቢና ትክክል ነው ብለው የሚያምኑትን ይፃፉ::
3. የአያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አጠቃቀም የሚታየው ራሳቸውን በቻሉ ዓረፍተ ነገሮች መካከል ሲገቡ ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው ሁኔታ ጭምር ነው::
4. እርማቱ ከዚህ በታች የቀረበውን የአያያዥ ቃላትና ሐረጋት አከፋፈልና አመዳደብ መሠረት በማድረግ ይታረማል::

### ምድብ ሀ

የአንድ ፅሑፍ ሁነት /event/ ሲዘገብ የጊዜ ቅደም ተከተሉን የሚያመላክቱ (ጊዜ ጠቀስ) አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት::

ምሳሌ፡- መጀመሪያ፣ ቀጥሎ፣ በአንድ ጊዜ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ በአጠቃላይ “መቼ” የሚለውን ጥያቄ የሚመልሱ አመልካቾች በዚሁ ምድብ ይካተታሉ።

**ምድብ ለ**

የፀሐፊውን የፅሑፍ አደረጃጀት ስልትን የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት

ምሳሌ፡- ለምሳሌ፣ ለማጠቃለል ያህል፣ ይህም ማለት፣ ከዚህ ጋር በተገናዘበ መልኩ፣ ለምሳሌ፣ በአጭሩ እና የመሳሰሉት ናቸው። በዚህ ምድብ ሥር የሚካተቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት በምድብ ሀ እንደጠቀሱት የዘገባው አካል ሳይሆኑ አንድ ፀሐፊ በፅሑፉ ውስጥ የሚኘ ዓረፍተ ነገሮችን አገልግሎት (Function) አንባቢው እንዲረዳ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ውጫዊ ተግባርን የሚያከናውኑ ናቸው። በዓይነታቸው መለያየት የተነሳም በንኡሳን ክፍሎች ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ።

1. ክትትሎሽ አመልካች (Sequencing) ምሳሌ፡- በቅድሚያ፣ ቀጥሎ፣ በአጠቃላይ ወዘተ.
2. በድጋሚ መግለፅ (Re-expressing) ምሳሌ፡- በሌላ አነጋገር፣ ይህም ማለት፣ ወዘተ.
3. በዝርዝር መግለጽ) (Specifying) ምሳሌ፡- እነዚህም፣ በስም ለመጥቀስ፣ ወዘተ.
4. ለይቶ ማመልከት (Referring ምሳሌ፡- ይህን በሚመለከት፣ ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከረው፣ ከዚህ በተለየ መንገድ
5. በድጋሚ ማንሳት (Resuming) ቀደም ሲል ወደተነሳንበት ነጥብ ስንመለስ፣ በድጋሚ ለማስታወስ፣ ወዘተ.
6. ምሳሌ መስጠት (Exemplifying) ምሳሌ፡- ለምሳሌ፣ ይህንን በይበልጥ ለመግለፅ፣ ወዘተ.
7. ማጠቃለል (Summarizing) ለማጠቃለል፣ በአጭሩ፣ ወዘተ.
8. ትኩረት መስጠት (Focusing) በዚህ ምዕራፍ ለማንሳት የሚሞከረው፣ ቀጥሎ የምንሸጋገረው፣ ወዘተ.

እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገው በምድብ “ሀ” ከተካተቱት አያያዦች መካከልም በዚሁ ምድብ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ መሆናቸውን ነው። ምክንያቱም ወሳኙ ጉዳይ የፀሐፊ የፅሑፍ አደረጃጀት ስልትን ለማመልከት የገቡ መሆናቸው ነው።

ምሳሌ፡- መጀመሪያ ዶሮዋን ገነጣጠለቻት። (በምድብ “ሀ” ውስጥ የሚካተት)

በመጀመሪያ ደረጃ ያደገችው ቢኖር (በምድብ “ለ” ውስጥ የሚካተት)

ምድብ ሐ

አንድ ፀሐፊ በፅሑፉ ውስጥ ስላሰፈራቸው መረጃዎች ወይም ሐሳቦች ወዘተ. ያለውን አተያይ የሚያመለክቱ አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት፡፡

ምሳሌ፡- በተመሳሳይ፣ ስለሆነም፣ ምንም እንኳ፣ የሆነሆኖ፣ ከሆነ፣ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህም አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት በሦስት ንኡሳን ምድቦች ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ደግሞ በሥራቸው ሌሎች የንኡስ ንኡስ ምድብ አላቸው፡፡

**አካይ (Additive)** ፡- በዚህ ምድብ የሚካተቱ አያያገሮች ጸሐፊው ለሚፅፈው ጉዳይ ተጨማሪ መረጃዎች ወይም ሐሳቦች ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. **ተጨማሪ ማስረጃን መጥቀስ (Adducing further evidence)** ምሳሌ፡- በተጨማሪም፣ ከዚህ ሌላ ወዘተ.
2. **የተነገረውን ሐሳብ ለመሸርሸር (De-emphasizing)** ፡- በተመሳሳይ፣ ባጋጣሚ፣ ወዘተ.

**ልየታ (Adversative)** ፡- በዚህ ምድብ የሚካተቱት አያያገሮች ደግሞ ፀሐፊው በሚፅፈው ጉዳይ ላይ ተቃራኒ ነው የሚለውን ሐሳብ ወይም መረጃ ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. መካድ /ማስተባበል (denying expectation) - ምሳሌ፡- ምንም እንኳ፣ ቢሆንም፣ ወዘተ.
2. ያልተጠበቀ ነገር እንደሚከሰት መቀበል (Admitting the unexpected) - ምሳሌ፡- እርግጥ ነው ባጋጣሚ፣ ወዘተ.
3. የተጠበቀው ቀርቶ ያልተጠበቀው ነገር ሊከሰት እንደሚችል መንገር (Correcting from expected to unexpected)- ምሳሌ፡- በምትኩ፣ በተቃራኒው፣ ወዘተ.
4. ማነፃፀር (Contrasting) - ምሳሌ፡- በሌላ በኩል፣ በተመሳሳይ መልኩ፣ ወተ.
5. የነበረውን እንዳልነበረ ማድረግ (Dismissing) - ምሳሌ፣ የሆነሆኖ፣ በሁሉም አቅጣጫ፣ በማንኛውም መልኩ፣ ወዘተ.

ሰበባዊ (Causal)፡- በዚህም ምድብ ውስጥ የሚካተቱ አያያገሮች የምክንያትን፣ የውጤትን፣ የዓላማን እና የሁኔታን እርስ በርሳዊ ግንኙነትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡
እነዚህም፡-

ሀ. ፀሐፊው ከሚያነሳቸው ጉዳዮች ውጭ ያሉ ሁኔታዎችን የሚያመላክቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- ሀይለኛ ድካም ተሰምቷታል። በዚህ የተነሳ ከክፍሏ መውጣት አልቻለችም።

ለ. ፀሐፊው በሚፅፋቸው ጉዳዮች ላይ በሚነሱት ውስጣዊ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ፡- ጉዳዩ ከመጠን በላይ የተወሳሰበ ነው። በዚህ የተነሳ በአሁኑ ሰዓት በጉዳዩ ላይ ከዚህ በላይ መሄድ አንችልም።

በአጠቃላይ አንድ ፀሐፊ አተያዩን ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ ለማመልከት የሚጠቀምባቸው ቃላት እና ሐረጋት በሚከተለው መልኩ ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ።

1. አጠቃላይ (General) ምሳሌ፡- በመሆኑም፣ ስለዚህ፣ በዚህ የተነሳ (Consequently)፣ ወዘተ.
2. ምክንያታዊ (Reason) ምሳሌ፡- በዚህ ምክንያት፣ ምክንያቱም፣ ወዘተ.
3. ውጤት (Result) ምሳሌ፡- ከተገኘው ውጤት በመነሳት፣ ከዚህ በመነሳት፣ ወዘተ.
4. ዓላማ (Purpose) ምሳሌ፡- ይህንን መሠረት በማድረግ፣ ይህንን ለማሳካት፣ ወዘተ.
5. ሁኔታ (Condition)ምሳሌ፡- ከሆነ፣ አለበለዚያ፣ ወዘተ.

(ከተራ ቁጥር 2 ጀምሮ ለተጠቀሱት ሀሳቦች ምንጭ Nuttall, 1982:95-98)።

## አባሪ 4 ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

### አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
### የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
### የኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል
### አማርኛ ማስተማር ሥነዘዴ መርሃ ግብር
### የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በመንግስት እና በግል ትምህርት ቤት በሚማሩ የ11ኛ ክፍል ተጠኝ ተማሪዎች የሚሞላ የፅሑፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪ፣ የዚህ ፅሑፍ መጠይቅ ዓላማ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ገላጭ ድርሰት ሲፅፉ የአያያዥ ቃላት እና ሀረጋት አጠቃቀም እና ስርጭት መመርመር ነው፡፡ ስለሆነም ለጥናቱ ዓላማ መሳካት ያንተ/ቺ/ አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የፅሑፍ መጠይቁን በቅንነት እና በታማኝነት እንድትሞላ/ዪ/ ይጠበቃል፡፡ ከፅሑፍ መጠይቁ የሚገኘው መልስም ከዚህ ጥናት ውጭ ለሌላ ተግባር እንደማይውል ላረጋግጥልህ/ሽ/ እመዳለሁ፡፡ በተረፈ ውድ ጊዜህን /ሺን/ መሰዋእት በማድረግ የፅሑፍ መጠይቁን በመሙላትህ/ሽ/ አመሰግናለሁ/ሻለሁ/፡፡

አጥኚው

ማሳሰቢያ

- በፅሑፍ መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡
- የፅሑፍ መጠይቁ አማራጭ መልስ (ዝግ ጥያቄ) እና ክፍት ጥያቄ የያዘ ነው፡፡ ስለሆነም ለአማራጭ ጥያቄው የመልሱን ፊደል በማክበብ መልስ/ሺ/ ለክፍት ጥያቄው ደግሞ ሐሳብህን/ሺን/ በፅሑፍ መልስ/ሺ/፡፡

የተማሪው ዳራ

ዕድሜ ____________ የትምህርት ቤቱ ስም ________________

ፆታ _____________

የክፍል ደረጃ ________________

1. ስለ አያያዥ ቃላት እና ሃረጋት ምንነት እና አጠቃቀም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተምረህ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/?

   ሀ. አዎ ለ. የለም

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አያያዥ ቃላት እና ሀረጋት በስንት እንደሚከፈሉ የማርከው/ሽው/ ነገር አለ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

3. በተራ ቁጥር "2" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ " ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ በስንት እንደሚከፈሉ ገልፀህ/ሽ/ ዝርዝራቸውን አስቀምጥ/ጪ/።

4. በአማርኛ ቋንቋ ዕሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ ጊዜን ለማመልከት /ለመጠቆም/ የምትጠቀምባቸው /ሚባቸው/ አያያዥ ቃላት እና ሀረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

5. በተራ ቁጥር "4" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ ለአብነት ያህል የወሰኑትን ዘርዝር/ሪ/።

____________________________________________________

____________________________________________________

6. በአማርኛ ቋንቋ ዕሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ ዕሑፍህን/ሽን/ ለማደራጀት/ የሐሳብ ቅደም ተከተል ለመጠበቅ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/አያያዥ ቃላት እና ሀረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

7. በተራ ቁጥር "6" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ የምታስታውሳቸውን/ሺያቸውን/ ዘርዝር/ሪ/።

____________________________________________________

____________________________________________________

8. በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ የራስህን/ሺን/ አተያይ (አመለካከት) ለማመልከት (ለመጠቆም) እንዲረዳህ/ሽ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/ አያያዥ ቃላት እና ሀረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

9. በተራ ቁጥር "8" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ.አዎ" የሚል ከሆነ የምታውቃቸውን /ቂያቸውን/ ዘርዝር/ሪ/።

____________________________________________________

____________________________________________________

10. በአማርኛ ቋንቋ ዕሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ ተጨማሪ ሐሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት /ለመጠቆም/ ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

11. በተራ ቁጥር "10" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ.አዎ" የሚል ከሆነ የምትጠቀምባቸውን /ሚባቸውን/ ዘርዝር/ሪ/፡፡

12. በአማርኛ ቋንቋ ዕሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ ተቃራኒ ሐሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት /ለመጠቆም/ ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

13. በተራ ቁጥር "12" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ የምታስታውሳቸውን/ሺያቸውን ዘርዝር/ሪ/፡፡

14. በአማርኛ ቋንቋ ዕሑፍ ስትፅፍ/ፊ/ ምክንያታዊ ሐሳብ ያለህ/ሽ/ መሆኑን ለማመልከት /ለመጠቆም/ ስትፈልግ/ጊ/ የምትጠቀምባቸው/ሚባቸው/አያያዥ ቃላት እና ሐረጋት አሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

15. በተራ ቁጥር "14" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ የምታስታውሳቸውን/ሺያቸውን ዘርዝር/ሪ/፡፡

16. ስለ ድርሰት ምንነት እና የአፃፃፍ ዘዴ ተምረህ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/?

ሀ. አዎ ለ. የለም

17. በተራ ቁጥር "16" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ ድርሰት ፅፈህ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/?

ሀ. አዎ ለ. የለም

18. በተራ ቁጥር "17" ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ "ሀ. አዎ" የሚል ከሆነ ስንት ጊዜ እንዳፃፍክ/ሽ/ ግለፅ/ጭ/፡፡

19. በተራ ቁጥር “17” ለተጠየቀው ጥያቄ መልስህ/ሽ/ “ሀ. አዎ” የሚል ከሆነ በድርሰትህ/ሽ/ ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምህን/ሽን/ በተመለከተ የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ እርማት ሰጥተውህ/ሽ/ ያውቃሉ?

ሀ. አዎ ለ. የለም

______________________________________________

______________________________________________

# አባሪ 5 ለመምህራን የቀረበ ቃለመጠይቅና ዝርዝር መልስ

## የመምህራን ቃለ መጠይቅ

የትምህርት ቤቱ ስም/ኮድ/ ከፍተኛ

የመምህሩ ኮድ 01

ሰዓት 4:30 ቀን ___________

ውድ መምህር ይኸ ጥናት በ11ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን

1. በመንግስትና በግል ት/ቤት የሚያስተምሩ መምሕራን ምሳሌ እንደሰጡት የተዘጋጀ መጠይቅ ነው::

**ጥያቄ** በዕህፈት ክሂል ላይ ስለ አያያዥ ቃላት ሀረጎች ምንነትና አጠቃቀም የስተምራሉ ወይ የሚል ነው::

**መልስ** በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ሰፊ ሽፋን አይሰጡም በአጠቃላይ አስተምሬአለሁ:: በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ገብቻለሁ::

**ጥያቄ** ስለ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት አከፋፈል በሚመለከትስ ያስተምራሉን ማለት በተለያዩ ክፍል ይከፈላሉ እነዚህ በዚህ ክፍል እነዚህ ደግሞ በዚህ ከፍ በማለትና በመመደብ ያስተምራሉ::

**መልስ** ተማሪዎች የሚያውቁት ነገር ነው:: አጠቃላይ የሚያውቁት ነገር ነው::

**ጥያቄ** አጠቃላይ የሆነ ነገርነው የምነግራቸው አያያዥ ቃላት ማለት ምንድን ነው? በምን በምን ነው? ሁኔታ ነው የምንጠቀምባቸው የት ቦታ ነው? ይሄ የት ቦታ ነው የሚገባው? የሀሳብ ዝምድና ያላቸው የሚያያይዙ አሉ አፍራሽ የሆኑ ነገሮች የሚያያይዙ አሉ? እና እንዳአገባባቸው የትየቱ ጋ እንደሚገቡና እንደሚጠቀሙባቸው አጠቃላይ የሆነ ነገር ነው ገለፃ የማደረግላቸው

**ጥያቄ** እንግዲህ አጠቃላይ የሆነ ነገር ይህ ነው እንጂ በዚህ ክፍል ይመደባሉ አያያዥ ቃላትና ሀረጎች በሁለት በሶስት ወይም በአራት ይከፈላሉ እንዚህ እነዚህ ናቸው ብለህ አላስተማርክም::

**መልስ** አዎ በዚህ መልኩ ከፋፍዬ አላስተማርኩም

**ጥያቄ** ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ ጊዜን ለማመልከት፣ ፅሁፋቸውን ለማደራጀተ ወይም ለማዋቀር የራሳቸውን አተያይ/አመለካከት/ ለማመልከተ /ለመጠቆም/ ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጋት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስተምረው ያውቃሉ?

**መልስ** አዎ አምና በተለይ ስለድርሰተ የሚያነሳ አለ አንቀፆች እንዴት እነደሚሰፋፋ እዚህ ላይ አያያገሮችን እንዴት እንደምንጠቀምባቸውና አንቀፆችን እንደምናስፋፋቸው የተለያዩ ቦታ እያስገባን አንቀፅትን እንደምናሳድግ/እንደምናስፋፋ ነወ ያስተማርኩት

ጥያቄ ተማሪዎችም ተጨማሪ ሀሳብ ተቃራኒ ሀሳብና ምክንያታዊ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን በማመልከት ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላትና ሀረጎች አስተምረው ያውቃሉ?

መልስ ይህ ምንድነው ጥያቄዎቹ ዝርዝር ነገሮች ናቸው እና እኔ ስለአያያዥ ቃላቶች አምና ሳስተምር አንደኛ መፅሀፍ አጭር ንበተን ነው የሚሰጠው አጭር መግለጫ አብዛኛው ለተማሪዎች ተማሪ ተኮር እንደሚባለው ሁሉ ነገር የሚሠሩት ተማሪዎች ናቸው እኔ እንዳልኩህ በጣም ጥርት ያለ ነገር ሳይሆን አጠቃላይ የሆነ ነገር ነው የምሰጣቸው እንደዚህ እየከፋፈልኩ በዝርዝር እንዳስቀመጥኩት አይደለም በዚህ መልኩ አላስተማርኩም::

ጥያቄ ተማሪዎች የድርሰት አፅፈው ሲያውቁ በአያያዥ ቃላትና ሀረጎች አጠቃቀም ዙሪያ እርማት ይሰጣሉ? የሚሰጡ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ሁል ጊዜ ወይስ አልፎ አልፎ (የሚል ጥያቄ አለ?)

መልስ ያው እርማት መስጠት የግድ ይጠበቀበናል ምክንያቱም ትምህርት የጋራ ስራ ስለሆነ ከመልመጃዎች በኋላ እርማት ይኖራል ወጥ የሆነ አንድ ማስተካከያ ይኖራል በዛ መሠረት እናደርገዋለን:: ብዙ ጊዜ ደብተራቸውን አርማለሁ እርስ በርስ እንዳተራረሙስ እስንሁን ባለው ሁኔታ አላደርግም በግሩፕ ስራ እንጂ እርስ በርስ እንዲያርሙ አላደርግም::

ጥያቄ የአያያዥ ቃላትንና ሀረጎችን አከፋፈልና አመዳደብ ሲያስተምሩ በ11ኛ ክፍል መረሃ ትምህርትና ከ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሀፍ ውጪ ሌሎች (የት/መረጃ መሣሪያ) ድጎፍ ሰጪ መፃህፍትን ተገልግለዋል በምንጭነት ተገልግለዋል /ይገለገላሉ የሚሉ/ ነው::

መልስ መማሪያ መፃህፍትን በዋነኝነት እንጠቁማለን የግድ ተዛማጅነት ያላቸው መፃህፍት እንጠቀማለነ ምክንያቱም እንዳንድ ጊዜ እዚህ መማሪያ መፅሀፍ ላይ የተፃፈ ሌላ ቦታ ስትሄድ የመፋለስ ሁኔታ አለ:: ብዙ ጊዜ ይህ ነገር ከተማሪዎች ጋር ውዝግብ ይፈጥራል:: ይህን ጉዳይ ለማስተካከል ብዙ ጊዜ በመጠቀሻነት የተለያዩ መፃህፍትን እጠቀማለሁ::

ጥያቄ ምን አይነት መፃህፍት ነው የምትጠቀሙ

መልስ እዚህ ቤተመፃህፍት አሉ ብዙ ጊዜ ከስነፅሁፍ ጋር በተያያዘ ከሆነ የአቶ ዘሪሁን አስፋው የስነ ፅሁፍ መሠረታውያን እጠቀማለሁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ከ9-12 የሚል አጠር አጠር ያሉ ኖቶችና ጥያቄዎች አሉት እሱ ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ::

ጥያቄ እግረመንገደህንም ስለ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በሚመለከት እመለከታለሁ::

መልስ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን ከፋፍለህ ታስተምራለህ ወይ ነው ያልከኝ ወደኋላ ልመለስና አያያዥ ቃላትን በመከፋፈል አላስተምርም በጥቅሉ ነው /በአጠቃላይ/ ነው የማስተምረው::

ስለሀረግ አምናም 10ኛ ክፍልም ዘንድሮም በ11ኛ ክፍል እነሱን እየከፋፈልኩ ነው የማስተምረው

**ጥያቄ** ስለ ድርሰት ምንነትና አፃፃፍ ዘዴ በተማሪዋችም ትምህርት ሰጥተው ያውቀሉ?

**መልስ** አዎ ስለድርሰት ምንነትና የድርሰት አይነቶች በማል ሰለ አፃፃፍ ዘዴአቸው አስተምሬአለሁ የድርሰት አይነቶችን በተለይ አራቱን አስተምሬአለሁ በ10ኛ ሆነ በአስራ አንደኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ በተወሰነ መልኩ የሚነንንው ስላለ አስምሬአለሁ::

**መልስ** የተለያዩ ድረሰቶተን እንዲፅፉ አላደረኩም

**ጥያቄ** የ11ኛ ክፍል የአማርሃ ቋንቋ ተማሪዎችም በሚፅፉት ፅሁፍ የአያየኸር ቃላትና ሀረጋት አጠቀቀማቸውን በተመለከተ ጠቅለል ያለ ሀሳብ ቢሰጡኝ?

**መልስ** አብዛኛውን ጊዜ እኔ የመማሪያ መፅሀፍን ተከትዬ ነው የምሄደው አንዳንድ ከጊዜውም ጋር ከምን ጋር በማያያዝ የተለያዩ ፅሁፎችን እንዲፅፉ ብዙ ጊዜ አላደረኩም እነዚህ ነገሮች ጋ ከአያያኸር ቃላተና ሀረጋት ጋር ያለው ግንኙነት በሚመለከት ሠፋ ያለና የሄድኩበት ሁኔታ የለም በሂደት ምናልባት በጥልቀተ ልየው እችላለሁ::

**ጥያቄ** ቢሰበሰቡና በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ባለው ባስቀመጠው መልኩ ታስተምራለህ እግረመንገድህንም እርማት ትሰጣቸዋለህ?

አመሰግናለሁ::

የትምህርት ቤቱ ስም/ኮድ/ እናት

የመምህሩ ኮድ 02

ሰዓት 8፡00 ቀን __________

በአስራአንደኛው ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምላሽ እንዲሰጡበት የተዘጋጀ ቃለመጠይቅ ነው::

ይህ ጥናት በመንግስትና በግል ት/ቤት የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቂ መምህራን ምላሽ እንዲሰጡበት የተዘጋጀ ነው::

**ጥያቄ** በዕህፈተ ክሂል ትምህርት ላይ ሰለአያየኸር ቃላትና ሀረጎች ምንነትና አጠቃቀም ያስተምራሉ

**መልስ** አራቱ የክሂል አይነቶች ፅህፈትን ጨምሮ በየደረጃው አለ የማንበብ የመፃፍ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎት አሉ እነዚህ በተወሰነ ደረጃ አሉ እ. . . ምንድን ነው ተሰበጣጥረው ነው የሚገኙት እ በቀጥታ መናገር ይኖሯል መጀመሪየ እዛ አነድ ምንባብ በማቀርብበት ጊዜ እዛ ውስጥ የማዳመጥ አለ የማዳመጥ ክሂሎቸውን ተማሪዎች ያዳብራ ከዛ በኋላ ደግሞ እንደዚሁ የመናገር ክሂላቸው ደግሞ ጥያቄዎችን በመመለስ ያዳብራሉ ከዛ በኋላ ደግሞ የተለየዩ ጥያቄዎች አሉ በነዛ መሠረት ክሂላቸውነ እንዲየዳበሩ የሚደረግበት ሁ

ኔታ አለ:: እ. . . ቅደም እንዳልከኝ ግን ይሄ ከአያያዥ ቃላትና ሀረጎች እነሱ እራሳቸውን የቻሉና የተወሰነ ቦታ ነው ያላቸው ሰፊ ሽፋን አልተሰጣገርው በጣም በጥቂት ሁኔታ ነው እኔ ያጋጠመኝ አንደኛ ስሚስተር ላይ ትንህ ቦታ ነው እሱም አንድ ሁለት ቀን አይበልጥም ስለአያያዥ ቃላት ያስተማርኩት ከዛ በኋላ ደግሞ ስለሀረግም እንደዚሁ መሀል አካባቢ የተወሰነ አለው ስለሀረግ ምንነትና ስለሀረግ አይነቶች ባጠቃላይ አስተምራለሁ:: ዘጠነኛ ሆነ አስረኛ ክፍል አስተምሬአለሁ:: በዘጠነኛ ክፍል የለም 10ኛ ክፍል እና አስራአንደኛ ክፍል አስተያያዥነት አላቸው::

ጥያቄ 2 የአያያዥ ቀላትና ሀረጋትን አከፋፈልና አመዳደብ በሚመለከት አስተምረዋቸው ያውቃሉ ያስተምራሉ:: ማለት አያያዥ ቃላትና ሀረጎች በተለያዩ ክፍል ይከፈላሉ እነዚህ በዚህ ክፍል እነዚህ ደግሞ በዚህ ክፍል በማለት ተማሪዎችዎን አስተምረዋል

መልስ ዞሮ ዞሮ ስለአያያዥ ቃላት ተማሪዎች የሚያውቁት ነገር ነው ቋንቋ ሲባል እንግዲህ አማርኛ ብቻ ሳይሆን እንግሊዝኛ ውስጥም ይማሩታል ገን ምንድነው እኔ አጠቃላይ የሆነ ነገር ነው የምነግራቸው አጠቃላይ የሆነ አያያዥ ቃላት ማለት ምንድነ ነው? ጠቀሜታቸው በምን ሁኔታ ነው የምንጠቀምባቸው የት የት ቦታ ነው እንዴት ነው እንትናቸውን ጠብቀው ይሄ የት ቦታ ነው የሚገባው የሀሳብ ዝምድና ያላቸውን የሚያያይዙ አሉ፣ አፍራህ የሆኑ ነገሮችን የሚያያይዙ አሉ እንደ አገባባቸው የት የቱጋ እንትን እንደሚለና እንደምንጠቀምባቸው አጠቃላይ የሆነ ነገር ነው ያው . . . ገለፃ የማደርግላቸው::

ጥያቄ እንግዲህ አጠቃላይ የሆነ ነገር እንጅ አያያዥ ቃላትና ሀረጎች በሁት ወይስ በሶስት ወይም በአራት ይከፈላሉ እነሱም እነዚህ እነዚህ ናቸው ብለው አላስተማሩም::

ጥያቄ ተማሪዎችዎ ድርሰት ሲፅፉ ጊዜን ለማመልከት ፅሁፋቸውን ለማደራጀት ወይም ለማዋቀር የራሳቸውን አተያይ ወይም አመለካከት /ለማመልከት ወይም/ ለመጠቆም/ ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስተምረዋል?

መልስ አዎ አስተምራለሁ እንዳልኩህ ነው በተለይ 10 ቅፍል ስለድርሰት ምንነትና አፃፃፍ የሚል ክፍለ ነበረ እዛ ላይ አያያዥ ቃላትን የማነካካ ቦታ አለ:: እዛጋ እንትሮች አሉ አንድም ከሱ ጋር በተያያዘ አንቀፅ የማስፋፊያ መንገዶች የሚል አለ ከዛ ጋር በተያያዘ አንቀፆች እንዴት እንደሚያስፋፉ እዚህ ውስጥ ደግሞ አያያዥ ቃላቶች እንዴት እንዴት እንደምንጠቀምባቸው እዛ አካባቢ ማለት ነው:: እንዲህ እንዲህ አይነቶችን እንዳልኩህ በተወሰነ መልኩ ነው የምናያቸው ያየኋቸው ማለት ነው:: በጋራ እንዲሰሩ እንደዚህ እርስ በርስ የመነጋገር ነው እንጂ እርስ በርስ ደብተር ተለዋውጠው እንዲተራረሙ እኔ እስካሁን አላደርግም::

ጥያቄ ገን ደብተራቸውን ወስደህ ታርማለህ::

መልስ አዎ ወስጄ አርማለሁ::

ጥያቄ የአያያዥ ቃላትና ሀረጋትን አጠቃቀም ሲያስተምሩ ከ11ኛ ክፍል መርሃ ትምህርትና ከ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሀፍ ውጪ ሌሎች (የት/መርጃ መፃሪያዎች) በምንጭነት ተገልግለዋል

መልስ ይኖራል ብዙውን ጊዜ እንታበኖቹ እንኚን ብዙም አይኖሩም ያው መማሪየ መፅሁፉ ነው የለው እሱ በዋነኛነት እንጠቀማለን ከዛ በኋላ ደግሞ የግድ ትንህ ተዛማጅነት ያላቸውን መፅሀፎች እናያለን ምክንያቱም ምንድነው መሰለህ አንዳንዱ ጊዜ እዚህ መፅሀፍ ላይ የተፃፈው ነገር ይኖራል። እና ሌላ ቦታ ስትሄድ የመይበስ ሁኔታ ምናምን አለ እና እነዚህ ነገሮች በተማሪዎች ላይ ብዙ ጊዜ ኮንቪኝሮን ይፈጥራል። ያንን ለማስተካከል እኔ ብዙ ጊዜ በማጣቀሻነት ያው እጠቀማለሁ። ብዙ ጊዜ ከስነፅሁፍ ጋር የተያያዘ ከሆነ የአቶ ዘሪሁን አስፋው የስነፅሁፍ መሠረታውያን የሚባል መፅሀፍት አለ እሱ አጠቀማለሁ ከዛ ውጪ ደግሞ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ከ9-12 የሚል ደግሞ አለ አጠር አጠር ያሉ ኖቶችና ጥያቄዎች አሉት እሱ ጋ ብዙ ጊዜ እጠቀማለሁ።

ጥያቄ ስለአያያዥ ቃላትና ሀረጎች በሚመለከት ታያለህ ማለት ነው? ማጣቀሻዎችን ታያለህ?

መልስ አዎ እግረመንገዴን ይቀርታ ወደኋላ ልመለስ ቅድም አንድ ጥያቄ ምንድነው ከፋፍለህ ታስተምራለህ ነው ያልከኝ አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን አያያዥ ቃላተን ብዙውን ጊዜ ምክፍል አይደለም የማስተምረው በጥቅል ነው ቀድም እንዳልኩህ አንቀፆችን እንደምናስፋፋባቸው ያው የሰያዬ ቦታ እያስገባን አንቀፆችን ማሳደግ እነደምንችል አምና ያስተማርኳቸው።

ጥያቄ ተማሪዎችዎ ተጨማሪ ሀሳብ ተቃራኒ ሀሳብና ምክንያታዊ ሀሳብ ያላቸው መሆኑን ለማመልከት ስለሚጠቀሙባቸው አያያዥ ቃላተና ሀረጎች አስተምረው ያውቃሉ?

መልስ አሁን ይሄ ምንድነው ጥያቄዎቹ ዝርዝር ነገሮች ናቸው። አዋ እና እኔ ስለአያያዥ ቃላቶች አምና ሳስተምር እነዳልኩህ እንደሃ መፅሀፍ አጭር ትንተናን ነው የሚሰጠው አጭረ መግለጫ ነው ከአብዛኛውን ለተማሪዎች ተማሪ ተኮር እንደሚባለው ሁሉን ነገር የሚሠሩት ተማሪዎች ናቸው። እነ እንዳልኩህ በጣም እንትን ያለ ነገር ሳይሆን አጠቃላይ የሆነ ነገር ነው የምሰጣቸው እንደዚህ እየከፈልኩ በዝርዝር እየስቀመጥኩ አይደለም በዚህ መልኩ አላስተማርኩትም።

ጥያቄ ተማሪዎችን ድርሰት አፅፈው ሲያበቁ በአያያዥ ቃላትና ሀረጎች አጠቃቀም ዙሪያ እረማተ ይሰጣሉ የሚሰጡ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ሁልጊዜ ወይስ አልፎ አልፎ (የሚል ጥያቄ አለ)

መልስ ያው እርማት መስጠተ ሁልጊዜ ነው ያለነው በመማረ ማስተማር ሂደት እርማት መስጠተ የግድ ይጠበቀብናል። ምክንያቱም ትምህርት የጋራ ስራ ስለሆነ ሁሌ እናደርገዋለን። እና ምንድን ነው ሁስገዜ ይጠቀማሉ ወይ ነው አዎ ማለት ያው አንድ እንትን ይኖራል፡ ብዙውን ጊዜ እንደዚህ አይነት ነገሮችን የምንሰራው ከመልመጃዎች

ጋር በተያያዘ ነው መልመጃ ከስራ በኋላ ወጥ የሆነ አንድ የሆነ ማስካኪያ ይኖራል::
አዎ በዛ መሠረት ያው ታረማለሁ::

**ጥያቄ** ደብተራቸውን ወስደህ ታርማለህ

**መልስ** አዎ ደብተር አርማለሁ በዙ ጊዜ እነዱውም እኔ እንትን ከዚያ ጋር ነው ከደብተር ጋር . . .

**ጥያቄ** እርስ በርስ እንዲተራረሙስ?

**መልስ** እኔ እስካሁን ባለው ሁኔተ አላደረገም ተማሪዎች እርስ በርስ ሳይሆን ምናልባተ የገሩፕ ስራዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሀረግ አምሃም 10ኛ ክፍል ዘንድሮም እየከፋፈልኩ ነው የማስተምረው እያንዳንዱን ሀረግ ባህሪው እንዴት ነው ይመናምን እያንዳንዱን ከፋፍዬ ማለት ስማዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረግ በማለት በእንትን እየከፋፈልኩኝ እሱ ላይ ትንሽ ከዛኛው በተሻለ ሰፋ አድርጌ ሰጥቻለሁ::

የትምህርት ቤቱ ስም/ኮድ/ <u>የካቲት</u>

የመምህሩ ኮድ 03

ሰዓት 4፡00 ቀን ______________

**ጥያቄ** አያያዥ ቃላትንና ሀረጋትን ከክፍል ውስጥ አስተምረው ያውቃሉ::

**መልስ** ከዕፊት ክሂል ጋር በተያያዘ አያያዥ ቃላትና ሀረጋትን አስተምራለሁ::

አያያዥ ቃላትን ከአገልግሎታቸው አንፃር ከፋፍዬ አስተምራለሁ በሚና ከፋፍለን እናስተምራለን በአጠቃላይ በዚህ የተነሳ ከማጠቃለል አንዳንድ ደግሞ ቀጣይነት ያላቸው መሆኑን መጀመሪያ አንድ ሀሳብ ይኖራል በቀጣይነትም በተጨማሪም በዚያው ሀሳብ ዙሪያ ተመሳሳይነት ያለው መሆኑ ነው::

ሌላው ለተማሪዎች የሚነገራቸው አገልግሎት አንፃር ተመሳሳይና በምክንያትና በውጤት የሚደገፉ ነገሮች በሚመጡበት ሰዓት አያያገሮችን እንጠቀማለን ለምሳሌ ሲጋራ ማጨስ መጥፎ ነው ስለዚህ ከዚህ እንድትቆጠብ::

በርካታ አያያዥ ቃላትን ከነተግባራቸው ለተማሪዎቹ አስተምራለሁ:: በ11ኛ ክፍል የመማሪያ መፅሐፋቸው ላይ ቢያንስ 8 ቃላት ተዘርዝረውላቸው መ/መፅሀፍ ስለሚጠይቁ የግዴታ ከዚህ አንፃር ት/ቱ ይሰጣል::

**ጥያቄ** የእዚህ የአያያዥ ቃላት አከፋፈልና አመዳደብ አስተምረው ከሆነ በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ ብለው አስተምረዋቸዋል ዝርዝራቸውስ::

**መልስ** ዋና ዋና ዎቹ በ3 እና በዚያ አካባቢ ነው ከፋፍዬ የማስተምራቸው::

1ኛ. ተጨማሪ ሀሳብ ሲኖር በዚያ ዙሪያ የሚታከል አካይ ተጨማሪ ሀሳብ አፍልቃል::
2ኛ. ጊዜዎችን በማመልከት የምንጠቀምባቸው አያያገሮች አሉ ለምሳሌ ባለፈው ጊዜ፣
3ኛ. ደግሞ አንድ ሀሳብ ይቀራብና ያው ሀሳብ ከሌላው ሀሳብ እንደሚለይ ለማመልከት አስተምራለሁ ለምሳሌ ሁለት አንቀፅ ይቀርባል እንደሚል ማለትም በሌላ በኩል በማመልከት፣

- የልየታ የጊዜ ጠቀስ የተጨማሪነትን /አካይ/ አስተምራለሁ::

ጥያቄ ተማሪዎችዎ ድርሰት ሲፅፉ ጊዜን ለማመልከት ፅሁፍቸውን ለማደረጃት የራሳቸውን አተያይ ለመማልከት የሚጠቀሙባቸው አያያገሮች ለተማሪዎችዎ አስተምረው ያውቃሉ?

- ፅሁፋቸው በጊዜ ቅደም ተከተል ተሰናስሎ መደራጀት አለበት ምክንያቱም ነገ የ12ኛ ክፍል ቀጥሎ የተቋም ተማሪዎች ናቸው ስለዚህ በደንብ አስተምራቸዋለሁ::

ጥያቄ ተጨማሪ ተቃራኒ ምክንያታዊ ሀሳብን ለመጠቆም የሚጠቀሙባቸው አያያገሮች አስተምረው ያውቃሉ?

መልስ በ8ኛ ክፍል ምክንያት ውጤት በዚህ ምክንያት ከዚህ የተነሳ ለማስተማር ሞክሬአለሁ::

ጥያቄ ተማሪዎችዎን ፅሁፍ /ድርሰት/ አፅፈው ሲያበቁ አያያዥ ቃላትን በተመለከተ እርማት ሰጥተው ያውቃሉ ሁል ጊዜ ወይስ አልፎ አልፎ እርማት የማይሰጡ ከሆኑ አያያዥ ቃላትን ለይተው አርመዋል ወይ ለተማሪዎች ምሳሌ ምላሽ አላቸው ወይ::

መልስ እንደማፅፋቸው የድርሰት አላማ ይለያያል የተወሰነ ርዕስ ተሰጥቷቸው ወይም በመማሪያ መፅሀፋቸው በተሰጣቸው ርዕስ ተንተርሰው ተማሪዎች እንዲፅፉ ከሆነ አላማው ይለያያል:: ለምሳሌ ስለተለያዩ ስርዓተ ነጥብ ከልሆነ ይቻላል:: ስርዓተ ነጥብ ከሆነ ትኩረቴ በስርዓተ ነጥብ ላይ ነው:: ነገር ግን አያያዥ ቃላት ሳስተምር መፅሀፉም ስለሚያስተምር አያያዥ ቃላተን በተመለከተ ድርሰት እንዲፅፉ ካደረኩ እርማቴም ሆነ ምጋቤ ምላሽ የምሰጣቸው አያያዥ ቃላትን በተመለከተ ይሆናል::

